# ተማሪነት

ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ ለዛሬ ማስታወሻዬ መነሻዬ ናቸው፤ እኚህ ስመጥር በ1948 ዓ.ም **«የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም»** የሚል መፅሐፍ ፅፈዋል፤ ከስድሳ ዓመት በፊት ለህትመት የበቃውን ይህን ሀብት እኔ ያነበብኩት በቅርቡ ነበር።

የደራሲው አጠቃላይ ግንዛቤ ለመርዳት እንዲያግዘን ተከታዮቹን መልዕክት ተኮር የሆኑትን አባባሎች አስቀድሜ በመቀጠል ስለ ተማሪነት ጥቂት ነጥቦችን አስተዋውቃለሁ፡-

- «ሰው በዚህ ዓለም ሲቆይ መማር ያስፈልገዋል» (ገፅ 19)
- «ሰው…የመመራመር ችሎታ ተሰጥቶት የተፈጠረ ነው» (ገፅ 25)
- «ሰውን ሰው የሚያደርገው የሚኖርበት ማህበርና በዙሪያው የከበበው ዓለም ነው» (ገፅ 71)
- «ሰው የሚኖርበት ማኅበርና ዙሪያውን የከበበው ዓለም ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ሁለተኛ ፈጣሪዎቹ ናቸው» (ገፅ 71)
- «ተማሪ ቤት የእውቀት ገበያ ናት» (ገፅ 92)
- «ተማሪ ቤት ባይኖር የሰው ግዛቱ ከመሬት አልፎ በባህር፣ በአየር፣ ለመስፋፋት ባልቻለ ነበር» (94)

የተቀሩትን በየገፁ የሚገኙ እምቅ ግንዛቤ ያዘሉ አባባሎችን ለአንባቢዎቼ ትቼ የተማሪነት መነሻ





ቃል የሆነው የ«ተማረ»ን ፍቺ ሀዲስ እንደተረጎሙት ላስተዋውቅ «ሰው የማያውቀውን እንግዳ ነገር በሰው፣ በመፅሐፍ ወይም በሌላ አማካኝነት ሲያውቅ ተማረ» ይባላል።(ገፅ 11)

ይህን ፅኑ ፍቺ ተግባራዊ ለማድረግ እና ተማሪነት ዘላቂ እንዲሆን ሶስት መሰረታዊ ሀብቶች መኖር ይገባቸዋል፤ እኒህ ሶስቱ በተናጥልና በትስስር ተማሪን ፈጥረው ተማሪነትን ያፈልቃሉ።

ሀዲስ አለማየሁ ትምህርት **ከሶስት ማዕከላት ይቀዳል** ሲሉ የመጀመሪያው የቤተሰብ ትምህርት፤ ሁለተኛው የተማሪ ቤት ትምህርት፣ ሦስተኛውን የማህበር ትምህርት በማለት አከታትለዋል።

እኔም ተማሪነትን እሳቸው ባስተዋወቁበት ጎዳና ባጓጉዘው ብዙ እንደምንጠቀም ልብ አልኩኝ፤ እኔ ብቻ ግን አይደለሁም በተለይም ወላጆች ፤ መምህራን፤ ሕብረተሰብ በዋናነት በተማሪና ተማሪነት ጉዳይ ላይ ስፍራ እንዳላቸው ልብ በሉ። **«የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም»** ድርሳን «ውጤታማ ማህበረሰብና ጠንካራ ሀገር ከወዲሁ ይታወቃል» ይላል ለአባባሉ ዋቢ ሲጠራም።

በትምህርት ስራ ላይ ቤተሰብ ወሳኝ ነው፤ ብዙዎች ዕውቀትን በአቋራጭ መንገድ ከትምህርት ቤት እንደሚያገኙ በማሰብ በቅርባቸው ያለውን የገዛ ሐላፊነታቸውን በመተው ተማሪ ተማሪ ቤት የሚገባበትን ቀን ይጠብቃሉ፤ ይህ ግን ልከኛው መመዘኛ አይደለም ውጤታማነት ዕማሮን በማግኘት መሰረቱን የሚጥለው ከህፃንነት ጀምሮ ነው፤ ያም በቀዳሚነት የልጅ ቀራቢ የሆኑትን ወላጆች ይመለከታል፤ የወለዱ ልጆቻቸው ተገቢ በሆነው ስብዕና ይቀረፁ ዘንድ ራሳቸው ወላጆች በአግባቡ መቀረፃቸውን እያስተዋሉ በወለዷቸውም ላይ ይጥሩ ዘንድ ግድ ነው።

ሀዲስ «…የህፃን አእምሮ ሊቀረፅ እንደተሰናዳ ርጥብ ጭቃ ነው፤ ርጥብ ጭቃ በመልካም ሆነ በመጥፎ አከኳኋን እንዳነፁት ወይም እንደቀረፁት ይታነፃል፤ ይቀረፃል፤ እንዲህ ያለውም ህንፃ ወይም ቅርስ ካልደረቀ ከመጥፎ ወደ መልካም… እንደገና ተለውጦ ሊታነፅና ሊቀረፅ ይችላል፤ ከደረቀ በኋላ ግን ካልተሰበረ ሊለወጥ አይችልም የህፃን አእምሮው በርጥብነቱ በመልካምም ሆነ በመጥፎ አኳኋን እንደቀረፁት ይቀረፃል፤ ስለዚህ የቤተሰብ ትምህርት ከሌላው ትምህርት ሁሉ ቀዳሚ በመሆን መሰራች ነው…» (ገፅ 26) በማለት ሕፃናት ወደ ተማሪ ቤት ከመምጣታቸው በፊት ቤተሰብ ያለበትን ኃላፊነት ያውጃሉ።

በተማሪነት ሕይወት ውስጥ የተማሪ ቤት መኖር ደግሞ በልጆቹ ሕይወት ውስጥ የተደራጀ ዕውቀትን ለማስገኘት ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ድረስ ማዕከላት ይኖሩ ዘንድ ግድ ነው።

ይህን ተቋም ሀዲስ ሲገልጡት «ማህበሩ የራሱን ደኅንነት ዓላማ በማድረግ ባሰናዳው የትምህርት ፕሮግራም እያንዳንዱ ተማሪም የራሱን ኑሮ ለማሻሻል በሚማረው ትምህርት እርስ በርሳቸው ይጠቃቀማሉ ነገር ግን ማኅበሩ ከዚህ የዘረዘራቸውንና እነሱንም የመሳሰሉት የትምህርት ፕሮግራም ሲያሰናዳ ለታሪኩ፣ ለባህሉ፣ ለስርዓቱ፣ ለልማዱና ለኑሮው እንደሚስማማው አድርጎ ስለሚያሰናዳ ተማሪዎቹ ለማኅበሩ ታሪክ፣ ባህል፣ ስርዓት፣ ልማድና ኑሮ ጋር ተስማምቶ የተሰናዳውን የትምህርት ቤት ትምህርት መቀበልና ገንዘብ ማድረግ የቻሉ እንደ ሆነ ራሳቸውንም ማህበረሰባቸውንም መጥቀም ይችላሉ» (ገፅ 58) ይላሉ።

ይህ ገለፃ በትምህርት ማዕከላት የተገኘ ተማሪ ዕውቀቱን በመቅሰም ከመምህራኑ እና ከዚያ ከሚገኙት ሰነዶች ሁሉ ተጠቃሚ በመሆን ማደግ በተማሪነት ወግ ውስጥ ይቀጥላል፡፡ ይልቅኑ መምህራን፣ ከቤተሰብ የተረከቧቸውን ህፃናት ተረክበው ቀናዎቹን የበለጠ በማቅናት ጠማሞችን አቅንተው ለማሳደግ ኃላፊነትን እንደወሰዱ ከወዲሁ ልብ ማለት ተገቢ ነው።

በመጨረሻ ተማሪነት ቤተሰብን ያማከለ፣ ትምህርት ቤትን ያማከለ ሕይወት ብቻ ሳይሆን በአቻነት ሕብረተሰቡ በራሱ እውቀት (ትምህርት) መሆኑ ነው፤ ይህን ሀዲስ አለማየሁ የማህበር ትምህርት በማለት ይጠሩታል ሲያብራሩም ከህብረተሰቡ የሚገኘው ዕውቀት የቤተሰቡም፤ የተማሪ ቤቱም አካል ነው፤ ሶስቱ መጋቢያን ተሳሳሪነት ኖሯቸው የሚዘልቁ እንጂ በመቀዳደም አይጋጩም ይልቅስ «ለሰው የሚኖርበት ማኅበርና ዙሪያውን የከበበው ዓለም ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ሁለተኛ ፈጣሪዎቹ ናቸው» (ገፅ 72) ከዚህም የተነሳ ተማሪ በሰዎች መካከል የተገኘ ፍጡር መሆኑን ልብ ማለት ዕውቀትን ከሰፊው የዓለም ሕብረተሰብ ሁሉ በመገብየት ራሱን ሊቀርፅ ያስችለዋል።

እነዚህ ሶስቱ ተሳስረው ባሉበት ቦታ ሁሉ ውጤታማነት፣ ፍሬያማነት አለ፤ ተማሪነት በዘላቂነት በየሰው ሕይወት ውስጥ ሰፍኖ ሲታይ ግላዊና ሀገራዊ እድገት በአስተማማኝነት ይታያል የተማሪነት ትርጉምም እውን ይሆናል።

እናንተ በመደበኛውና በኢመደበኛው የትምህርት ዓለም ውስጥ ያለፋችሁ ሰዎች ዛሬ ተማሪን ተረከባችሁ ትቀርፃላችሁ፤ ነገ ልጆችን ወልዳችሁ በሕይወታችሁ ታንፃላችሁ፣ መሰረትን ትጥላላችሁ በተያያዥም የህብረተሰቡ አባል ከመሆናችሁ የተነሳ አርቃችሁ በመመልከት ለሰው ልጆች ደህንነት የሚበጀውን ሁሉ ታደርጉ ዘንድ ሀላፊነት አለባችሁ ይልቅኑ በክርስቶስ በመሆን የጌታን ፈቃድ ለመፈፀም የወሰናችሁ ወንድሞችና እህቶች ምን ያህል የፀና አደራ ይኖራችሁ።



# መምህርነት

በመምህርነት ሙያ በርካታ አመታትን አስቆጥሪያለሁ። በእነዚህ ጥቂት በማይሰኙ ዓመታት ውስጥ መምህር ሆኜ እንድቀጥል ያስቻለኝን መሰረታዊ ምክንያትን ደግሞ ፈትሼ አግኝቼዋለሁ።

ተማሪ ሳለሁ የነበረኝ የማወቅ ፍላጎት፣ ጉጉት እና ጥረት በየዓመቱ በገጠሙኝ ተማሪዎች ላይ ማየት ቀዳሚው የአስቀጣዬ መሰረት ነው፤ ሊማሩ የወደዱ ሁሉ በየርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዴት? መቼ? የት? ለምን? ብለው ይጠይቁኛል፤ ባልረኩበት፣ ባላስተዋሉት እና በተደናገሩበት ሁሉ ላይ ያደረግነውን የጋራ ምክክራችን ስመዝን ግርምትን፣ አድናቆትን፣ ፍካትንና እረፍትን እንደሚለግሳቸው ልብእላለሁ። ይህ ምልከታዬ የማያቋርጥ ትጋትን ይፈጥርብኛል፤ በውጤቱም ተማሪዎቼ አስተማሪዎቼ ሆነው አገኛቸዋለሁ፤ ሕያውነት ያለው ዐውዳዊ ቅብብልም የየዕለት እንጀራዬ በመሆኑ ከማዕዱ አለመለየትን መምረጤ ለጥቅሜ ነው።

እንግዲያስ ተጠቃሹ ምክንያቴ በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የተከናወኑ ግኝቶች ናቸው፤ ሌላኛው ተማሪዎች ከመደበኛው የትምህርት ዓለም ወጥተው በሙያ መስኮቻቸው ተሰማርተው የማግኘት ዕድለኝነት ነው፤ በየጊዜው አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ስሜታዊ፣ ማህበራዊ እና መንፈሳዊ ዕድገታቸውን የአቅሜን ያህል ስታዘብ ከርሜ ኋላ ደግሞ በሁሉ ዘርፍ ማደጋቸውን ሳያቋርጡ ሰክነው ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውን፣ ሕብረተሰቡን፤ ሀገራቸውን እና ዓለምን ሲጠቅሙ አገኛቸዋለሁ፤ እሰማቸዋለሁም።

ማግኘቴ እና መስማቴ ደግሞ ትንሽ ሳለሁ መምህሬ «የሰውን አእምሮ በአግባቡ መቅረፅ መቻል ምንኛ ያስደስታል» ያሉኝን አስበውና እኔም የመምህርነት እውነተኛ ፍሬ በትዕግስት የጠበቀውን ፍሬ መብላቱ ነው እያልኩኝ ለመፅናቴ ሌላኛው አንኳር ጉዳዬ አደርገዋለሁ።

ሦስተኛው**መምህራን ባይኖሩ ኖሮ እንዴት እንሆን ነበር?**የሚል ፅሑፍ ከሁለት ዓመት በፊት ማንበቤን አስታውሳለሁ ፅሑፉ ምርምራዊ ነው፤ በዚያ ንባብ «አንድ ሺህ ቀናት ለብቻ አቀርቅሮ ከማጥናት አንድ ቀን ከጥሩ መምህር ጋር ማጥናት ይሻላል» የሚለውን የጃፓኖች ምሳሌ ዘክሯል፤ ዛሬ በስልጣኔ ልቀው የሚገኙት ጃፓኖች የመደነቃቸው ሁነኛ መንስኤ የመምህራን አግባብነት ያለው የመማር ማስተማር ስራ መሆኑን አብዛኛው የጃፓን ሕዝብ ያምንበታል፤ በሀገሬም ይህንኑ ርዕሰ ጉዳይ አስበዋለሁ።

«መምህራን ባይኖሩ ኖሮ ኢትዮጵያስ ምን ትሆን ነበር?» ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ ዘላቂው ባለዕድሜ ድረስ ዓይን ገላጭ መምህር ባይኖር የደረስንበትን ያክል እንኳን እንደርስም ነበር፤ እላለሁ ይህ መመፃደቅ አይደለም እውነት ነው፤ መምህር ሆኜ ለተማሪዎቼ ስልትን ማመላከቴ፤ አቋራጭ መፍትሔን ማቅረቤ፣ ችግር ፈቺ አጣቋሚ መሆኔ፣ የተዘጋ የመሰለውን ከፍት ማድረጌ፣ የሺውን ቀን ጨለማ በብርሀን መተካቴ፣ መምህር ሆኜ ለመከረሜ ሌላኛው ሚዛን ደፊ ጉዳዬ ነው።

ግና እነህ ሶስቱም ምክንያቶቼ የእኔ ብቻ ሊሆኑ አይችሉም የመምህራን ሁሉ ናቸው። አራተኛውና የመጨረሻው ደግሞ «ለሌላው መኖር» የሚችል ቀዳሚ የሕብረተሰቡ ተጠሪ መምህር መሆኑ ነው። በመሰረቱ ዘላቂና አትራፊ ስራን ለመስራት ፍቅር ወሳኝ ነው። ሰውን የመውደዱ ፍቅር የገዛ ልጁን ሳይሆን የሌላውን ሰው ልጅ መውደድ አብዩ ምክንያት ነው።

ይህን ፍቅር በብዙ ፈተናዎች ውስጥ እያሳለፉ ማጤን ይቻላል፤ የተማሪዎች ስነ- ምግባር በአሉታዊ ተፅዕኖዎች እየተሸረሸረ የአስቸጋሪው ቁጥር ሲጨምር ለመምህሩ የሚከፈለው ክፍያ የማያወላዳ ሳይሆን ሲቀር በየጊዜው በስራ ላይ ተጨማሪ ጫናዎች እየበረከቱ ሲመጡ፤ ከሕብረተሰቡ በተለይም በገዛ ተማሪዎቹ የሚያገኘው ምስጋና፣ አክብሮት እና ዕውቅና ሲጠፋ አንዳንድ ወላጆች የልጆቻቸው ቀዳሚ አሳቢ መሆናቸውን የዘነጉበት ሁኔታ እያደገ ባለበት ወቅት፤ መምህር ሆኖ መዝለቅ ፍቅር ነው። ይህም በእኔም በአጋሮቼም ውስጥ ስላለ መጪውን ዓመት ለመቀበል እኔ አልሰጋም።

እናንተ የዘንድሮ ሰዎች እውነት እውነቱን የነገርኳችሁ ሆን ብዬ ነው፣ የሕፃናት፣ የልጆች፣ የወጣቶች እና የጎልማሶች መምህር ሆኖ ራስን ማግኘት ትልቅ ሐላፊነትን ከመረከብ ጋር ተያያዥ ነው። ዕድገትን በተመለከተ የተሟላ ሙሉ ስብዕና በአግባቡ እንዲያቆጠቁጥ መሰረት የሚጣልበት ዕድሜ የተማሪነት ዘመን ነው። እነርሱን የማስተማር ዕድል ገጥሟችሁ በጥንቃቄ በአግባቡ ካሳደጋችኋቸው ያድጋሉ ካቀጨጫችኋቸው ይቀጭጫሉ። ሁሉን ከነፈጋችኋቸው ደግሞ በሕይወት እያሉ ይሞታሉ። ሕያዋን ግን ሙታን፣ ከዚህም የተነሳ ለስራችሁ እና ለልጆች ፍቅር ይኑራችሁ፣ የደሞዛችሁ መለኪያ





ሙሉ ስብዕናን የተላበሱ የሕብረሰቡ የልጆች ዕድገት ብቻ ይሁን ይልቅኑ ጥበብ በተሞላው አቀራረብ ኢየሱስንና ትምህርቱን ከገለፃችሁማ እንዴት ታደላችሁ!

# እግዚአብሔር ፀሎትን ይሰማል

*ለፀሎት መልሶቻችን ተገቢ ዝግጅት ማድረግ*

«ከለመኑት» ሁሉ ይጠበቃል።

ፅሑፌን ሁነኛ ታሪክ በመግለፅ እጀምራለሁ፤ ታሪኩ ያነበባችሁት ወይም የሰማችሁት ሊሆን ይችላል፤ አልያም «አዲስ» ከሆነባችሁም ደስ እያለኝ እቀጥላለሁ።

***

- ሐምሌ 16/1884 ወይዘሮ የሺ እመቤት ዘጠነኛ ወንድ ልጃቸውን በሰላሙ ተገላገሉ።
- ከተገላገሉ በኋላ ወገኖቻቸው ልጁን በሱፍ ጨርቅ ጠቅልለው በአገልግል አድርገው ይወስድባቸው ስለነበር እናትየው «ልጅ በደህና ወልጄ ታቅፌ ለማሳደግ ስፈልግ ብዙ ተሳቅቄያለሁ ይህ ዘጠነኛው ፅንሴ እጅግም አላስቸገረኝም ነበር ሕይወት እንዲኖረው መነጠል አለበት ካላችሁ በጤና አድጎ በሰላም እንዳየው እናንተም ፀልዩልኝ...» ነበር ያሉት።
- ተፈሪ ተወልዶ ከሁለት ዓመቱ በኋላ ወይዘሮ የሺመቤት ምጥ እንደገና ይዟቸው በጭንቅ ውስጥ ገቡ፤ ልጁ ተወለደ ግን ሕይወት አልነበረውም፤ እሳቸውም በጣር ውስጥ ገቡ ብዙም አልቆዩም መጋቢት 6/1886 ላይ እኩለ ሌሊት ላይ አረፉ።
- ራስ መኮንን ልጅ እንዲኖራቸው ባለቤታቸው በአረገዙ ቁጥር ይፀልዩ ነበር፤ ባለቤታቸውም





እንዲሁ ይፀልዩ ነበር፤ ግን ከ10 ምጦች ዘጠኙፅንሶች በሕይወት ይኖሩ ዘንድ አልቻሉም ሁሉም እንደ ተወለዱ ሞተዋልና።

- ራስ መኮንን የፀሎታቸውን መልስ አግኝተው ግን በመልሱ ውስጥ ተከታታይ ፀፀት እንደገጠማቸው **«ረዥሙ የስልጣን ጉዞ»** የሚለው መፅሐፍ «...ከብዙዎቹ መካከል አንድ ለእናቱ ሆኖ የተረፈላቸውን ልጃቸውን ተፈሪን ሳያዩት እና ሳያቅፉት በመሞታቸው ባለቤታቸው ራስ መኮንን ዕድሜያቸውን ሙሉ ሲፀፀቱ ኖሩ» ይላል።(ገፅ 22) ወይዘሮ የሺመቤት ልጅን ያሳየኝ ብለው ፀልየው ነበር ግን ሳያዩት ሞቱ ራስ መኮንን የሰው ምክር በመስማት ብቻ ልጁን ከእናቱ ባለማስተያየታቸው «ይህን መቼ አሰብኩኝ» በሚል ፀፀት ሲቃጠሉ ኖሩ።

ያ! አንዱ ልጅ ግን አድጎ (ከዚህ በሁዋላ አንቱ ማለት ይገባኛል) በኢትዮጵያ አልጋ ወራሽም ንጉስም ሆነው ከ60 ዓመት በላይ ገዝተው፤ ከ80ዓመት በላይ ኖረው አለፉ። በውኑ፤-

- ሰዎች ስለምን ይፀልያሉ? በፀሎት መልሶቻቸው ላይ ያላቸው ዝንባሌስ ምን ሊሆን ይገባል?
- ሰዎች የፀሎታቸው መልስ ከሆነው ጉዳይ ጋር እስከምን ድረስ ሊጓዙ ይገባል?

***

ከ1983 በፊት የነበረው የኢትዮጵያ መንግስት በርካታ ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም የዛኑ ያህል በርካታ ደካማ ጎኖች ነበሩት።

በተለይም ደካማ ጎኖቹ ሁሉን አቀፍ በመሆን ጉዳት የማድረስ አቅማቸው እየሰፋ ሲመጣ የኢሕአዲግ ጦር አዲስ አበባን ሲከብ ኢትዮጵያውያን ወደ እግዚአብሔር መፀለይን እንደ ሁነኛ መፍትሄ ቆጥረው ወደ እግዚአብሔር ፊት በግልና በጋራ በተከታታይ ይቀርቡ ጀመር።

ሀ. መንግስት በጦርነት መፅናቱን እንደ መፍትሄ አካል በመጠቀሙ ሀገሪቱ የደም መሬት እንዳትሆን ተፀለየ፤

ለ. ወንጌላውያን ክርስትያኖች ከ1967 ጀምሮ በተከታታይ የእምነት ነፃነታችንን ከቀደመው በበለጠ በማጣታቸው፣ ህንፃዎቻቸው በመወረሱ እና እግዚአብሔር የለሽ ማህበረሰብ መስፋፋት አማኞችን በፀሎት ወደ ጌታ አስቀረበ፤ በዚህም ጦርነቱን አቁምልን፣ የእምነት ነፃነትን ስጠን በማለት

ተለማመኑ። እግዚአብሔርም ሰማ፡ ቀጥሎስ ምን ሆነ፡- የፀሎታቸውን መልስ እግዚአብሔር ሲሰጥ እነርሱ «እንዴት አድርገው ተጠቀሙበት?» ምላሹ ለቀጣዩ እንቅስቃሴ ብዙዎች አልተዘጋጁም የሚልነው።

አለመዘጋጀታቸውን የሚጠቁመን በ2001 ዓ.ም ደረጀ ከበደ የዘመረበት «የነፃነት ልጆች» ዝማሬ ነው፡-

የነፃነት መዘዝ የአምልኮ ነፃነት
በበጎቹ መግቢያ ተኩሎች ዘው አሉበት
ስርዐት የሌለበት
ገደብ የሌለበት
የኢየሱስ ስም ለንግድ ጨረታ የወጣበት
ለአምልኮ ነፃነት ሱባኤ ተገብቶ
መሰደድም ቀረ ከላይ ትዕዛዝ ወጥቶ
መግቢያ በሩ ሰፋ ሰው ተግተለተለ
እንክርዳዱ ስንዴ ተኩላው በግ መሰለ
የድል አጥቢያ አርበኛ ዘለቀ ሆ ብሎ
ውጪያው ምሰሉን ወጉን አስተካክሎ።

ከዝማሬው በመነሳት እግዚአብሔር ሱባኤ የገባውን ጉባኤ ሰምቶታል፤ ግን ፀላዮቹ

- ቤተ ክርስቲያን ስለመመስረትና ስለ ወንጌል ስርጭት፣
- ደቀመዝሙር በማድረግ ስለመፅናት፣
- ሀገሪቱን በሰላም ወንጌል በማስተዳደርና በመምራት ጉዳይ ላይ እግዚአብሔር ፀሎታችንን ሲመልስልን «እንዴት እንዴት እናደርገዋለን?» የሚል ቅድመ ዝግጅት አብዛኛው አልነበረውም።

አለመኖሩ የሚታወቀው ከፀሎቱ መልስ ማግስት ጀምሮ በተከሰተ በርካታ ደካማ ገፅታዎች ነው፤ በቤዛ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ፀሎትን በሚመለከት ያለው እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ትክክለኛ ነው። ከዚህም የተነሳ ላለፉት በርካታ ዓመታት የፀሎት ርዕስ ያስመዘገብናቸው «መዝገበ ፀሎት» እየሞሉ ተቀይረዋል፤ ያሁኑም ትልቅ ድርሳን «ሞልቶ» ተርፏል።





በየሀሙሱ፣ በየእሁዱ ፀልየን ጌታ ፀሎታችንን እንደፈቃዱ ሰምቶልናል።

ከምስጋና ርዕሶቻችን፡-

- ታምሜ ድኛለሁ፤
- በሰላም ተገላግያለሁ፣
- በሀዘኔ እግዚአብሔር አፅናናኝ
- ትምህርቴን አጠናቀቁ
- አገልግሎቴ ሰፋልኝ
- መፅሐፌ ታተመልኝ
- ስራ ያዝኩኝ
- ቤተሰባችን ተረጋጋ
- የተጣሉት ታረቁ ወዘተ...

እነዚህ ሁሉ የልመና ርዕሶች ምላሽ ነበሩ፤ ግና፡-

- እግዚአብሔር ፀሎትን ሰምቶ ያዳነው እንዴት እየኖረ ነው?
- ከሀዘኑ ያፅናናው ምን እያደረገ ነው?
- ልጅን የታቀፉ ወላጆች ልጃቸውን እንዴት እያሳደጉ ነው?
- የአገልግሎት ዕድል የገጠማቸው ምን ያህል ፍሬያማ ስራ እየሰሩ ነው?
- የታረቁ ግንኙነታቸውን ለማደስ ምን እያደረጉ ነው?
- በቤተክርስቲያናቸው ሰላምንና ፍቅርን ለመለሰላቸው ጌታ በቀጣይነት በግልና በጋራ ምን እያደረጉ ነው?

***

እግዚአብሔር ፀሎታችንን ይሰማል፤ ይህንንም ማቴ 7፡7 ለምኑ ይሰጣችኋል፣ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ አንኳኩ በሩም ይከፈትላችኋል፤ የሚለምን ሁሉ ይሰጠዋል፣ የሚፈልግም ያገኛል፤ ለሚያንኳኳም በሩ ይከፈትለታል ይላል።

በሽታ በእርግጥም ከሕብረተሰቡ ከመለየት ባሻገር በእግዚአብሔር መቅደስ እንዳይገኙ አድርጓቸው ስለነበር ተሰቃይተዋል፤ መፍትሄ አለው የተባለውን ሰው ዝና ሲሰሙ ግን ወደ እርሱ መጥተው ለመኑት ጌታም ፀሎታቸውን ሰምቶ ምላሽ ሰጣቸው፤ ተፈወሱ፤ ግና ከአስሩ አንዱ ብቻ ነበር የመፈወሱ ሁነኛ ግብ እግዚአብሔርን ማክበር እንደነበር የተረዳው ከዚህም የተነሳ ተመልሶ ጌታውን አከበረ፤ ጌታ ግን ስለተቀሩት ዘጠኙ ተናገረ የፀሎት መልስ ተጠቃሚነት ዘርፈ ብዙ ነው፤ ብዙዎቹ ግን በአግባቡ ተጠቅመው የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየፈፀሙበት አይደለም።

## ቁም ነገር ስስት

ልከኛ ግንኙነት ከሕያው እግዚአብሔር ጋር ማድረግ የሚችሉ ሁሉ መለኪያ አላቸው፤ ፀሎታቸውም ይሰማላቸው ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የእርሱ ልጆች የመሆንን መብት ያገኙ ናቸው፤ ልጆቹ «እንደ ፈቃዱ ፀልየው በተቀበሉት የእግዚአብሔር ቸርነት በምድር ላይ ሲኖሩ ከራሳቸው ውጭ ሌሎችን የመመልከት ግዴት አለባቸው፤ ያ ግዴታ «ሰውን እንደ ራስ አድርጎ በመውደድ ፍቅር» ይገለፃል፤ ፍቅር ደግሞ በተገቢው ፍቺው በ፣ቆሮ 13፡1-8 ተተርጉሟል፤ የትኛውም የፀሎት ጥያቄ በምላሹ በቀጥታ ከራስ ጋር የተያያዘ ቢመስልም ምላሹ ግን ከሰዎቹ ጋር ተገናኚ ሆኖ እንዲዘልቅ እግዚአብሔር ወስኗል፤ ይህን የሱን ፈቃድ ለመፈፀም ዝግጅቱን ከወዲሁ ማጤን፣ ማመንና መተግበር ከተጠያቂነት ያድናል፤ እግዚአብሔርም ይከብራል፤ በግል፣ በቤተሰብ፣ በማህበርም ሆነ በሀገር ለውጥ ይታያል።



# ተግዳሮቶች

ተከታዮቹ ጥያቄዎች ለንባባችን መነቃቂያ ስለሆኑ ልብ እንበላቸው።

- ተግዳሮቶች የሚገጥሙን ለምንድን ነው?
- ተግዳሮቶችን መከላከል ይቻላል ወይ?
- ተግዳሮቶችን ማሸነፍስ እንዴትይቻላል?

***

በጠበበ መንገድ ላይ ሁለት ቀንዳም ፍየሎች ተገናኙ። እንዲሁም በአንድ ገመድ የታሰሩ ሁለት የተራቡ አህያዎች በየፊናቸው መኖ ተዘጋጀላቸው።

***

አንድ ፍየል ብቻ በሚያሳልፍ አንዲት መንገድ ላይ፡- አንዱ ከአዲስ አበባ ወደ ደብረዘይት እየሄደ ሌላኛው ከደብረ ዘይት ወደ አዲስ አበባ እየመጣ ባለበት ቀጭን መንገድ ላይ ተገናኙ። እነዚህ ፍየሎች፡-

ሁለቱም መድረሻ ግብ አላቸው፤ ሁለቱም የየራሳቸው ጉዳይ አላቸው፤

ሁለቱም ጊዜውን በመሻማት ሊጠቅም የሚችል ስራ መስራት ይፈልጋሉ፤

ሁለቱም ፍየል በመሆናቸው የጋራ ማንነት አላቸው። ይሁን እንጂ ትውውቅ የላቸውም። በየራስ ዝግጅታቸው ኑሮዋቸውን በመምራት ሲጓዙ አንድ ፍየል ብቻ ከሚያሳልፈው ጠባብ ድልድይ ላይ ተገናኙ፤

ድልድዩ በመቶ ሜትር ገደል ላይ የተሰራ እልፍ እላለሁ ብለው ቢስቱ ከማይተርፍበት እንጦሮጦስ የሚወርዱበት አደገኛ ስፍራ ላይ ተገናኝተዋል።

በተገናኙበት ስፍራ ግን ምኞታቸውን ከዳር ለማድረስ ግንባር ለግንባር ተገናኝተው ተገፋፉ፤ ተሞካከሩ፣ ተለታተሙ፤ አንዱ ሌላውን ለመግፋት ሞከረ ሌላውም በተራው እየገፋው ዘለቀ።

በዚህ ሁሉ አንዲት ጋት ሁለቱም ፈቅ ማለት አልቻሉም፤ ሁሉም ነገር ከትግል ጋር በዚያው ቆመ።

***

ሁለቱ አህያዎች ሲሰሩ ውለዋል፤ ሁለቱም ሸከም በዝቶባቸው ነበር። ሁለቱም ረጅም ጉዞ ተጉዘዋል፤ ሁለቱም ባለቤቶቻቸው የጫኑባቸውን እየጨመሩባቸው ዘልቀዋል፤ እንዲህም ቢሆን:-

- ሁለቱም በቂ መኖ በየአቅጣጫቸው ተዘጋጅቶ ጠብቋቸዋል፤

- እንዲህም ቢሆን ሁለቱም በአንድ ገመድ ታስረዋል፤

- ሁለቱም በረሀባቸው ልክ ወደ መኖው ተሳሰቡ፤ ሁለቱም ግን ወደ ተዘጋጀው መኖ አልደረሱም።

ከዚህ የተነሳ የኋላ እግራቸው የደረሰ ያህል አንዱ ሌላውን ይራገጥ ጀመር፤ መኖው አልተነካም እነሱ ግን በመጓተት ተሰቃዩ በእርግጥም ተጎዳዱ።

***

ተግዳሮት ተገድግዶ አላሳልፍ ሲል ወይም ጠቦ አላስገባ አላስወጣ ሲል ያ ምክንያት የሆነው ምንም ነገር ተግዳሮት ወይም Challenge ተብሎ ይጠራል ፍየሎቹም ከጉዞው ተገትተዋል፤ አህዮቹም በረሀባቸው ላይ ጉዳትን ጨምረዋል።





ክርስትና ከክርስቶስ የተነሳ ስሙን ያገኘ እምነት ነው። ክርስቲያን ማለትም ከክርስቶስ ጋር ያለ ወይም የእርሱ ተከታይ ማለትነው።

እንኪያስ ክርስትና ክርስቶስንና የክርስቶስን ትምህርት ቅድሚያ በመስጠት ራሱን የሚያኖር እምነት ነው፤ በምድር ስንኖር ለመኖር የሚያበቁ በርካታ ነገሮችን ከቤተሰቦቻችን፣ ከማህበረቡ እና ትምህርት ከምናገኝባቸው ተቋማት በማግኘት እንጠቀማለን።

ክርስቲያን ስንሆን ግን ክርስትያን የመባል አቅምን ያገኘነው ከእግዚአብሔር በመወለዳችን ብቻ ነው፤ ኒቆዲሞስን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ዳግም ልትወለድ ይገባል» በማለት እንደ መከረው፤ ይኸው እውነት በየግላችን ተግባራዊ በሆነ ግዜ ክርስቲያን እንባላለን።

የተግዳሮት ምንነት ሁለት ልደትን ከማግኘት ጋር ይያያዛል፤ ከሰው መወለድ፣ ከእግዚአብሔር መወለድ፤ የምድር ዜግነት፤ የሰማይ ዜግነት አብረው የተያያዙለት ሰው በእርግጠኝነት ተግዳሮት በዘመኑ ሊገጥመው ይችላል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙርነትን ሲያስተዋውቅ ክርስቲያን ሆኖ መኖርንና የእርሱ ተከታይነትን ቀዳሚ ተግባር በማድረግ ከመነሻው ልክ የሆነውን አስተማረ።

«ኑ ተከተሉኝ ሰዎችን አጥማጆች አደርጋችኋለሁ» አላቸው(ማቴ 4፡20) ይህ ጥሪ ለሁለቱም ወንድማማቾች ለጴጥሮስና ለእንድርያስ ብቻ የተሰጠ መመሪያ አይደለም። ለማንም በክርስቶስ ለተጠራ ሁሉ የሚሰጥ ሐላፊነት ነው፤ሰውን ማጥመድ ወንጌልን በመስበክ ክርስቲያን በማድረግ አይቆምም፤ ክርስቲያን ተብለው የሚጠሩትንም በዘመናቸው ሁሉ የእርሱ ተከታዮች ሆነው እንዲዘልቁ ሐላፊነትን መስጠት ወይም መወጣት ነው፤ ሰዎች በእግዘአብሔር ነገር ብቻ ተጠምደው እንዲኖሩ የመጣር እና የማድረግ አደራ ክርስቲያን ተብለው በተጠሩ አማኝ ወንድና ሴት ኑሮ ውስጥ መገለጥ ይኖርበታል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ቃሌን ሰምቶ በተግባር የሚያውል ቤቱን በዐለት ላይ የሰራን ብልህ ሰው ይመስላል። ዶፍ ወረደ፣ ጎርፍም ጎረፈ፣ ነፋስም ነፈሰ፣ ያንን ቤት መታው በዐለት መሰረት ላይ ስለተመሰረተ አልወደቀም» (ማቴ 7፡24) በዚህ ገለፃ «ቃሌ» ያለለት የኢየሱስ ትምህርት ነው፤ ትምህርቱ ሰዎች ሁሉ ሊታዘዙት የተገባነው፤ ይልቁኑ አማኞች የማያመቻምቹበት መመሪያቸው ነው።

የቤዛ ባፕቲስት የአባላት መታወቂያ «የእግዚአብሔር ቃል የእምነታችንና የተግባራችን መገለጫ መሆኑን ያበስራል፤» ከአስሩ ዝርዝር ውስጥ የመጀመሪያው እሱ ነው፤ ይህ መሆኑ ተገቢም

ትክክልም ነው፤ ከጋሪው በፊት የሚቆመው ፈረሱ ጋሪውንና በጋሪው ላይ ያሉትን ሰዎች ጎትቶ ወደ ተፈለገው ስፍራ ያደርሳል፤ በተቃራኒው ቢሆን ግን ስህተት ይሰራል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተግዳሮት መኖሩን አልደበቀም፤ የሚጎርፍ ጎርፍ፣ የሚጠራርግ ንፋስ አለ፤ ይህ በሰው ታሪክ ውስጥ በዘላቂነት ይኖራል፤ ቢሆንም ከዚህ ለመትረፍ አግባብነት ያለውን መሰረት ከመነሻው በመጣል መዝለቅ የአንድ ክርስቲያን ሕይወቱ አልያም የኑሮ ግዴታው ነው።

ዘላቂነት ያለው መሰረትና በድል የሚዘልቅ ኑሮን ክርስቲያኖች እንዲኖራቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤ ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው እኔም እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» (ማቴ 28፡18-20 )አለ።

የክርስትና ስያሜ ከክርስቶስ ጋር ተያይዞ መቀጠልን ያመላክታል። ክርስቶስ ባስተማረውና ባዘዘው መፅናት ደግሞ ዳግም ተወልጄያለሁ ባለ አማኝ ኑሮ ውስጥ ሊገለጥ ግድ ነው።

ኢየሱስ ያለ በቂ ምክንያት «ስልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል» አላለም፤ ኢየሱስ አማኑኤል የተባለበትንና የሆነበትን ታሪክ በሞቱ በትንሳኤውና በዕርገቱ ተግባራዊ አድርጓል። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ መሰረታዊ ችግር እንዲሁም ዘላቂ እንቅፋቱን ፈቃደኛ ሆኖ በመስቀሉ መስዋዕትነትና በትንሳኤው ሀይል አስወግዶታል፤ በዚህም እግዚአብሔር አብን አርክቷል፤ ልብ ካልን ተሰቅሎ ሳለ ነበር በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ የሆነው። በፍፃሜውም ላይ ነበር ከፍ ባለ ድምፅ «ተፈፀመ» በማለት የብስራቱን አዋጅ ያወጀው፤ በዚያ ጊዜ ነበር የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ለሁለት የተቀደደው፤ በዚያ ወቅትም ነበር ምድር ተናውጣ ዓለቶች የተሰነጣጠቁት፣ መቃብሮችም ተከፍተውእንቀላፍተው የነበሩት ብዙዎች ቅዱሳን የተነሱት፤ እኒሁ ሰዎችም ነበሩ ከኢየሱስ ትንሳኤ በኋላ ወደ ቅድስት ከተማ ገብተው ለብዙዎች የታዩት» (ማቴ 27፡45-56)

እነዚህ ክንውኖች ኢየሱስ በሰማይና በምድር ስልጣን እንደተሰጠው ይናገር ዘንድ ያደርገዋል፤ በዚህ ግዜ ውስጥ ነው፡-

አማኞች ወይም ክርስቲያኖች ከዲያብሎስ ፍርሀት ነፃ የወጡት፣ ሰውን ከእግዚአብሔር ለይቶት የነበረው የሀጢአት ጉልበት የተረታው በዚህ ግዜ ነው «ኢየሱስ» ተብሎ መድሀኒት ይሆን ዘንድ፣ «አማኑኤል» ተብሎ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በተለይም ከእርሱ ከሆኑት ጋር መሆኑ





የተረጋገጠው ወይም የፀናው፤ እንግዲህ በዚህ እውነት ነው ተግዳሮትን የምንመዝነው።

ያዳነን የጠራን ጌታ በሰማይ ቢሆን በምድር የበላይ የሆነ ባለስልጣን እሱ ብቻ ሆኗል። እርግጥ እሱ በአካል በሰዎች መካከል ዛሬ የለም፤ ባይኖርም መለኮት የሆነው መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶናል፤ እሱም የክርስቶስን ፈቃድና ሀሳብ፣ ትምህርቱንም ጭምር እለት ዕለት እያሳወቀን ያስተዳድረናል።

በዚህም «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው» ከእኛ ጋር ከሆነልን ከእግዚአብሔር ጋር ሆነን በምድር ላይ ለቀናት፣ ለወራት፣ ለአመታት እንኖር ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኗል።

በክርስቶስ ያሉ ክርስቲያኖች ተግዳሮቶች በየጊዜው ይገጥማቸው ዘንድ ይችላል። ይህም የሆነው ከእግዚአብሔር በመወለዳቸው ምክንያት ነው፤ የእግዚአብሔር የሆነው ፈቃዱን ይፈፅሙ ዘንድ ተለይተዋል፤ ከዚህም የተነሳ አስተሳሰባቸው፣ እምነታቸው አደራረጋቸው ሁሉ እግዚአብሔር ከወደደው ጋር መጣጣሙን የማየት ሐላፊነት በእነርሱ ላይ አለ። ይህን ሐላፊነት ለመወጣት በሚፈጠርው ሂደት ውስጥ ተግዳሮት ይኖራል።

አባል በሆንኩባት ቤተክርስቲያን ያሉ አባላት በውሀ ጥምቀት ሲቀላቀሉ ከእጃቸው ከሚገቡት ሁለት ነገሮች አንዱ መታወቂያ ሲሆን ሌላው መተዳደሪያ ደንቡ ነው፤ በመታወቂያው ላይ «ስራ» የሚል አለበት፤ በዚያ ላይ የሚፃፈው «ምስክርነት» የሚል ነው፤ ስራችንና አገልግሎታችን ምስክር መሆን ነው፤ ያየነውን፣ የሰማነውን፣ በራሳችን የሆነውን፣ እንዲሁም ምስክሮቼ ትሆናላችሁ የተባልንበትን ኢየሱስን የመግለፅ ስራ በእያንዳንዳችን ላይ ኖሯል፤ ከዚህም የተነሳ በሰዎች ሁሉ ፊት በቃልና በተግባር ቃለ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ብርሀን የገለፀልንን በመኖር የምንዘልቅ ምስክሮች ነን።

እንኪያስ ምስክር ሆነናል ወይስ ጥብቅና ቆመናል፤ ምስክር ሆነናል ወይስ ዝምታን መርጠን ተሸብበናል፤ ምስክር በመሆን ጨለማውን ገልጠናል ወይስ ለጨለማው መጨለም ተጨማሪ ዕድል ፈጥረናል፤ ምስክር በመሆን የሕይወትን ሽታ በሕይወት ሊኖሩ ላሉት፣ የሞትን ሽታ በፍርድ ስር እንዳሉ በማሳወቅ መዝለቅ አልያም ተደላድለንና ተቻችለን፣ ቀይጠና ሸቅጠ መኖርን በመምረጥ የተግዳሮት መነሻም መደምደሚያም ሆነናል።

***

አስታውሱ ፍየሎቹና አህያዎቹ በፈተና ላይ ናቸው። ተግዳሮት ገጥሟቸዋል። ፍየሎቹ መለታተም ጀምረዋል። በዚሁ ከቀጠሉ ሁለቱም ይጎዳሉ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው ከፊል ጉዳት ይገጥማቸዋል።

ሁለቱም በቁመት ተመጣጣኝ፣ በዝርያ አንድ ናቸው ይህ ደግሞ አስፈሪ ያደርገዋል። መለታተም የጀመሩት ፍየሎች ከመሞካከር በሁዋላ ቆመው አሰቡ። በውጤቱም ሁለቱም ከግባቸው እንዲደርስ አንደኛው ቆሞ ሳይሆን ተኝቶ ሌላውን ለማሻገር ፈቃደኛ ሆነ፡፡ አደረገው። ከዚህም የተነሳ ሁለቱም ተላለፉ።ተግዳሮት ሲመጣ ከመጎዳዳት በፊት ረጋ ብሎ ማሰብ ከዚያም የተገደገደውን በአግባቡ ማስተናገድ መቻሉን ከእነዚህ ፍየሎች ምሳሌ መማር ይቻላል።

***

እህያዎቹ ተጎዳድተዋል፤ ተረጋግጠዋል፤ የሚታይ እንጂ የማይበላ የሆነላቸውን መኖ በዚህ አካሄድ ፈፅሞ ሊያገኙት አልቻሉም፤ ጉልበታቸውን ከጨረሱ በኋላ ግን ሁለቱም አህያዎች የእኔ የሚለውን የከረረ እምነት በመተው «ለምን የእኔን መኖ አንተ ዞረ መጥተህ በአንድ ላይ አንበላውም፤ ስንጨርስ ደግሞ የአንተን በአንድ ላይ አንበላውም» በሚል ድንቅ ምክር ትግሉ ተረታ። ተግዳሮቱ ተወገደ፤ «የእኔ ማለት የአንተ ነው ያንተ የሆነውም ለእኔ ይጠቅማል» ሌላውን እንደራስ አድርጎ የመውደድ ተግባር ነው።

***

በመሰረቱ አገልጋዮች ሁሉ ሰዎች ናቸው፤ እነዚህ ሰዎች ደግሞ ደካማ ፍጡራን ናቸው፤ ቤተክርስቲያን ዳግም በመወለድ የክርስቶስ የሆኑትን ሁሉ ያለልዩነት ትሰበስብ ዘንድ ስለሚገባ ሰዎችን በዕድሜ፣ በፆታ፣ በዘር፣ በነገድ፣ በትምህርት ልዩነት አትደለድልም። ከዚህም የተነሳ ከፍተት ለመፍጠር ምክንያት የሚሆኑባት እንቅፋቶች በተጨማሪ አሉዋት። ቤተ ክርስቲያን የገሀነም ደጆች ሊቋቋሟት የማይችሏት ተቋም ብትሆንም፡- ዲያብሎስን በመቃወም እንድትፀና ተመከራለች።

እንደ እውነቱ ከሆነ  ከዚህ እውነት የተነሳ ክርስቲያኖች በምን በምን ይፈተናሉ? በማለት ዕድሜን ያማከለ፣ ልምድን ያማከለ፤ ዝርዝር ተግዳሮቶች ማቅረብ የማያዋጣ ነው፤ ይልቅስ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር የሆነውን ፈቃድ በአግባቡ እንዳይወጡት እንቅፋት ስለሚሆነው መሰረታዊ ጉዳይ ብቻ ተነጋግረን እንጨርስ።

እንቅፋቱን አለማወቅ፣ ማንነትን መዘንጋት፤ ከእግዚአብሔር ዕቅድ የወጣ ግንዛቤን ማዳበር ሁነኛው የክርስቲያን እንቅፋት ነው፤ ራሷን ያላወቀች እናት እና ሁለት ልጆቿ በጉዳዩ አስበው፣ መክረው፣ ያዋጣናል የሚል ጥያቄ ወደ መምህራቸው ሶስት ሆነው ይዘው መጡ በወቅቱ አስር ደቀመዛሙርት ተመልካች ሆነው ጉዳዩን አደመጡ፤ ካደመጡ በኋላም እነርሱ የተግዳሮቱ (የእንቅፋቱ) ባለቤቶች ሆነው ተገኙ፤ የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከልጆቿዋ ጋር ወደ ኢየሱስ ቀረበችና እጅ ነሳች አንድ ነገር እንዲያደርግላትም ለመነችው። ኢየሱስም «ምን ትፈልጊያለሽ?» አላት እርስዋም





«በመንግስትህ እነዚህ ሁለቱ ልጆቼ አንዱ በቀኝህ አንዱ ከግራህ እንዲቀመጡ አድርግልኝ» አለችው ኢየሱስ «የምትለምኑትን አታውቁም...» አላቸው ሙሉ ገለፃው በማቴ 20፡21-28 ላይ ተፅፏል።

አማኞች፣ አገልጋዮች፣ ክርስቲያኖች የእንቅፋቱ ተጋሪ ላለመሆን ራሳቸውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን በቅድሚያ እግዚአብሔርን ማወቅ እና ዘላቂውን የጌታን አደራ በተግባር ማዋል አለባቸው።

የዘብዴዎስ ልጆች እናታቸውን ተናጋሪ እና ጠያቂ አድርገው በኢየሱስ መንግስት ልጆቿ በግራና በቀኝ እንዲቀመጡላት ለመነች። እሱ ግን ሶስቱንም «የምትለምኑትን አታውቁም» አላቸው፤ በዚህ ውዝግብ የተቀሩት አስሩ ደቀመዛሙርቱ በቁጣ ተሞሉ በጥቅሉ አስራሁለቱ ደቀመዛሙርት አገልጋዮች ቢሆኑም ግን እነርሱ ያላለፏቸው ተግዳሮቶች ነበሩዋቸው።

የሁሉም አቅም ድንገተኛ በመሰለው ጥያቄ ነበር የተገለጠው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሊኖሩት የተገባውን ዘላቂ መመሪያ አሳወቃቸው፤ እሱም «የአህዛብ ገዢዎች በሕዝባቸው ላይ ጌቶች እንደሚሆኑ በኃይልም እንደሚገዟቸው ታውቃላችሁ» አላቸው።

ኢየሱስ ግልፅ የሆነውን ሀገራዊ አገዛዝን በማንሳት ፍቅር የሌለው፣ ትህትና የጎደለው፣ የግል ማንነትን ሊያገዝፍ የወደደ አገዛዝ በገዢዎች ዘንድ እንደነበረ አሳይቶ ሊሆን የተገባውንና ተግዳሮትን የማሸነፍ ፀጋ ግን ምን መሆን እንዳለበት ነገራቸው *«በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን የበላይ ለመሆን የሚሻም የእናንተ ባሪያ ይሁን የሰው ልጅ እንዲያገለግሉት ሳይሆን ለማገልገልና ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት መጥቶአልና»* አላቸው።

ይህ የኢየሱስ ገለፃ ሰፊ ማብራሪያ ሊሰጠው አያስፈልግም። ተግዳሮትን ለመቋቋም ኢየሱስ የመጣበትን ተልዕኮ መመልከትና ለሌላውም የመኖር መገለጫ የሆነውን ፍቅርንና ትህትናን ቀዳሚ በማድረግ መዝለቅ የተግዳሮት መቋቋቋሚያ ሆነ። ይህ ነው በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ እረፍትን፣ ነፃነትን፣ ደስታን እየተካፈልን እንድንኖር የሚያደርገው።

ከዚህ ከወጣ ግን ከክርስቶስ የተነሳ ክርስቲያን ያስባለንን አቅም እናጣዋለን። ከዚያም አልፎ «እግዚአብሔር የሌለ ያህል የሚመስልን ኑሮ እንኖራለን። በፅዮን ያየህ መፅሐፍ ውስጥ **«እግዚአብሔር በእርግጥ አለ?»** የሚል ፅሑፍን አንብቤያለሁ፡-

«ፀጉር አስተካካዩ» የሚያስተካክለውን ሰው እኔ **ግን እግዚአብሔር አለ ብዬ መቼም አላማምንም?ይላቸዋል** ሰውየውም «ለምን እንደዚህ አልክ? መቼም ምክንያት ይኖርሀል ብዬ አገምታለሁ» ይሉታል።

ፀጉር አስተካካዩም «ቀላል ጥያቄ ጠየቁኝ ይህን በር ከፈት አድርገው ብቻ ቢመለከቱ መልሱን ያገኙታል። ስፍር ቁጥር የሌለው ሰው በድህነት፣ በስቃይ፣ በደዌ ሲማቅቅ ያያሉ እውነቴን ነው የምሎት እሱ ኖሮ ቢሆን ይህን አያደርግም ነበር» በማለት በእርግጠኝነት ይመልሳል። ሰውየው በልባቸው «ለዚህ ዓይነት ዓይነ ጠባብ ምን መልስ ይሰጣል» በማለት አዝነው ይወጣሉ። እንደወጡ ግን አንድ ፀጉርና ፂሙ ጭብርር ያለ መቀስና ምላጭ ለዘመናት ያላዩት የሚመስል ሰው በመንገድ ላይ አዩ! ፈጥነው ወደ ፀጉር አስተካካዩ ሄደው:-

*«አንተ ፀጉር አስተካካይ በኢትዮጵያ እንደሌለ ታውቃለህ?»* በማለት ድንገተኛ ጥያቄ ያቀርቡለታል። አስተካካዩም «ተው እንጂ እኔ ህያው ምስክር አይደለሁም እንዴ» ይላቸዋል።

ተስተካካዩ ግን «በጭራሽ ፀጉር አስተካካዮች የሉም ቢኖሩማ ኖሮ እንዲህ ያሉ ሰዎች ፀጉርና ፂማቸው ተንጨባርሮ ያለ ቅጥ ያደገባቸው ሰዎች ባልኖሩ ነበር» ብለው ሲሄድ ሲል «እንዲህ አይደለም እኮ ፀጉር ቆራጮች አሉ ችግሩ ግን እነኛ ሰዎች ወደ ፀጉር ቤት አይመጡም» አላቸው በዚህ ግዜ *«እንዲህ ካልክማ እግዚአብሔር አለ ችግሩ ግን ሰዎች እግዚአብሔር በአጠገባቸው እንዳለ ልብ አይሉም፤ አስተውለውም ወደ እርሱ አይሄዱም ። እርሱንም አይፈልጉትም። ከዚህየ ተነሳ ስቃይና ሰቆቃ ዓለምን ሊያጠፋት ደርሷል። አባክህን እግዚአብሔርን በአንተ ልክ አትመልከተው፤ በዚህ ከዘለቅህ ፀጉርን ከመቁረጥ ያላለፈ ሕይወት በመኖር ላይ ነህና ባትፈጠር ይሻል ነበር»* አሉት ይባላል (**ዘመን ተሻጋሪ ተረቶች** 28-30)

ተግዳሮት በአገልጋይ ሕይወት ውስጥ ኑዋሪና ዘላቂ መሆኑን ከመነሻው እንመን ከሴጣን የሚመጣን ፈተና እንደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቃሉ ጋር በማገናዘብ እንቋቋመው።

ከአዳማዊ ተፈጥሮአችን የሚመጣውን ተግዳሮት ስጋ በመንፈስ ላይ ደጋግሞ እንዳያጠቃ መንፈስ በስጋ ላይ እንዲበረታ ለመንፈስ ቅዱስ ድምፅ ራሳችንን እናቅና።

በዓለም በውስጧ በመኖር ዓለማዊ ስርዓቷን የምንካፈል መሆናችንን በመገንዘብ በውስጡ ስንኖር ሁሉን አሜን ብለን መገዛት ተገቢ አለመሆኑን በማወቅ መዝለቅ መናፍቃዊ አስተሳሰብንም ለይተን በማውጣት መቋቋምን መለያችን እናርገው።

***

ይህን ሁሉ መቋቋም ያቃተው አንድ ሚሲዮናዊ «ጓደኞቼ የት ደርሰዋል እኔ ግን ለውጥ ለማያመጣ ኑሮ እየሰበኩ መኖሬ ሰለቸኝ» በማለት ሊኮበልል መወሰኑን ለሚተማመንባቸው ታዋቂ አገልጋይ ፃፈላቸው እሳቸው ግን «ስብከትህን ስለመተው ከቶውንም እንዳታስብ በእግዚአብሔር





ዙፋን ያሉት መላዕክት በዚህ ታላቅ አገልግሎት እየቀኑብህ መሆኑን አትዘንጋ» አሉት በዚህም ልቡ ተነካ የገጠመውን ተግዳሮቱን በጊዜው ተቋቋመ፤ በአገልግሎቱም በረታ። (**ዌርዝቢ** 2ቆሮንቶስ ማብራሪያ ገፅ 40 ላይ)

ተግዳሮትን መቋቋም ራስን ማወቅ መሆኑን አለመዘንጋት መሆኑን በድጋሚ ልብ እንበል በበርካታ የቻይና ግዛቶች ወንጌልን ያደረሱ የእምነት አርበኛ ጄ.ሃድሰን ቴይለር «የእግዚአብሔርን ስራ ያከናወኑ ሰዎች ሁሉ እርሱ ከእነርሱ ጋር እንዳለ በመተማመን ብቻ ታላላቅ ተግባራት የፈፀሙ ደካማ ሰዎች ናቸው» በማለት የእሳቸውንና የእርሱን ተገቢ ልክ ይገልፃሉ።(**ዌርዝቢ** 2ቆሮ ገፅ 43)

አገልጋዮች ደካማ ሰዎች ናቸው፤ ቢሆኑም ግን ብርቱው ከእነርሱ ጋር እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ አብሮ ይኖራል አሜን።

# ኢየሱስ ክርስቶስ

# ዳግም መጥቷል ወይስ ዳግም ይመጣል?

ኢየሱስ ክርስቶስ 33 አመታትን በምድር ላይ አሳልፏል፤ ከእነዚህ አመታት ውስጥ 3 ዓመት ከመንፈቁን ከልጅነት እና ከወጣትነት የሕይወት ዘይቤው በበለጠ በአገልግሎቱ ወደ ሕብረተሰቡ ዘልቆ ገብቷል፤ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ከተጠመቀ በኋላ «የእግዚአብሔር መንግስት መቅረቧን፤ እንዲሁም ሰዎች ለፍሬ የሚበቃ ሕይወትን ንስሀ በመግባት እንዲገልፁ አስተምሩዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡- ድውያንን ፈውሷል፤ ሙታንን አስነስቷል፤ በአጋንንት እስራት ውስጥ ያሉትን ነፃ አውጥቷል፤ ወንጌልም ለሰዎች ሰብኳል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ራሱ አሳውቋል፤ ስለሌሎች ማንነት ተናግሯል፤ ደቀ መዛሙርቱንም በአግባቡ አሰልጥኗል፤ ከዚያም የሞትን ሃይል አሸንፎ ራሱን ካስነሳ በኋላ ለአርባ ያህል ቀናት ከደቀ መዛሙርቱና ከሌሎች ሰዎችም ጋር ተገናኝቱዋል። በመጨረሻም ወደ እግዚአብሔር አብ ለመሄድ ሲዘጋጅ እና ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ብሎ ለማረግ ጊዜው ሲደርስ ሁለት ሐላፊነቶችን ለተከታዮቹ ሰጠ፤ አንደኛው በማቴ 28፡18-20 ላይ ሲገኝ ሌላኛው በሐዋ 1፡8 ላይ ሰፍሯል፤

*«...ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ ወደ አሉበት ቀርቦ እንዲህ አላቸው ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው እኔም እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ማለቱ እና «እነርሱም ተሰብስበው ሳሉ*





*ጌታ ሆይ የእስራኤልን መንግስት መልሰህ የምታቋቁምበት ጊዜው አሁን ነውን?» ብለው ጠየቁት እርሱም (ኢየሱስ) እንዲህ አላቸው አብ በገዛ ስልጣኑ የወሰነውን ጊዜ ወይም ወቅት ማወቁ ለእናንተ አልተሰጣችሁምነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌም በይሁዳና በሰማሪያ ሁሉ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ ካለ በኋላ እያዩት ወደ ላይ አረገ ደመናም ከዐይናቸው ሰወረችው።»*

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን መመሪያዎች ሰጥቶ በአካል ከተለየ ከ2000 ዓመታት በላይ ሆነ።

በእነዚህ 20 መቶዎች ውስጥ መሲሀይቷ ማህበረሰብ (ቤተክርስቲያን) በምድር ላይ በመሆን ተልዕኮዋን በመፈፀም ላይ ትገኛለች፤ ስለ ኢየሱስ መመስከር፣ ደቀመዛሙርት ማድረግ እና ሐላፊነትን ለተከታዩ ትውልድ በማስተላለፍ እና ፍሬያማ በመሆን በአለም ውስጥ ቤተክርስቲያን ህልው ሆና ስራዋን ታዘልቃለች።

ለ 2000 ዓመታትም በተለያዩ ጊዜዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ በአህጉር አቀፍ ደረጃ እንዲሁም የምስራቁን ዓለምን እና የምዕራቡን ዓለም በአማከለ ሁኔታ በየጊዜው የሚፈጠሩ አወያይ መንፈሳዊ ጉዳዮችን ቅዱሳን በጋራ በመሆን ተገቢውን ሁሉ እየፈፀሙ ኖረዋል።

ይህንንም አሰራር በሐዋሪያት ስራ ምዕራፍ 15 ላይ በተከናወነ የሥራ ምስክር ተረጋግጧል። ድነት በፀጋ፤ ወይስ ድነት ከሥራ የተነሳ? ለሚለው ውዝግብ ሐዋሪያትና ምዕመናኑ ተሰብስበው የእግዚአብሔር የሆነውን እምነት በጋራ በመፈለግ ወደ ትክክለኛ ማጠቃለያ ደርሰው ነበር።

ይህን ልከኛ ፈለግ፡- በቤሪያውያን ዘንድም ተገኝቷል። «የቤሪያ ሰዎች ከተሰሎንቄ ሰዎች ይልቅ አስተዋዮች ነበሩ ምክንያቱም ነገሩ እንደዚህ ይሆንን እያሉ መፃህፍት በየዕለቱ በመመርመር ቃሉን በታላቅ ጉጉት ተቀብለዋል» (17፡11) የሚል ሪፖርት በሐዋሪያት ሥራ ላይ አግኝተናል።

ይህ አካሄድ በ1ኛውና በ2ኛው ክፍለ ዘመን ከ200 አመታት በላይ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተግባራዊ ሆኖ ተገልፁዋል። ይልቁኑ በ4ኛው ክፍለ ዘመን የ325 ጉባኤ ከመድረሱ በፊት እና ሙሉ ሆኖ ወደ ውሳኔ እስኪደርስ ድረስ ለበርካታ አመታት በአንድ ወገን ኢየሱስ ፍፁም ሰው ብቻ ነው የሚሉ ሲሞግቱ በትይዩም ኢየሱስ አምላክ ነው የሚለው ተገዳዳሪ ሆኖ ፀንቶ ነበር። ይህ ኋላ ላይ ለበርካታ ቀናት ውይይት ተካሂዶ ጥናቱ ዘልቆ እምነታዊ በተጨማሪ አመክኖአዊ የሆኑ መረጃዎች ደርጅተው በኒቂያ ጉባኤ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም ሰው ፍፁም እምላክ (እግዚአብሔር) መሆኑ ፀና።

በ381 ዓ.ም አወዛጋቢው ርዕሰ ጉዳይ የክርስቶስ ቤተ ክርስትያንን አተያየ፤ መንፈስ ቅዱስን

በተመለከተ በአንድ ወገን «ሀይል፣ ጉልበት፤ ሆኖ መግለፁ የመለኮትነት መገለጫ ምንም የለው» የሚለው አንዱ ሲሆን በሌላው አቅጣጫ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር መሆኑን ለማረጋገጥ በጉባኤ መከሩ። ይህም በፍፃሜው በቆስጠንጢኖስ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር መሆኑን አፀደቀ። በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ላይ ይህ ብቻ አልነበረም የሚዘከረው በ431 ዓ.ም ድኅትን በተመለከተ ሀጢአት በሰው ላይ ያደረሰው አሉታዊ ተፅዕኖ ሙሉ ጉዳትን ወይስ ከፊል በሚለው ውዝግብ ላይ ጉባኤው «የሰው ልጅ ሁሉ በኃጢአት ደንካራ ነው፤ በራሱ ለመዳን ምንም አቅም የለውም። ከዚህም የተነሳ የጌታ እገዛ ያስፈልገዋል» የሚል ውሳኔ በኤፌሶን ተወሰነ።

እናም እነዚህንና የመሳሰሉ ርዕሰ ጉዳዮች በየዘመኑ ተነስተዋል።

መነሳታቸው ደግሞ ተገቢ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን ፍፁማንን በመያዝ አገልግሎቷን የምትመራ ባለመሆኑና ቤተ ክርስቲያን አንድ ወጥ ማህበረሰብን ብቻ ለይታ የምታገለግል አለመሆኗ፤ ይልቅስ ሁሉንም ያለ ልዩነት ሰብስባ የምታስተዳድር፣ እንዲሁም ምዕመኗ በእግዚአብሔር አምሳል ከመፈጠራቸው የተነሳ ሁል ጊዜ ያስባሉ፤ ያመዛዝናሉ፤ ልኩን ለማወቅም ይጓጓሉ። ይህ እውን በሆነበት «ማህበር» አነጋጋሪ ነጥብ ይኖራል፤ ኖሯልም።

ለዚህም ሁነኛው መፍትሄ መመካከር፣ መወያየት፣ መፅሐፍ ቅዱስን ዋቢ አድርጎ በመምከር ወደ ማጠቃለያ መድረስ ነው።

ዛሬ ላይ ቆምን የመመካሪያ ርዕሰ ጉዳይ ቢመጣ ከዚህ በፊት ከነበሩት የመሲሐይቷ ማህበረሰብ አባላት በበለጠ እና በተሻለ ሁኔታ የሚያግባባ እና ወደ ልከኛው ማጠቃለያ የሚያደርሱ መረጃዎች ስላሉ ከምንም ጊዜ በበለጠ ጭብጦችን በአግባቡ ማየት ይቻላል።

***

«የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ ከኢየሩሳሌም መደምሰስ እና ከቤተመቅደሱ መውደም ላይ ያተኩራል» ይህ የ70 ዓ.ም አተያይ ሲሆን በትይዩ «በትንቢት የተነገሩ ያልተፈፀሙ ተስፋዎችን (ቃሎችን) መሰረት በማድረግ «ስነ መስተዳደሪያው» አካሄድን ተመርኩዞ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም የመመለሱ ሁነት ወደ ፊት ሊመጣ እንደሚችል» የሚያምነውን ትምህርት በማንሳት የቱ ለቅዱሳን መፅሐፍት ቅርብ ነው? በማለት እንናበባለን።

ዛሬ ይህ ተነሺ ነጥብ አድጎ ደርጅቶ ቀዳሚውን ሰባውያን (ፕሪተሪስት/Preterist) ተያይውን መርሐግብራዊ (ዲስፔንሴሽናል/Dispensetional) ተብለው የየራሳቸውን እምነት በስነ ፍፃሜ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ያነሳሉ፤ ይመክራሉ፤ ያስተምራሉ። እነዚህ ሁለት ዘርፎች ብቻ ሳይሆኑ





ሌሎችም ጥቂት፣ ጥቂት ለየት ያሉ የስነ ፍፃሜ ትምህርቶች መኖራቸው አይዘነጋም።

ዛሬ ስለ ክርስቶስ የዳግም መመለስን የመለያ ጊዜ በቅጡ ለማየት ታሪክ (**<u>የጥንትና የመካከለኛ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u>** ገፅ241-242) እንዳጣቆመው ማንም ምንም ዐይነት ርዕሰ ጉዳይን አንድም በተፃፉ ሰነዶች በመጠቀም አንድም ባልተፃፉ ሰነዶች ላይ በማተኮር ወደ ልኩ መቅረብ ይቻላል።

**የተፃፉ ሰነዶች:-**

ሀ. ለየቤተክርስቲያን የሚጠቅሙ ሆነው በመሪ አገልጋዮች የተፃፉ (መጽሐፍ ቅዱስን ያካትታል)፣ የጉባኤ ውሳኔዎች፤ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ የተፃፉትን በማጤን፤

ለ. ግለ ፀሐፎች የቤተ ክርስቲያን አባቶች ግላዊ ሰነዶች፣ የመናፍቃን ዘገባዎች፣ ዜና መዋዕሎች (ልክ ነን ልክ አይደለንም) በመባባል የተፃፉ ሰነዶች ማጤን

ሐ. የስነ ቁፋሮ ውጤቶችን በመመርመር በየዋሻው ላይ የተገኙ ፍንጮችን እንደ ካታኮምቦ በመሰሉ መረጃዎች ላይ በማተኮር (በግብፃውያን፤ በባቢሎናውያን በሮማውያንና በግሪካውያን በኢየሩሳሌም የሚገኙ ውጤቶች በመመርመር እንዲሁም በትይዩ ባልተፃፉም ሰነዶች ስር ቅርፃቅርፆች፣ ስዕላ ስዕሎች ባህላዊ ገላጭ ትውፊቶችን በምንጭነት በመጠቀም በክርስቶስ ዳግም መምጣት ላይ ወገኖች እንዴት እና ምን ብለዋል ብለን መመርመር እንችላለን።

***

ይህ ጥናት ኢየሱስ በአካል ሳይሆን በመንፈሳዊ ማንነት በ70 ዓ.ም እንደተናገረው ተመልሷል የሚለውን ሰፊ ጥናት ከኢየሱስ እመጣለሁ ያለበት ቃል እስከ አሁን ስላልተፈፀመ ዳግም በአካል መመለሱን እንጠብቃለን ለሚለው እምነት በቀዳሚነትና በዋናነት ቅዱሳት መፅሐፍትን በመረጃነት ቅድሚያ ይሰጣል።

ይህን ደግሞ ከግብ ማድረስ የሚቻለው በጋራ ስምምነት **ታቃስ** ን ቀዳሚ ማድረግ ሲቻል ነው።

**ታ-** ታሪካዊ ዳራን በአግባቡ በማጥናት መልዕክቱ በተነገረበት ወይም በተፃፈበት ጊዜ የነበሩ ተደራሲያን እንዴት ሊረዱት ይችላሉ፤ ከዚያ በመነሳት እኛስ የምናገኘው ጥቅም ምንድን ነውን ይመረምራል።

**ቃ-** *ቃሉ ቃሉን እንዲፈታው እንዲያብራራው አውዳዊ ይዘትን በቀዳሚነት በመያዝ፣ በሀረግ፣በ ዐረፍተ ነገር፣ በአንቀፅ፣ በምዕራፍ፣ በመፅሐፍ፣ በመፅሐፍት፣ በኪዳናት እያያያዙ የማጥናት እና የመወሰን ዝግጅት ነው።*

**ስ-** ስርዓተ ቋንቋ፤- መልዕክቱ በቋንቋው አማካኝነት ነው ወደ ግብብነት የሚደርሰው፤ ይህን ለመገንዘብ በወቅቱ የሚጠቀሙበት መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጎመበትን ቋንቋ ሕገደንብ ማወቅ። ለምሳሌ:- የአማርኛን ህገ ደንብ በትክክል ማወቅ በዚያም አቅጣጫ ለመረዳት ቅድሚያ መስጠትን ይመለከታል።

ከዚህም የተነሳ ይህ ዝግጅት ይህን የታቃስ ስልት በቀዳሚነት ይከተላል።

ይህን በታማኝነት መፈፀም ወይም/ማከናወን ጥቅም አለው:-

ሀ. ኢየሱስ ክርስቶስን አብልጠን እናውቀው ዘንድ እንዲሁም እንወደው ዘንድ የማድረግ አቅምን ያመጣል። *«መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉንም ነገር ይመረምራል... የጌታን ልብ ማን አወቀው... እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን» (1ቆሮ 2:15-16)«ክርስቶስንና የትንሳኤውን ኃይል እንዳውቅ በስቃዩ ተካፋይ እንድሆንና በሞቱም እርሱን እንድመስል እመኛለሁ ለሙታን ትንሳኤም እንድደርስ እናፍቃለሁ»* (ፊሊ 3:10-11)

ለ. የእግዚአብሔርን ዕቅድ ከትናንት ዛሬ በበለጠ እንድንረዳ በማድረግ የነጠረ እውነት ፈላጊዎችን ያስገርማል፤ በውጤቱም በእርሱ ላይ ብቻ እንድንደገፍ አቅም ይሰጠናል። «በአንተ ላይ ታምናለችና በአንተ የምትደገፈውን ነፍስ ፈፅመህ በሰላም ትጠብቃታለህ» (ኢሳ 26:3) *«እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ ሀሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሰራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን»* (ሮሜ 8:28)

ሐ. የአእምሮ ሰላምንና መረጋጋትን እንዲሁም በቅድስና የመኖር አቅምን ይፈጥራል *«የሚጠራጠር ሰው በነፋስ እንደሚገፋና እንደሚናወጥ የባህር ማዕበል ነው ያ ሰው ከጌታ አንዳች ነገር አገኛለሁ ብሎ አያስብ እርሱ በሁለት አሳብ የተያዘና በመንገዱ ሁሉ የሚወላውል ነውና»* (ያዕ 1:7-8)

መ. የፀጋን ምንነት፣ የእግዚአብሔር የሆነውን ፈቃድ መረዳት፤ የሴጣንን ክፉ ሀሳብ ላለመሳት ይረዳል። *«መልካም፤ደስ የሚያሰኝና ፍፁም የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን አለም አትምሰሉ»* (ሮሜ 12:2) *«... እባብ በተንኮል ሔዋንን እንዳሳታት ምናልባት የእናንተም ልቡና ተበላሽቶ ለክርስቶስ ካላችሁ ቅንነትና ንፅህና እንዳትወሰዱ እሰጋለሁ»* (2ቆሮ 11:3)





እነዚህን ሁሉ ጥቅሞች በዚህ ዝግጅት ውስጥ ማግኘት እንችላለን፤ እነርሱን ደግሞ ለማግኘት ተከታዩን ቢጋር አደረጃለሁ:-

ምዕራፍ 1. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ እርግጠኝነት፤

ምዕራፍ 2. ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም የሚመለሰው መቼ ነው?

ምዕራፍ 3. የሰባውያንና የስነመስተዳደሪያውያን እምነት :- በዳግም መመለሱ ላይ፤

ምዕራፍ 4. ለታቃስ ስልትና ለቤተክርስቲያን ታሪክ ተገዢ የሆነው ግንዛቤ፤

ምዕራፍ 5. ድምዳሜ/ማጠቃለያ፤

የተዘረዘሩትን አምስት ምዕራፎች በቅደም ተከተል ላመላከት:-

# ምዕራፍ አንድ

# የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ እርግጠኝነት

ለዚህ ምላሽ ቀዳሚ ምንጭ አድርጌ የምጠቀመው ቅዱሳት መጽሐፍትን ነው። በዚህ አካሄድ ውስጥ ከ66ቱቅዱሳን መጽሐፍት ወጣ ያለውን አቋምና እምነት ይዘው በምስራቅ እና በምዕራብ ቤተ ክርስቲያናት ባሉአዋልዶች ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስን ጠቋሚ ገለፃዎች ከተገኙ ለዚህ ዝግጅቱ እንደ ማዳበሪያ ያገለግላሉ።

በመሰረቱ ከመነሻው እርግጠኛ የምንሆንበት አንድ እውነት አለ፤ እሱም የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መፅሐፍት መሲሁ እንደሚመጣ የተናገሩ መሆናቸው ነው፤መፅሐፍቱ አወላለዱን፣ አስተዳደጉን፣ ሞቱንና ዋጅነቱን ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው ተናገሩ፤ ልክ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ድንግል ከነበረችው ከማሪያም በመወለድ ወደዚህ ዓለም መጣ:- ይህ የመጀመሪያው አመጣጡ ነው፤ ለብዙ ሺህ ዓመታት ሲጠበቅ የነበረው ኢየሱስ «ጊዜው በደረሰ ጊዜ ከሴት ተወለደ» (ገላ 4:4) ይህ እርግጥ ሆኖ እንዳገኘነው አሁን ደግሞ እሱ ራሱ ሁለተኛ ወደዚህ ዓለም በሚመለስበት ጉዳይ ላይ ናሙናዊ መረጃዎችን ለግብብነት ይቀርባል።

ለዚህም ኢሳ 46:11 አጋዥ ነው፤- *«... የተናገርኩትን አደርጋለሁ፤ ያቀድሁትን እፈፅማለሁ»* ይህ እግዚአብሔር በግለሰቦች፣ በሕዝቦች ፈቃድና ምኞት የሚመራ ሳይሆን እሱ ለራሱ ታማኝ በመሆን ከአፉ የወጣውን ቃል ከመፈፀም ወደ ኋላ የማይል፤ እንዲሁም ያቀደውን በሙሉ በራሱ መርሐግብር ከፍፃሜ የሚያደርስ መሆኑን ያረጋግጣል።

ሀርቦርት ሉከሪ/Herbort Lockyer/ All the messianic Prophecies of the Bible በሚለው መፅሐፉ፡- የሥላሴ ቃል በቁሙ በቅዱሳት መፅሐፍት ውስጥ ባይገኝም «እውነቱ» ግን በድግግም አለ፤ ልክ እንዲሁ የመሲሁ ቀዳሚ መምጣቱ ብቻ ሳይሆን ዳግም የመመለሱ ገለፃም እርግጡን አመላካች በሆነ ይዞታ ተተንትኗል። ለዚህም እንደ ሁነኛ ምሳሌ በዕብ 9፡28

*«... ክርስቶስ የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ለመሸከም እንዲሁም አንድ ጊዜ መስዋዕት ሆኖአል። ሁለተኛ ጊዜም ይገለጣል፤ ይህም ለሚጠብቁት ድነትን ለማምጣት እንጂ ሀጢአትን ለመሸከም አይደለም»* ይላል።

ይህን አገላለፅ መነሻ አድርገን ወደ ላይ መለስ ስንል 9፡26 «... በዘመናት መጨረሻ ራሱን መስዋዕት በማድረግ ኃጢአትን በማስወገድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተገልጧል» ይላል ይህ ያለቀለት ታሪክ ሆኖ ወደ ኋላ እንድንመለከት ያደርገናል።

9፡24 *«ክርስቶስ... አሁን ስለ እኛ በእግዚአብሔር ፊት ለመታየት ወደ... ሰማይ ገባ»* (አሁንም በስራ ላይ መሆኑን ያረጋግጣል)

9፡28 *«... ለሚጠባበቁት... ለሁለተኛ ጊዜ ይገለጣል»* (ወደ ፊት የሚሆነውን ያጣቁማል)

ብዙ የቅዱሳን መፅሐፍት አገላለፆች በኢየሱስ ዳግም መምጣት ላይ ይህን የመሰሉ ተያያዥ አባባሎችን ይዘው ይገኛሉ፤ በተለይም በአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ318 ያህል ክፍሎች በ27ቱቅዱሳን መጽሐፍት በመገኘት የኢየሱስን ሁለተኛ መመለስ አመላካች እና አረጋጋጭ ሆነው ተፅፈዋል፤ ቁጥሩን ለመፅሐፍቱ ይካፈሉት ቢባል በየመጽሐፉ 25 ያህል ጊዜ ስለ ኢየሱስ ዳግም መምጣት ተጠቁሟል ማለት ነው፤ ከእነህ ውስጥ

ማቴ 24፡39 *«እስከዚያ ጊዜ ድረስ ምን እንደሚመጣ ሳያውቁ ድንገት የጥፋት ውሃ እንዳጥለቀለቃቸው የሰው ልጅ ሲመጣም እንደዚሁ ይሆናል... 42 እንግዲህ ጌታችሁ የሚመጣበት ቀን ስለማይታወቅ ነቅታችሁ ጠብቁ... 44 የሰው ልጅም ባላሰባችሁት ሰዓት ይመጣልና እናንተም እንዲሁ ዝግጁ ሁኑ...»*

25፡14-30 *የእግዚአብሔር መንግስት አገልጋዮቹን ጠርቶ ያለውን ንብረት በአደራ በመስጠት ወደ ሌላ አገር ለመሄድ የተነሳ አንድን ሰውን ትመስላለች... 19 የአገልጋዮቹም ጌታ ከብዙ ጊዜ በኋላ ከሄደበት ተመልሶ የሰጣቸውን ገንዘብ ተሳሰበ... (ይህ ከማር.13፡34-37ጋር ይገጣጠማል)...ስለዚህ ጊዜው መቼ*





*እንደሚሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ ትጉ ፀልዩም* (ቁ.33)

ፊሊጵ. 3፡20-21 *እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን እርሱም ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ኃይል ከቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ስጋችንን ይለውጣል።*

1ተሰ. 4፡13-18 *«ወንድሞች ሆይ አንቀላፍተው ላሉት ሰዎች ሳታውቁ እንድትቀሩ አንፈልግም ደግሞም ተስፋ እንደሌላቸው እንደሌሎቹ ሰዎች እንድታዝኑ አንሻም 14 ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሳ ካመንን በኢየሱስ ሆነው ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደዚሁ ያመጣቸዋል 15 በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነው እኛ በሕይወት ያለንና ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉትን አንቀድምም...»*

1ዮሐ 3፡2 *...ወደፊት ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም፤ እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለንና እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን...*

ሐዋ 17፡31 *«... በመረጠው ሰው አማካኝነት በዓለም ላይ በፅድቅ የሚፈርድበትን ቀን ወስኗልና እርሱንም ከሙታን በማስነሳቱ ለሰዎች ሁሉ ይህን አረጋግጧል።*

ሐዋ 1፡11 *«...እናንተ የገላቲያ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ እዚህ የቆማችሁት ለምንድነው? ይህ ከእናንተ ዘንድ ወደ ሰማይ ሲያርግ ያያችሁት ኢየሱስ ልክ ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት በዚሁ ሁኔታ ይመለሳል።*

ዮሐ. 14፡3 *ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ።*

ያዕ 5፡7 *እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሱ...8 የጌታም መምጣት ቀርቧል።*

ይሁዳ 14-15 *ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ ስለ እነዚህ ሰዎች እንዲህ ሲል ተንብዮአል፡- እነሆ ጌታ ከእልፍ አእላፍ ቅዱሳኑ ጋር ይመጣል ይህም በሰው ሁሉ ላይ ለመፍረድ እንዲሁም ዐመፀኞችን ሁሉ በከፋት መንገድ በሰሩት የዐመፅ ሥራና በከፋት በእርሱ ላይ ስለተናገሩት የስድብ ቃል ሁሉ አጥፊነታቸውን ይፋ ለማድረግ ነው*

*ቲቶ 2፡13 ...የተባረከ ተስፋችን የሆነውን የታላቁን የአምላካችንንና የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ በመጠባበቅ ነው...*

እንግዲህ እነዚህን የመሰሉ ተያያዥ የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም መመለስ የሚያበስሩ ክፍሎች እንዳሉን ልብ እንበል።

ከብሉይ ኪዳን ሊጠቀሱ ያላቸው በዋናናት ተከታየቹ ቢሆኑ ይመረጣሉ። እነርሱም ቢሆኑ ግን፣ አሻሚነት፤ ድርብ ትርጉም እና ለትርጓሜ የአለመመቻቸት ችግር ሊኖራቸው ስለሚችል መጠቀሳቸው ብቻ በዋቢነት እንደመጨረሻ ማረጋገጫ ተደርጎ አይወሰድ። በናሙናነት ኢሳ 25፡8፤ 26፡21፣ዳን. 12፡1-3፣ኤር.23፡5፣ ኢዮኤል 1፡15 እና 3፡14-17 ሚክያስ 5፡2-4፣ዘካ. 14፡5-9 ተጠቃሾች ናቸው።

ከአዲስ ኪዳን 12 የናሙና ጥቅሶችን መውሰዴ ስለ ዳግም መመለሱ አመላካችና በቂ ናቸው የሚል እምነት አለኝ።

*ዳሩ ግን ዳግም መምጣቱንና ለመምጣቱ እንደ በቂ ሁኔታ ሊጠቀሱ የሚገባቸው ወይም* በዘመኑ ላይ ልዩነት ሊፈጥር የሚችል ምክንያት አብሮ ተያይዞ መነሳቱን በተያያዥነት ካልተጠቀሰ፡ - እርባናው መጠነኛ ብቻ ይሆናል። ከዚህም የተነሳ ዳግም ለመመለሱ ወይም በመመለሱ አብረው ሊገለጡ ወይም ሊሆኑ የሚገባቸውን ላመላከት፡-

**አንደኛው፡-** የተጀመሩ ስራዎች መጠናቀቅ አለባቸው አልፋው ኦሜጋም መሆኑን መግለፅ። ይህም ከዳግም መምጣቱ ጋር ይያያዛል በዕብ 12፡2 *«የእምነታችን ጀማሪና ፍፃም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመልከት እርሱ በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን ታግሶ የመስቀሉንም ውርደት ንቆ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጧል...»* ይላል ከዚያም በቁጥር 28 ላይ *«ስለዚህ ከቶ የማይናወጥ መንግስት ስለምንቀበል እግዚአብሔርን እናመስግን ደግሞም ደስ በሚያሰኘው መንገድ በአክብሮትና በፍርሀት እናምልከው አምላካችን የሚያጠፋ እሳት ነውና»* ይላል፤ ታሪክ መደምደሚያ ይኖረው ዘንድ መመለሱ አስፈላጊ ነው።

**ሁለተኛው፡-** በውድቀት ላለው ፍጥረት የተገባው ተስፋ ፍፃሜ ያገኝ ዘንድ መመለሱ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ሮሜ 8፡18-23 *«የአሁኑ ዘመን ሥቃያችን ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር ሲነፃፀር ምንም እንዳይደለ እቆጥራለሁ፤ ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ በናፍቆት ይጠባበቃል፤...እስከ አሁን ድረስ ፍጥረት ሁሉ በምጥ ጊዜ እንዳለው ስቃይ በመቃተት ላይ እንደሚገኝ እናውቃለን»* ይላል። ይህ ዳግም





በመመለሱ መቀየር አለበት።

**ሦስተኛው፡-** ለሞት ድንበር ማበጀት ወይም ማብቂያ ማምጣት ያስፈልጋል ራዕ. 2፡4 *«ከእንግዲህ ወዲህ ሞት ወይም ሀዘን...አይኖርም የቀደመው ስርዐት አልፎአልና»* 1ቆሮ 15፡54 *«...የሚሞተው የማይሞተውን በሚለብስበት ጊዜ ሞት በድል ተዋጠ የተባለው ቃል ይፈፀማል»* 2ጢሞ 1፡10 *«አሁን ግን ሞትን በወንጌል አማካኝነት ሕይወትንና ኢመዋቲነትን ወደ ብርሀን ባወጣው በመድሀኒታችን በክርስቶስ ኢየሱስ መምጣት ተገልጧል። እኔም ለዚህ ወንጌል የምስራች ነጋሪና ሐዋሪያ አስተማሪም ሆኜ ተሾምሁ... የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያች ቀን ድረስ መጠበቅ እንደሚችል ተረድቻለሁ።»* ይላል።

**አራተኛው፡-** የሴጣንን ሽንፈት ድንበር ሊበጅለት ይገባል፤ ይህም ከኢየሱስ መመለስ ጋር ይተሳሰራል፤ ዕብ 2፡14 *«...በሞት ላይ ኃይል ያለውን ዲያብሎስን በሞቱ ኃይል እንዲደመስስ ነው...»* ይላል።

1ዮሐ. 3፡8 *«ኃጢያትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው ምክንያቱም ዲያብሎስ ከመጀመሪያው አንስቶ ሀጢአትን የሚያደርግ ነው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የተገለጠው የዲያብሎስን ስራ ያፈርስ ዘንድ ነው»*

*ራዕ 20፡10 «ያሳታቸው ዲያብሎስም አውሬውና ሀሰተኛው ነብይ ወዳሉበት ወደ እሳትና ዲኑ ባህር ተጣለ...»* ይላል።

**አምስተኛው፡-** በገዛ ሕዝቡና በዓለም ሁሉ ላይ የሚፈርድበት ጊዜ ሊመጣ ይገባዋል። ዮሐ.5፡22 *«አብ በማንም ላይ አይፈርድም ነገር ግን ፍርድን ሁሉ ለወልድ አሳልፎ ሰጥቶአል»*

ዮሐ. 12፡48 *«በማይቀበለኝና ቃሌን በሚያቃልል ላይ የሚፈርድበት አለ፤ የተናገርሁት ቃል ራሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል።»*

1ቆሮ 4፡5 *«ስለዚህ ጊዜው ሳይደርስ በምንም ነገር አትፍረዱ ጌታ እስኪመጣ ጠብቁ...»* ይላል።

**ስድስተኛው፡-** ለንስሀ የሚበቃው የመጨረሻ ሰው በጌታ ሆኖ እንዲገኝ ዳግም መመለሱ አብሮ ይያያዛል። 2ጴጥ 3፡8-9 *«ወዳጆች ሆይ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ አመት ሺህ አመትም እንደ አንድ ቀን መሆኑን ይህን አንድ ነገር አትርሱ፤ አንዳንድ ሰዎች የዘገየ እንደሚመስላቸው ጌታ የተስፋ ቃሉን ለመፈፀም አይዘገይም፤ ነገር ግን ማንም እንዳይጠፋ*

*ፈልጎ ሁሉ ለንስሀ እንዲበቃ ስለ እናንተ ይታገሳል...»* እነዚህ ስድስት ያህል ምክንያቶች *«መቼም»* ጌታ ይምጣ እንደ ቃሉ ግን ግብ ሆነው ከግምት ውስጥ ይገባሉ።

## ምዕራፍ ሁለት

## ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም የሚመለሰው መቼ ነው?

ጥያቄው ጊዜን አመላካች ስለሆነ ይህን በተመለከተ ሊኖረን የሚገባው ምላሽ በርካታ ሊሆን ይችላል። በእግዚአብሔር ቃል ላይ ብቻ አትኩሮ እንዲመለስ ሲወሰን ደግሞ አንድም፡- ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ጉዳይ ላይ በቅርብ መሆኑን መናገሩ፣ ጊዜውን በምልከቶቹ ለመረዳት መምከሩ እንዲሁም በየጊዜው የተነሱ ፀሐፊዎችና ቃሉን የሚያጠኑ ተመራማሪዎች ጊዜውን በተመለከተ የተለያየ ምላሽ መስጠታቸው ጭብጡን አነጋጋሪ አድርጎታል።እንኪያስ መቼ ነው የሚመጣው? ለሚለው ጥያቄ ለየቅሉ የቆመ መልስን የመጽሐፍ ቅዱሱ ጥናት አቀብሏል፤ ከእነርሱ ውስጥ ጥቂቱን እናነሳሳ፡- ለምሳሌ

ገላ 4፡4 «የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር... ልጁን ላከ»

ሐዋ 2፡1 «በዐለ ሃምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ...»

እንደመንደርደሪያ የተነሱት እነዚህ ሁለት ክፍሎች የሚያስተላልፉት ጉዳይ ሁለት የተለያየ ጭብጥን ነው፡-

**አንደኛው** የኢየሱስ ከማሪያም መወለድን ይህንንም እግዚአብሔር አብ ማድረጉን **ሁለተኛው** ኢየሱስ ካረገ በኋላ እንደ ተስፋ ቃሉ መሰረት የመንፈስ ቅዱስ የአሰራር ለውጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ መከናወኑን ገላጮች ናቸው።

ሁለቱም፡- **«በደረሰጊዜ»** የሚል የቁርጠኛ ቀን መምጣትን፣ የተወሰነ ጊዜ መኖሩን፡- እግዚአብሔር በአቀደው መሰረት ሁሉ ነገር መከወኑን አረጋጋጭ ሐረግ ነው።

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የዳግም መመለስ የመቼ ጥያቄ ምላሹ ሰው ስለተመኘ፣ ስለተጠባበቀ፣ በፆም በፀሎት ስለተጋ፣ ስለአመፀና፣ እግዚአብሔርን ስላስቆጣ የሚሆን ነገር ሳይሆን እሱ ልዑልነቱን የገለፀበትን ማንነት በወሰነው ቢጋሩ የሚከውን መሆኑን ያረጋግጣል።

ልክ እንዲሁ ተፈላጊው ገላጭ ሐረግ **«በመጨረሻው ቀን፣** ወይም **ዘመን»** የሚሉ ገላጮችን





መጽሐፍ ቅዱስ መያዙ ነው፤ ይህን አባባል ሁልጊዜ፡- በየቆምንበት ዘመን ላይ እየተገኘን ከፊታችን ሊመጣ ያለውን ጊዜ በማየት የመጨረሻው ዘመን ደርሷል ወይም ቀርቧል እንላለን። እንዲሁም እንደአግባቡ የመጨረሻው ጊዜን ከከንውኑ በመረዳት ይህ የተከናወነ ስራ መገለጫ ነው እንላለን።

በምሳሌነት የዮሐንስ ወንጌል አምስት ጊዜ ያህል «በመጨረሻው ቀን... አስነሳዋለሁ» ይላል ዮሐንስ 6፡39,40,44,54 እንዲሁም 11፡24 ይህ ተገልፃል፤ በማያሻማ ሁኔታ እነዚህን ከመፃኢ ጊዜ ጋር እንድናስብ እንገደዳለን።

የሐዋ 2፡16-17 አንስተን ስናጤን ደግሞ «ይህ በነብዩ በኢዮኤል የተባለው ነው እግዚአብሔር ይላል «በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል ሥጋ በለበሰ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ...» ይህ ገለፃ ያ የመጨረሻ ቀን ወደ ኋላ በማየት በዓለህምሳን በመጨረሻ ቀን መገለጫነት እንረዳዋለን።

ከዚህም ተነሳ፡- በኋለኞች ዘመናት፣ ወይም በመጨረሻው ቀን የሚሉ ገለፃዎችን እንደመጣልን በመወሰን ከዚህ ንቅንቅ አንልም ማለት አይቻልም፤ በብሉይ ኪዳን በስፋት የተገለፁ የመጨረሻ ቀናት መገለጫዎች ከሕዝበ እስራኤል ቅጣት ጋር ተከናውነዋል። ከዚያ ውጭ ያሉ ደግሞ ትንቢታዊ ሆነው በጥበቃ ስር ይሆናሉ።

*መነሻችን «መቼ»ን ለመመለስ የጀመረ ነው፤ ይህን መጠየቅ ነውር አለመሆኑን ያስተማሩን* የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ሲሆኑ ሌላኛው የየገዛ አእምሮአችን በገዛ ፈቃዱ ለሚጠይቀው ጥያቄ ምላሽን መፈለጉ ነው።

በማቴ 24፡3 ላይ *«እርሱም በደብረዘይት ተቀምጦ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው ንገረን ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድን ነው? ብለው ጠየቁት ኢየሱስ ለዚህ ጥያቄ የሰጠው መልስ የአህዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግስት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል። በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል»* አለ (ማቴ 24፡14)

በሌላ ጊዜም ሐዋ 1፡6,7,8 እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ *«ጌታ ሆይ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግስትን ትመልሳለህን?» በማለት ጠየቁት የእርሱም ምላሽ «አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ ሁሉ በሰማሪያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ»* አላቸው። በኢየሱስ ምላሽ ውስጥ በርካታ መሰረታዊ ጭብጦች አሉ። የእነርሱን ትንታኔ በሌሎቹ ተከታታይ ምዕራፎች ይነሳሉ።

ታዲያ የመቼን ጥያቄ ምላሽ ለመስጠትከሞከሩ ትንታኔዎች ውስጥ፡-

➢ኢየሱስ በበዓለ ሀምሳ ዕለት ተመልሶ መጥቷል፤

➢ኢየሱስ ቤተ መቅደሱ በሚደመሰስበት ወቅት ተመልሶ መጥቷል፤

➢ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣበትን ማንም ማወቅ ስለማይችል በአስተምህሮው መነጋገር ትርጉም የለውም፤

➢ኢየሱስ ዳግም በመመለሱ ላይ እርግጠኛ ብንሆንም የጋራ አቋም መያዝ ግን አይቻልም። የሚሉ ምላሾች ባለፉት 2000 አመታት ተነስተዋል፤ ተነግረዋል፣ ተሰብከዋል።

ይህ ጥናት ፍሬያማ እንዲሆን ግን «መቼ» ለሚለው ጥያቄ የተሰጡ ምልከታዎችን ለመጓጓዣነት እንዲጠቅመን፣ ለዕውቀትም እንዲያግዘን እነሳሳቸዋለሁ።

## <u>የኢየሱስ ዳግም መምጣትን በሚመለከት የተሰነዘሩ አመለካከቶች</u> :-

ሀ. በዚያኑ ዘመን የተፈፀመ (In that History) ገለፃዎቹና ትንቢቱ በተነገረበት ቅርብ ዘመን ውስጥ የሚፈፀሙ ስለነበሩ በአንደኛው የክፍለ ዘመን ከልል ፍፃሜ አግኝቷል። የዮሐንስ ራዕይም ገለፃ ዮሐንስ የነበረበትን ጊዜ ብቻ የሚያመለክት ነው።

ለ. የቤተክርስቲያን የመነሻ መድረሻ (All of History) ታሪክ ሲደመደም እና ይህ ሁሉ ሲጠናቀቅ ኢየሱስ ይመለሳል ይላል። ለዚህም የዮሐንስ ራዕይን ዮሐንስ ከኖረበት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በኢየሱስ መምጣት እስከሚጠቀለልበት ያለውን ጊዜ በ7 ክፍሎ ይመድባል። ለዚህም ራዕ 2-3 ላይ ያለውን ገለፃ እንደሚከተለው ያደረጃል።

➢ኤፌሶን ሐዋሪያዊት ቤተክርስቲያን ከ(30-100 ዓ.ም)

➢ሰምርኔስ ስደተኛይቱ ቤተክርስቲያን ከ(100-313 ዓ.ም)

➢ጴርጋሞን ፖለቲከኛይቱ ቤተክርስቲያን ከ(313-590 ዓ.ም)

➢ትያጥሮን ጳጳሳዊት ቤተክርስቲያን ከ(590-1517 ዓ.ም)

➢ሰርዴስ የተሀድሶዋ ቤተክርስቲያን ከ(1517-1730 ዓ.ም)

➢ፊላድልፍያ ወንጌላዊቷ ቤተ ክርስቲያን ከ1730-1900 ዓ.ም)





➢ሎዶቅያ ከዳተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ከ(1900-ዳግም ምፅዐቱ)

ከዚህም የተነሳ ይህ 21ኛ ክፍለ ዘመን ለኢየሱስ ዳግም መመለስ የቅርብ ቅርብ መሆኑን ያመለክታል በማለት ይተረጉማሉ።

ሐ. ከታሪክም ያለፈ Above History (ከታሪክም በላይ) ኢየሱስ መቼ ይመጣል? ለሚለው ጥያቄ ለምልከት የሚያገለግል በቂ ምንም ነገር የለም፤ ይልቅስ ዳንኤልም ሆነ ማቴዎስ፣ሕዝቅኤልም ሆነ ራዕይ ዮሐንስ የሰጧቸው መግለጫዎች ቅኔያዊ አገላለፆች ስለሆኑ እግዚአብሔር ሕዝቡ ሀሳቡን ይረዳ ዘንድ ያቀረበበት ተውኔታዊ (ድራማዊ) ገለፃ ነው፤ እግዚአብሔር ከሴጣን ጋር ያለውን ትግል በመግለፅ አሸናፊነቱን ያሳየበት ገለፃ ብቻ ስለሆነ:- ዳግም የመመለሱን የውሳኔ ቃል በእነዚህ ውስጥ በቁርጠኝነት መፈለግና መወሰን ያስቸግራል የሚል መልስን ይዘዋል።

እነዚህ እንደተጠበቁ ሆነው ተከታይ ብዙ እንዳላቸው የሚታመኑ የሺህ ዓመት መንግስት ተንታኞች ኢየሱስ መቼ ዳግም ሊመለስ እንደሚችል አሳውቀዋል፤ አገላለፃቸው ጥቂት ጥቂት ልዩነት ስላለው አሁንም ዋንኞቻቸውን በማስተዋወቅ ልወሰን:- በመሰረቱ ራዕ. 20 ስለሺህ ዓመት ይናገራል። እናም ለሺህ ዓመት መነሻችንም መድረሻችንም ይህ ክፍል ነው፤ ከዚያ በመንደርደር:-

1. ኢየሱስ ከሺህው ዓመት በኋላ ይመጣል (post Millennialism) እስከዚያው ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን እያሰፋችና እያሳደገች የሺህ ዓመቱ መንግስት እስከሚመሰረት ድረስ ትዘልቃለች ይላል።

2. በሺህ ዓመቱ መካከል (AMillennialism) የእስራኤል ተስፋ እና ቃል ኪዳን ወደ ቤተ ክርስቲያን ተሻግሯል፤ ከዚህ በኋላ ስለ እስራኤል መጨነቅ አይገባም፤ ይህም ደግሞ አሁን ሆኗልና ሺህ ዓመት የሚባል መስፈርት ወይም መፃኢ ተስፋ የለም።

3. ዘመነ መስተዳደር ከሺህ ዓመት በፊት (Dispensational Millennialism) የቃል በቃል ትርጉምን ዋቢ አድርጎ በመነሳቱ እስራኤልንና ቤተክርስቲያንን ለያይቶ ያያል፤ ያምናልም፤ እግዚአብሔር እስራኤል አመፀኛ በመሆኗ የእርሷን መከሊት በመንጠቅ ለቤተክርስቲያን ሰጥቷል፤ ኋላ ላይ እስራኤል ንስሀ ገብታ ከጌታዋ ጋር ስትስማማ የቤተመቅደስን እና የብሉይ ኪዳን አገልግሎት በቦታው ይተካል፤ መስዋዕትም ይካሄዳል።

4. ከመከራው ዘመን በፊት ንጥቀት ይሆናል። (Thepre-tribulation Rapture) ቤተ ክርስቲያን በንጥቀት አማካኝነት ከዚህ ምድር ስትወሰድ በተከታዩ 7 ዓመታት ቅድመ እኩሌታና ድህረ እኩሌታ ላይ ሀሳዊው ከእስራኤል ጋር ይግባባል ውሎ አድሮም ጥላቻ

ይኖራል ከሰባት አመት በኋላ ኢየሱስ ይመጣል ኢየሱስም ለሺህ ዓመት በምድር ይነግሳል።

5. ከታሪካዊው የሺህ ዓመት መንግስት በፊት (Historical Premillennialism) በሺህ ዓመት መንግስትና በዘመነ መስተዳደር መካከል ያለውን ልዩነት የሚያስታርቅ ነው፤ ራዕይ ምዕራፍ 13 ያለውን አውሬ ሮም በማድረግ ገልፆ ኋላ ላይ የክርስቶስ ተቃዋሚ ተደርጎ ይቆጠራል። በምዕራፍ 19 የክርስቶስ ዳግም መምጣት የሴጣንን ክፋት በማሸነፍ የሚገለፅ መሆኑን ያመለክታል።

ከእነዚህ ተጠቃሽ ነጥቦች ውስጥ በሺው ዓመት ላይ አነጋጋሪው ጉዳይ፡-

**ሀ.** ኢየሱስ የክህነትን ስርዓት ቀይሮታል፡- ይህም «ሌዋዊው ክህነት እንደ መልከ ፀዴቅ በሆነ ክህነት ኢየሱስ ለዘላለም እንደሚለውጠው እግዚአብሔር በመሀላ ቃል አረጋግጦለታል

«ክህነት ሲለወጥ ህጉ ደግሞ ሊለወጥ የግድ ነውና» ዕብ 7፡12

«አንተ እንደ መልከ ፄዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ይመሰክራልና» (ዕብ 7፡17 መዝ 110፡4)

«እርሱ (ኢየሱስ) ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው ዕብ 7፡24

«ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈፅሞ ሊያድናቸው ይችላል። (ዕብ 7፡25)

**ለ.** የኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕትነት ለዘላለም ነው፡- በምንም ዐይነት መንገድ የኢየሱስ መስዋዕትነት እንደገና በእንስሳ መስዋዕት የሚተካ አይደለም። «እርሱም እንደነዚያ (እንደ ብሉይ ኪዳን) ሊቀካህናት አስቀድሞ ስለ ራሱ ሀጢአት በኋላም ስለ ህዝቡ ሀጢአት ዕለት ዕለት መስዋዕት ሊያቀርብ አያስፈልግም ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈፅሞ አድርጓልና (ዕብ 7፡27) ይላል።

**ሐ.** አዲስ ኪዳን አሮጌውን ተክቷል «አዲስ በማለቱ ፊተኛውን (አሮጌውን) አስረጅቷል አሮጌውና ውራጅ የሆነውስ ሊጠፋ ቀርቧል ዕብ 8፡13 ሁለተኛውን ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል (ዕብ 10፡9) የዚህንም እርግጠኝነት ሉቃ 21፡6 ላይ «እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነው፤ እጅ በሰራው መቅደስ አይኖርም» በማለቱ ቤተመቅደሱ እንደገና ተገንብቶ አይሁዳዊ ስርዓት ይጀምራል ማለት ዘበት ነው(**የእረኛው <u>ምርኩዝ</u>** ቅፅ 2 ገፅ 668-670 2000 ዓ.ም)





እንግዲህ በቅጡ ለማስተዋል፤-ተገቢ ጭብጦችን በድጋሚ ላመላከት ይህም ለተከታዮቹ ምዕራፎች እንደ ማሳለጫ ሆነው ያገለግሉኛል። ለዚህም አጋዤ የ «The<u>Covenant & the Kingdom»</u> by Charles Simpson p.397-400 1995 ነው።

## ሁሉን አመካካቹ ጥቅስ

ቲቶ 2፡11-13

*11 «ድነት የሚገኝበት የእግዚአብሔር ፀጋ ለሰዎች ሁሉ ተገልጧልና ይህም ፀጋ በኃጢአት መኖርን ዓለማዊ ምኞትን ክደን በአሁኑ ዘመን ራሳችንን በመግዛትና በፅድቅ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት እንድንኖር ያስተምረናል ይህም የተባረከ ተስፋችን የሆነውን የታላቁን የአምላካችንንና የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ በመጠባበቅ ነው...»*

### የአንዳንዱ «አመለካከት መንደርደሪያ»

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ሲገባ፡- በሀጢአት፣ በሞት እና በሴጣን መንግስት ላይ ድል መንሳቱን በትንሳኤው ከገለፀበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ዘመን የመጨረሻው ጊዜ ነው፤ ያለንበትም ከያኔ የጀመረ ጊዜ የሚሊኒየሙ ወይም የሺው ዓመት መገለጫ ነው፤ ሺህ ዓመት የተሰፈረ ቁጥር ሳይሆን ምሳሌያዊ ንግግር ነው፤ ብዙ ዘመንን የሚወክል፤ ይህ ጊዜም በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ የበለጠ ታላቅነቱ ይገለፅበታል፤ሲመለስ በእርሱ የሞቱትን ያስነሳል፤ ፍርድ ይካሄዳል፤ ዘላለማዊው ኑሮ ዘላቂ ይሆናል። (A millennialism)

(የቤተክርስቲያን ዘመን - ዳግም መመለስ - ፍርድ - የዘላለም መንግስት) ለዚህ ግንዛቤም መንደርደሪያዎቹ ኤፌ 1፡20 1ቆሮ 15፡20-28 ማቴ 24፡36 ራዕ 20፡11-13 ራዕ 20፡2-6 ዮሐ 15፡15-19 ማቴ 10፡22-

«...ክርስቶስን ከሙታን ሲያስነሳውና በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው የታየው ነው፤ የተቀመጠውም ከግዛትና ከስልጣን ከኃይልና ከጌትነት እንዲሁም በአሁኑ ዘመን ብቻ ሳይሆን በሚመጣውም ዘመን ሲሆን እሱም ሊሰየም ከሚቻለው ስም ሁሉ በላይ ነው። (ኤፌ.1፡20-21) ...ያን ቀንና ሰዓት ግን ከአብ በስተቀር የሰማይ መላዕክትም ቢሆኑ ወልድም ቢሆን ማንም አያውቅም፤ ልክ በኖህ ዘመን እንደ ሆነው የሰው ልጅ መምጣትም እንደዚሁ ይሆናል (ማቴ 24፡36-37)።

ይህን አቋም እያሳደገ እና እያስተማረ ያስኬደው ቅዱስ አውግስጢን ነው ከ420 ዓ.ም ጀምሮ በቀጠሉት 1100 ዓመታት ሉተራውያንን ካልቪናውያንና እንግሊካኖች ግንዛቤያቸውን የቃኙት በዚህ ነው።

አሚሊኒያኖች ራዕ 20ን ተምሳሌትያዊ (Symbolic)ነው፡- ይልቅስ ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን እያደሱ በየጊዜው እንዲኖሩ በመምከር በዓለም ያለው ስርዓት ልክ የኖህ ዘመን እንደነበረው ዘልቆ እግዚአብሔር አብ የወሰነው ቀን ሲደርስ ኢየሱስ ዳግመኛ ይመጣል (ይመለሳል) ይላሉ።

## የሌላው አመለካከት መገንደርደሪያ

ድህረ ሚሊኒያሊዝም (ሺህ አመት) በ Post millennialism የተገለጠው ቤተ ክርስቲያን ለሺው ዓመት መጀመር የሚያግዙት ቅድመ ሁኔታዎችን ሁሉ በማመቻቸት ትሰራለች፤ ከቃሉ የተነሳ፣ ከመንፈስ ቅዱስ እገዛ እና አጥቢያ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ ኖረው ሊያመጡ የሚችሉትን የብርሀንነትና የጨውነት ሐላፊነት ይወጣሉ፤ የዚህም አቅም የሺውን አመት ዘመን አንድ በማለት ያስቀጥራል። ይህም ጊዜ ተጠብቆ ሲያልቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ይመለሳል ፍርድና ዘላለማዊ መንግስት ይቀጥላል።

(የቤተ ክርስቲያን ዘመን - ሚሊኒየም - ዳግም መመለስ - ፍርድ - የዘላለም መንግስት) ይህ አመለካከት ንጉስ ቆስጠንጢኖስ ክርስቲያን በመሆን ሰፊውን ዓለም ከ4ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በክርስትና ሽታ ለማጤን ከሞከረበት ጊዜ ጀምሮ ቤተክርስቲያን መንግስትን ወደ ክርስቶስ በማፍለስ እና በመቋቋም ፍፁም ሰላም ያለበትን ሁኔታ ትመሰርታለች። የክርስቶስ የሆነችው ቤ/ክ ፍቅርን፣ አንድነትን፣ ሰላምን የማምጣት አቅሟ ግልፅ ሆኖ ይመጣል። ከዚያም የሺህ ዓመት መገለጫ በዓለም ሁሉ ይታያል የሚል እምነት አለው።

ይህ ግንዛቤ ኢየሱስ ዳግም ከመመለሱ በፊት ቤተክርስቲያን የእርሱን የመሰለ አገዛዝን በዓለም ላይ ታመጣለች ብሎ መፅናቱ አነጋጋሪ ሊሆን ይችላል።

ኢሳ 2፡1-4 ኢሳ 61፡1-11 ኢሳ 62፡1-12 ኢሳ 65፡17-25 ኢሳ 60፡1-22 ሉቃ 19 የሐ 1፡5 ተጠሪዎቹ ናቸው

«... ብርሀን በጨለማ ያበራል ጨለማም አላሸነፈውም» (ዮሐ. 1፡5) «...በዘመኑ ፍፃሜ... እርሱ በሕዝቦች መካከል ይፈርዳል የብዙ ሰዎችን አለመግባባትን ያስወግዳል እነርሱም ሰይፋቸውን ቀጥቅጠው ማረሻ፣ ጦራቸውንም ማጭድ ያደርጋሉ፣ ሕዝብ በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሳም፣ ጦርነትንም ከእንግዲህ አይማሩም...» (ኢሳ 4፡1-5)። ይህ ክፍል ዓለም ልትሆነው የሚገባውን ከፍተኛ ደረጃ ያስረዳል ኢሳ 4፡5 በተባበሩት መንግስታት የመግቢያ በር ላይ ሲፃፍ ተሰፋው ከቤተክርስቲያን በምድር ላይ መኖር የተነሳ ለውጥ ይመጣል የሚል ነው።





## የአመለካከት ሶስት መገንደርደሪያ

ቅድመ ሺህ አመት፡- ይህ ከቀደሙት የሚለየው ሺውን አመት አስጀማሪ በመሆን የሚመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ይህም መምጣቱ ድንገት፣ እንደሌባ ይሆናል፤ መግዛትም ይጀምራል፣ የመጀመሩ መገለጫ ግን የምድር መንቀጥቀጥ፣ ጦርነት፣ ረሀብ፣ ከፍተኛ መጥለቅለቅ፣ ጥፋት በዓለም ላይ መምጣቱ ምልክት ሆነው ይገለጣሉ፤ በቤተ ክርስቲያንም ታይቶ የማይታወቅ መከራ፣ ስደት እና ሀሳዊ ትምህርት ይበዛል።

(የቤተ ክርስቲያን ዘመን - ታላቁ መከራ - ዳግም መመለስ - የሺህ ዓመት ግዛት - ፍርድ - ዘላለማዊ መንግስት) መገለጫው ይሆናል።

በዚህ ሺህ አመት እግዚአብሔር የምድርን እርግማን ፈፅሞ ያስወግዳል፣ በመጨረሻም ሲጣንን ከሺው ዓመት በኋላ ፈትቶት ያምፅ ዘንድ ዕድል ይሰጠዋል።

ማቴ. 24፡14 2ተሰ 2፡8 2ጢሞ 2፡12 ራዕ 20፡6 ራዕ 20፡7-10 ራዕ 21፡10-27 1ተሰ 4፡13-18 2ተሰ 2፡12 2ጴጥ 3፡10

«...ለሕዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግስት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል ከዚያም መጨረሻው ይመጣል። ማቴ 24፡12 «...የጌታ ቀን ግን እንደ ሌባ ይመጣል፤ በዚያች ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ የሰማይም ፍጥረት በእሳት ይጠፋል፤ ምድርና በእርሷም ላይ ያለ ነገር ሁሉ ይቃጠላል...» (2ጴጥ 3፡10)

## ሌላኛው የአመለካከት መገንደርደሪያ

Dispensational millennialism አሜሪካዊው ወንጌላዊ C.L.Scofield ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ያመጣው ግንዛብ ነው፤ በትምህርቱ እስራኤልና ቤተክርስቲያንን በተለያየ መርሐ ግብር ውስጥ ይመለከታል። በዝግጅቱ የዳንኤልን መፅሐፍ እና የራዕይ መጽሐፍ በዋና ምንጭነት ይቀበላል፤ ክርስቶስ በስውር በመምጣት ቤተክርስቲያንን ይወስዳል፤ በምድር ላይ መከራ ይሆናል፤ ኢየሱስ ዳግም ይመጣል። ሺህ አመቱ በመጀመሪያ ፍርድንና ዘላለማዊ መንግስትን ያካትታል (ቤተክርስቲያን - ንጥቀት - መከራ - ዳግም መምጣት - ሺህ አመት - ፍርድ - ዘላለማዊ መንግስት) ይህን ለማመላከት ማቴ 13 ማቴ 24 ማቴ. 25 ዳን. 7 1ተሰ. 4፡17 1ተሰ. 4፡18 የሐ. 14፡26 ይጠቀማል።

***

እንግዲህ የእነዚህ ሁሉ የአመለካከት መነሻ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፤ በመሰረቱ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ ሌሎችም አመለካከቶች አሉ፤ እንዲሁም ቢሆን ግን፡-

1ኛ **ኢየሱስ ራሱ ተመልሶ መምጣቱን መግለፁ** «...የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ በደመና ሲመጣ ያዩታል» ማቴ 24፡30 እንዲሁም «...በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ ይህ ባይሆንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር የምሄደውም ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ...» (ዮሐ 14፡2-3 በማለት መመስከሩ።

2ኛ **መላዕክት አስቀድመው መናገራቸው** «እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ ደግሞም «የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል። አሏቸው። (ሐዋ 1፡10-11)

3ኛ **የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት** «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ እነሆ ገበሬው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሰ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል፤ እናንተ ደግሞ ታገሡ ልባችሁንም አፅኑ የጌታ መምጣት ቀርቧልና (ያዕ 5፡ 7-8)።

እነዚህ ምስክሮች ስለ ጌታ ዳግም መምጣት እንድናስብ ብቻ ሳይሆን እምነን እንድንጠብቅ ያግባባሉ፤ ግን አሁንም መቼን ለመመለስ ሰዎች ባደረጉት ጥረት ውስጥ የመለኪያ መቁጠሪያቸውን በ2 ጴጥ 3፡8 ላይ በማድረግ ዘመኑን ያስቆጠሩ ብዙዎች አሉን።

ጴጥሮስ «...በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ አመት ሺህ አመትም እንደ አንድ ቀን እንደሆነ...» ከሚለው በመነሳት ስድስት ቀንን በስድስት ሺህ አመታት ለመቀየር ሞክረዋል። ከዚህም የተነሳ ከአዳም ውድቀት እስከ ክርስቶስ በስጋ መገለጥ 4000 አመታት አኑረው በ4 ቀን አበጁት።

ክርስቶስ ካረገበት እስከ አሁን ያለው 2000 አመታት እንደ ሁለት ቀን በመቁጠር 4+2=6 የስድስተኛው ቀን ፍፃሜ እግዚአብሔር ስራውን ሰርቶ ያጠናቀቀበትና የሚያርፍበት ቀን ስለ ነበር ሰባተኛው በክርስቶስ ዳግም መምጣት ከ6000 ዓመታት በኋላ ያለው ጊዜ ክርስቶስ ዳግም በመመለስ ለሺህ አመት ወይም ለአንድ ቀን ይገዛበታል በሚል ጥበቃ ፀኑበት።

ይህንኑ ትምህርት ለማጠናከር የሙሴን የመገናኛ ድንኳን ውጪኛውን አደባባይ፤ የቅድስቱንና የቅድስተ ቅዱሳኑን ርዝመት፣ ስፋትና ቁመት በማስላት አሁንም ከኢየሱስ ዳግም መምጣት ልኬት





ጋር አገጣጠሙት።

በዚህም የውጪኛው አደባባይ ርዝመቱ 100 ክንድ፣ ስፋቱ 50 ክንድ ሲሆን ቁመቱ 5 ክንድ በሆነ የሐር ጨርቅ መጋረጃ የተከበበ ነበር (ዘፀ 27፡18) እንግዲህ የሁለቱን ወገኖች ርዝመት 100+100=200 ክንድ ስፋቱ 50+50=100 በአጠቃላይ የውጭኛው አደባባይ ርዝመት (ዙሪያውን) ስንደምረው 200+100=300 ክንድ ይሆናል

ይህን ዙሪያ ርዝመት በሀር ጨርቅ ቁመት ቢባዛ 300×5=1500 ይሆናል፤ ሺህ አመት እንደ አንድ ቀን በሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስሌት መሰረት አንድ ክንድ እንደ አንድ ዐመት ብንወስድ 1500 ዓመት ከሙሴ እስከ ክርስቶስ በስጋ መገለጥ ይወከላል ይኸም የሙሴን ሕገ ዘመን ይገልፃል።

ወደ ቅድስቱ በመግባት ርዝመቱ ሲሰራ 20 ክንድ ስፋቱ 10 ክንድ ቁመቱ 10 ክንድ ነው (ዘፀ 26፡1-37) ይህ ደግሞ 20×10×10=2000 ስኬዌር ክንድ ይሆናል አሁንም ሺህ አመት እንደ አንድ ቀን በሚለው ስሌት መሰረት አንድ ክንድ እንደ አንድ ዓመት ብንወስድ 2000 ዓመታት ይሆናል። ይህ 2000 ዓመት የቤተክርስቲያን ዘመንን ይወክላል።

ወደ ውስጠኛው ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ሲመጣ ርዝመቱ 10 ክንድ ስፋቱ 10 ክንድ ቁመቱ 10 ክንድ ነው (ዘፀ 26፡1-37) 10×10×10=1000ክንድ ይሆናል አንድ ክንድ እንደ አንድ ዓመት ሲታሰብ 1000 ውን ዓመት ክርስቶስ የሚገዛበትን ሺህ አመት ያመለክታል።

በትይዩ የሆሴዕን ትንቢት መሰረት በማድረግ ኢየሱስ መቼ ሊመለስ እንዳለው ማጣቀሚያ አለን የሚል ግንዛቤ አለ፤(ሆሴዕ አምስትን ማጥናት ተገቢ ነው)፤ «...ከሁለት ቀን በኋላ ያድነናል፤ በሶስተኛው ቀን ያስነሳናል በፊቱም በሕይወት እንኖራለን።»

ከሁለት ቀን በኋላ የሚለውን 2000 አመታት የቤተ ክርስቲያንን ዘመን በሶስተኛው ቀን የሚለውን ደግሞ የሺህ ዓመቱን ክርስቶስ ተመልሶ የሚገዛበትን ይወክላል ይላሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ ኢየሱስ የተናገረውንም የሉቃስ 13፡32 ገለፃን ለዚሁ የ«መቼ» ጥያቄ መመለሻ የሚያደርጉም አሉ።

ኢየሱስን «... ሕዝቡ ንጉስ ሔሮድስ ሊገድለው እንደሚፈልግ በመግለፅ ከዚህ ወጥቶ እንዲሄድ ለኢየሱስ በነገሩት ጊዜ ኢየሱስ የሰጣቸው መልስ «ሄዳችሁ ለዚያች ቀበሮ እነሆ ዛሬና ነገ አጋንንትን አወጣለሁ በሽተኞችንም እፈውሳለሁ በሦስተኛውም ቀን እፈፅማለሁ» በሉት ያለበትን ቃልስሌት አውጪዎቹ ኢየሱስ ዛሬና ነገ ያለበት ሁለት ቀን ቤተክርስቲያን የተሰጣትን ስራ ይመለክታል ይህም

ሁለት ሺህ (2000 ዓመታት) ይሸፍናል። በሦስተኛው ቀን ደግሞ የተመለሰበትን የሺህ ዓመቱን ዘመን የሚያመለክት ሲሆን ይህም የክርስቶስን የሺህ ዓመት አገዛዝ ይገልፃል ይላሉ።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ስሌቶች እንዲሁም በዳንኤል 69 ሱባኤ አልቆ በመሀል የቤተክርስቲያን ዘመንን በማመላከት 70ኛው ሱባኤ ከኢየሱስ የሺህ አመት አገዛዝ ጋር የሚያስተያዩ አስተምህሮች በአመዛኙ አደናጋሪ፣ እርስ በርስ ተጋጪ እና ዋዣቂ መሆናቸውን ልብ ማለት ተገቢ ነው(**የእረኛው <u>ምርኩዝ</u>** ቅፅ 1 ገፅ 2፣ 544-550)

ጊዜ ቆራጭ የሆኑ አመለካከቶችን ጨምሮ እና ሌሎች የተዛቡ ግንዛቤዎችን ያቀበሉ የቀደሙ መምህራንን **<u>«የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ ምግባር የመግቢያ ሃሳቦች</u>** ፀሐፊ ሮበርትሰን መኩልከን እንዲህ ይሏቸዋል «... ቅድመ አያቶቻችን ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የታወሩ በመሆናቸው ምክንያት መውቀሱ ምናልባት ግብዝነት ይሆናል እኛስ ዛሬ ላይ ያለነው በምን ሁኔታ ነው እውሮች በመሆን እውነቱን በቅጡ እንደመረዳት **<u>መጽሐፍ ቅዱስ ያካለውን እና ዝም ብሎ ያከፈበትን ተዳፍረን «ይኸው» ነው በቃ . . .</u>** የምንለው ይላሉ (መስመር ከራሴ ገፅ 344 2002 ዓ.ም)

ከላይ ለመዘርዘር የተፈለገው ኢየሱስ ክርስቶስ መቼ ይመለሳል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መመለሱን የሚያረጋግጡትን ጥቅሶች መነሻ በማድረግ ከዚያም አመለካከቶችን በማተያየት ለማስተዋወቅ ተሞክሯል፤ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ተከታታይ ምዕራፎች በአመለካከት ደረጃ ያልተነሳውን ግን በሰፋት አንስተን የምንመካከርበትን የሰባውያን (የፕሪቴሪስት) ግንዛቤን ማብራራት የጥናቴ ዋና ይሆናል።

# ምዕራፍ ሶስት

# ሰባውያንና (pereterist) ስነ መስተዳደራውያን (Dispensalists) <u>በዳግም መመለሱ ላይ</u>

የሰባውያንን ግንዛቤ በክርስቶስ ዳግም ምፅአት ያላቸውን ለመመዘን የታ.ቃ.ስ ስልትን መከተል የግድ ነው፤ ምርምራችን የቤሪያ ሰዎችን ስልት የተከተለ ስለሆነ እና የእግዚአብሔር የሆነውን እውነት በጋራ በመወያየት፣ በመጠያየቅ፣ ጥልቅ የሆነ ትጋት በመከወን ወደ ልከኛ ግንዛቤ መድረስ ቀዳሚ ጉዳዬ ነው።

**ሰባውያን** የሚለውን ስያሜ እንደመለያ የሰጠሁት የክርስቶስ ዳግም ምፅአት እና ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች በ70 ዓ.ም ሮማውያን ቤተመቅደሱን ያፈረሱበትንና በአይሁዳውያን ላይ ወደር የለሽ መከራ እና ስቃይ በማድረሳቸው አጥኒዎቹ 70ን የብዙ ተያያዥ አስተምህሮ መለያ አድርገው





መቁጠራቸው ቀዳሚ መነሺያዬ ነው።ልክ የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ፣ ሞትና ትንሳኤ በክርስትና አስተምህሮ ላይ ጉልህ ስፍራ እንደሚሰጠው በዚህም ጥናት ላይ 70 አመተ ምህረት የዚያን ያህል አገልግሏል።

ከዚህም የተነሳ ይህን ከሥነ ፍፃሜ ትምህርት አኳያ በምዕራፍ ሁለት ሳይካተት ለብቻው ከዚህ ቀጥሎ ይስተናገዳል፤

ከፍቹው እንጀምር:- ኔሮ ለ42 ተከታታይ ወራት ከፍተኛ ስደትን መከራንና እንግልትን በዘመኑ አድርጓል፤ በዚህም የአይሁድ ቀናተኞች፣ የተደራጁ መቃብያውያን፣ በአጠቃላይ አይሁድነት የተከበረ እምነት ነው ይዞታውም የእግዚአብሔር መለኮታዊ ስጦታ ነው ብለው የታመኑበትአይሁዶች ተዋጉ፣ ተቃወሙ፣ ተሰደዱ።

ይህ እንቅስቃሴ የሮም መንግስትን ልዕለ ሀያልነት የተፈታተነ ስለሆነ ይህን በማሸነፍ ለማረጋገጥ እንዲሁም ለሌሎች መቀጣጫ እንዲሆን ሮማውያን ከ40 ዓመታት በላይ የግንባታው ስራ የተራዘመበትንና ዕፁብ ድንቅ በመሆኑ በዓለም ካሉት አስደናቂ ቅርሶች ዋንኛ የሆነውን ቤተመቅደስ ይፈራርስ ዘንድ መንግስቱ አዘዘ። ቁርጠኞቹ ሮማውያንም ኋላ ላይ ቤተመቅደሱን «ተዉት» የሚል መመሪያም ቢላክ ባልሰማ ባይነት አፈረሱት።

የ«Preterist» ላቲኑ ቃል «Preterism» ነው:- «አለቀ ተደመደመ ሆነ» እንደማለት ነው፤ ልክ እንደ «አሮማይ»፤ የስነ መለኮት መዝገበ ቃልም የሰባውያንን (preterism)ንስነ አፈታት ከግምት በማስገባት *የእግዚአብሔር የትንቢት ቃሎች ሁሉ ዮሐንስ ራዕይን ጨምሮ ፍፃሜን አግኝተዋል። ከ70አ.ም.በሁዋላም የሚጠበቅ ሌላ መልዕክት የለም፤ የተነገረው ሁሉተፈፅሞበታል።ይላሉ።*

ይህ ትምህርት ትኩረት ተሰጥቶት ወደ ቅዱሳን ጆሮ እና አይን ለማድረስ የሞከሩ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ላይ የተገኙ ምሁራን ብዙ ናቸው። ይህ ማለት ግን የትምህርቱ ንቅናቄ ቀድሞ አልታየም ማለት አይደለም፤ ጉዳዩን ከ70 ጋር አያይዞት እንደ ዮሐንስ አፈወርቅ st.John chrysostm፣ እንደ ታላቁ ቅዱስ ባዜል st.Basille Great እና እንደ ቂሳሪያው ኢያሱባስ Eusebius of Caesarea የመሰሉ ሰዎች የእስራኤል ቀጣይነት እንደማይታያቸውና በክርስቶስ መሲህይቷ ማህበረሰብ ብቻ ኑዋሪ መሆኗን አስተምረው ነበር።

ከ1900 ዓመታት በኋላ ግን እንደ ጀምስ ስትዋርት ሩሰል James Stuart Rusell (የህዋ እምነት መስራች አይደለም) በ<u>the parousia</u> በሚለው መፅሐፉ፣ እንደ ማክስ ኪንግ Maxking በ <u>The Spirit of Propheey, Cross and The Parisia</u> በሚሉ መፅሐፎቻቸው ይህን ሰባ አስመልክተዋል፤

ቁርጥ ያለ አቋም ባይዙም ታዋቂዎቹ ሰባኪያንንና ፀሐፍት የሆኑት እና Dr. R.C.Sprual,Dr. Kenneth L እና Gentry and Gary Demor በዚህ ግንዛቤ ላይ ልባቸውን አስፍተዋል።

የ «The parousia» ትክክለኛ ትርጉም «መገኘት» ነው የ king James Strog dictionary ቃሉን «መምጣት፣ መገኘት፣ መመለስ በተለይም ኢየሩሳሌምን በፍርድ ለመቅጣት መገኘት» የሚለውን አጣቋሚ ፍቺ አስፍሩዋል።

ይህንንም ሰባውያን ለማቴ 24፡3 መግጠሚያ ፍቺ በማድረግ ይጠቀሙበታል፤ «ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ ሳለ ደቀመዛሙርቱ ብቻቸውን ወደ እርሱ ቀርበው «ይህ ሁሉ ነገር የሚሆነው መቼ ነው?የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክትስ ምንድን ነው?» ያሉበትን በቀዳሚ መረጃነት ይወስዳሉ።

ሰባውያን ለዚህ የስነ ፍፃሜ እምነት ራሱን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ሁነኛ እማኝ በመቁጠር እሱ እኮ፡-

ሀ. በማቴ 10፡23 *«...በአንድ ከተማ መከራ ሲበዙባችሁ ወደ ሌላ ከተማ ሽሹ በእውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ የእስራኤልን ከተማዎች ሁሉ አታዳርሱም...»*

ለ. ማቴ 16፡27 *«የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ሆኖ ከመላዕክቱ ጋር ይመጣል፤ በዚያን ጊዜም ለእያንዳንዱ እንደ ስራው መጠን ዋጋውን ይከፍለዋል»*

ሐ. ማቴ 24፡34 *«...በእውነት እላችኋለሁ ይህ ሁሉ እስኪፈፀም ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍል»*

መ. ማቴ 26፡64 *«...ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት አንተ እንዳልሽው ነው ነገር ግን ከአንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይሉ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ታያላችሁ እንዲሁም በሰማይ ደመና ሆኖ ሲመጣ ታዩታላችሁ እላችኋለሁ...»*

ከማለቱ የተነሳ ኢየሱስ የመመለሱ ጊዜ በቅርቡ ሊሆን እንደሚችል አመላክቷል፤ ከዚህም የተነሳ የገዛ ደቀመዛሙርቱ ባልሞቱበት ወይም ያ የወቅቱ ትውልድ ባለበት ጊዜ ይህ ተስፋ ተፈፅሟል፤ ከዚህ ጋር አስተሳስሮም ወይም አመሳስለው እንደ ሁነኛ መረጃ ሰባውያን የሚወስዱት ራዕይ መጽሐፍን ነው። ለምሳሌ ራዕ 1፡1 ይህ ራዕይ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚሆነውን ነገር ለአገልጋዮቹ እንዲያሳያቸው እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም መልአኩን ልኮ ለአገልጋዩ ለዮሐንስ ይህን ራዕይ ገለጠለት።





*ራዕ 2፡16 ጴርጋሞን... ስለዚህ ንስሀ ግባ አለበለዚያ በቶሎ ወደ አንተ መጥቼ ከአፌ በሚወጣው ሰይፍ እወጋችኋለሁ። ራዕ 3፡11 ፊላድልፍያ...እነሆ በቶሎ እመጣለሁ አክሊልህን ማንም እንዳይወስድብህ ያለህን አጥብቀህ ያዝ...» ራዕ 22፡6 ከዚህ በኋላ መልአኩ እንዲህ አለኝ «እነዚህ ቃላት የታመኑና እውነቶች ናቸው መንፈሱን ለነብያት የሚሰጥ ጌታ አምላክ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሚሆኑትን ነገሮች ለአገልጋዮቹ ለመግለጥ መልአኩን ላከ...»*

ራዕ 22፡20 «የእነዚህ ነገሮች ምስክር የሆነው «አዎ በቶሎ እመጣለሁ» ይላል ተጠቃሾቹ ክፍሎች በምን ዐይነት ሁኔታ ኢየሱስ እንደሚመለስ ባይናገሩም ነገር ግን ድርጊቱ በቅርብ ሊከናወን እንደሚችል አመላክቷል የሚል እምነት «ሰባውያን» አላቸው።

ከራዕይ መጽሐፍም ሌላ አንዳንድ መልዕክቶች የኢየሱስን በቅርብ መምጣት እንዳጣቆሙ ይታወቃል፤ ይታመናል፤ ለዚህ ግንዛቤያቸውም የሚከተሉትን መፅሐፍት በሰነድነት ያነሳሉ፡-

ሮሜ 13፡11-12 *«እንግዲህ ከእንቅልፍ የምትነቁበት ጊዜ መድረሱን በማወቅ ይህን ሁሉ አድርጉ ምክንያቱም በፊት ካመንበት ጊዜ ይልቅ አሁን የአዳኛችን መምጫ ቀን ይበልጥ ወደ እኛ ቀርቦአል፤ ሌሊቱ ሊያልፍ ነው ቀኑም ቀርቧል ስለዚህ የጨለማን ስራ አውልቀን ጥለን የብርሀንን የጦር መሳሪያ እንልበስ...»*

1ቆሮ 7፡29-31 *«ወንድሞቼ ሆይ እኔ የምላችሁ እንዲህ ነው ዘመኑ አጥሮአል ከአንግዲህ ወዲህ ሚስት ያለው ሚስት እንደሌለው ሆኖ ይኑር፣ ዕቃ የሚገዛ ዕቃው የራሱ እንዳልሆነ አድርጎ ይቁጠር በዓለም ሀብት የሚጠቀም በሙሉ እንደማይጠቀምበት ሆኖ ይኑር ምክንያቱም የአሁኑ ዓለም ሁኔታ አላፊ ነው»*

ይህ ገለፃም ተቀጣሪ ሆኖ የኢየሱስ ዳግም መመለስ ከተከናወነ በኋላ የሌለ ያህል እንዲቆጠር በማግባባት ዋቢ ሆኖ ቀርቧል።

1ቆሮ 10፡11 *«...ይህ ሁሉ ነገር የደረሰባችሁ ለእኛ የማስጠንቀቂያ ምሳሌ እንዲሆን ነው፤ የተፃፈውም በዘመናት መጨረሻ ላይ ለምንገኘው ለእኛ ትምህርት እንዲሆን ነው...»*

ያዕ. 5፡8-9 *«...እናንተም እንዲሁ ታገሱ የጌታ መምጫ ጊዜ ስለተቃረበ በተስፋ ፅኑ ወንድሞቼ ሆይ በእናንተ ላይ እንዳይፈረድባችሁ እርስ በርሳችሁ አትጨቃጨቁ እነሆ ፈራጅ የሚመጣበት ጊዜ ደርሷል...»*

ሰባውያን ከላይ የተዘረዘሩትን ሁሉ እንደ ወረዱ ካመንባቸው በእውነትም ጌታ በገዛ

ዘመናቸው ያኔ መጥቷል ለማለት ያስችለናል የሚል መደምደሚያን ያኖራሉ።

ሰባውያን እንዲህ ማሰባቸውንና ማመናቸውን ከሚሰጠው ጥቅም አኳያ ሲመነዝሩት:- ኢየሱስ በ70 ዓ.ም መመለሱ ተገቢ የሚሆነው:-

**አንደኛ** ኢየሱስ ቃሉን የሚጠብቅ ተስፋውንም የሚተገበር መሆኑን ያሳያል፤ ይህም የእርሱ መለኮትነት እንዲሁም ቃሉ ያለነቁጥ ስህተት ለክርስቲያኖች የተሰጠ መሆኑን ያረጋግጣል።

**ሁለተኛ:-** ሰባውያን ቀና ግንዛቤን ለዓለም ይይዙ ዘንድ ያደርጋል፤ ዓለሙ በሙሉ ይልቅኑ «የክርስቲያኑማህበረሰብ» የዓለም ፍፃሜን በመጠባበቅ ምድርም፤ የሰው ልጆችም የሚጠፉበትን በማውጠንጠን ጨለምተኛ የሆነ አቋም በመያዝ ይኖራሉ፤ ይህ ግን ለእኛ በተቃራኒው ነው ይላሉ።

**ሦስተኛ:-** ክርስትና ተግባራዊ ኑሮ መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችለው ይህ እምነት ነው፡ - ምድርን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ፣ ለተከታዩ ትውልድ ለማስተላለፍ መዘጋጀትን፣ በአጠገባችን ያሉትን ድሆች፣ በመርዳት እና በማካፈል የመኖርን አቅም ይሰጣል።

**አራተኛ:-** «የእግዚአብሔር ቃል እርስ በርሱ ተጋምዶ ወደ አንድ አቅጣጫ የሚፈስ መሆኑን ያረጋግጥልናል» ይላሉ ይህ ግን ለጌታ ቃል ታማኝ በመሆን ዝንባሌ እና ቶሎ፣ ቅርብ፣ የሚሉ ገለፃዎችን ለ70 ማብቃቱ ልክ ነው ባሉበት ትንሳኤን በተመለከተ፣ መጋባትን በተመለከተ ከሚወስዱት ግንዛቤ አኩያ ግራ አጋቢ አቋም እንዳላቸው ያመላከታል።

ሰዱቃውያን ትንሳኤ ሙታንን አያምኑም ግን ደግሞ ጥያቄ ይዘው ኢየሱስ ክርስቶስን ጠየቁት እሱም ተያያዥ የሆነ መልሱን ከፍፃሜ ታሪክ ጋር በማያያዝ መለሰ። በወቅቱ:-

እነርሱ የጠየቁት አንዲት ሴት *«ያገባት ዘር ሳያተርፍ ቢሞት ታናሹ ሊያገባት ይገባል» ስለሚል በተከታታይ ሰባቱ ወንድማማቾች አገቡአት በመጨረሻ እሷም ሞተች በትንሳኤ ታዲያ ለማንኛው ሚስት ትሆናለች? ባሉት ጊዜ የኢየሱስ ምላሽ ማግባት፣ መጋባት የዚህ ዓለም ሰዎች የሕይወት መገለጫ ነው ከዚህ ዓለም በኋላ በትንሳኤ ግን ይህ ስርዓት አይኖርም፤ እንደ መላዕክት ይሆናሉ»* በማለት መለሰ (ሉቃ 20:27-40)

በዚህ መልስ ኢየሱስ:- ሙታን ትንሳኤ እንዳላቸው እና ይህም በሚመጣው አለም እንደሚከናወን አስረዳ።

ሰባውያን ግን የኢየሱስን ምላሽ በዘመን ይከፍሉታል፤ የዚህ ዓለም ሰዎች የተባሉት በሙሴ





ሕግ ውስጥ የነበሩትን ከዚያም በሚመጣው ዓለም የሚለውን ከ70 ዓ.ም ጀምሮ ዳግም በመወለድ ትንሳኤን በማግኘት ተአምራዊ ስራ የተከናወነባቸውን አማኞች ይወክላል ይላሉ።

በዚህ መሰል የአተረጓጎም ስልት ሰባውያን የጌታ ራትን በተመለከተም የተለየ ግንዛቤ አላቸው፤ እስከ አሁን ያሉ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያናት ከጌታ ቃል እና ከኖራቸው ታሪካዊ ስምምነት የተነሳ የጌታን ራት/ቅዱስ ቁርባንን በወሰዱ ቁጥር የሚነበበው ምዕራፍ 1ቆሮ ም 11፤17-34 ነው።

*23 ከጌታ ኢየሱስ የተቀበልሁትን ለእናንተም ያስተላለፍሁላችሁ ትምህርት ይህ ነው... 26 ይህን ኅብስት በምትበሉበት ጊዜና ይህንን ፅዋ በምትጠጡበት ጊዜ ሁሉ ጌታ ኢየሱስ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ...»*

በማለት ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማንያን ይህን አሳወቀ። በመሰረቱ ቆሮንቶስ ከኢየሩሳሌምና ከቤተመቅደሱ ርቃ ያለች ሀገር ናት ምድሩ የአይሁዶች ሳይሆን የአህዛብ ነው፤ አረማውያን የየገዛ እምነታቸውን የሚለማመዱበት በነበረ ሕዝብ መካከል ነው ቤተክርስቲያን ተመስርታ ያለችው በዚያ ላሉት ወገኖችም ነበር ትክክለኛውን ግንዛቤ በመያዝ ይዘልቁ ዘንድ የሚፅፈው።

በዚህ ጉዳይ ላይ ጌታ እስኪመጣ ድረስ የጌታን ራት መውሰድ፣ ስለ ሞቱ፣ ስለ መከረኝነቱ፣ አማኞች በማሰብ የወንጌልን ስራ እንዲያዘልቁ ያመላከታል።

ሰባውያን ግን «እስከ» (until)በሚለው ላይ ትንታኔ ይሰጣሉ፤ ለዚህም ሮሜ 5:14 እና 1ጢሞ 4:13ን ይጠቀሳሉ።

«...ሞት ከአዳም አንስቶ <u>**እስከ**</u> ሙሴ በሰው ሁሉ ላይ ስልጣን አገኘ (ሮሜ 5:14) ...እኔ <u>**እስከመጣ**</u> ድረስ ቅዱሳት መፅሐፍትን ለህዝብ በማንበብ.... ይላል በእኒህ ሁለት ክፍሎች ያሉት እስከ ወይም until ሞትን በሙሴ ላይ አስቁሟል የሚል ፍች የለውም፤ እንዲሁም ጢሞቲዎስ ጳውሎስን ካገኘ በኋላ ንባብና ስብከት አቁሟል ማለት አይደለም፤ ይልቅስ ቀጣይነትን በውስጡ የያዘ አገላለጥ ነው።

ሰባውያን በ70 የኢየሱስ መመለስ እውን ሆኗል፤ ከማለት ባሻገር የእሱን ሞት በማሰብ ስርዓቱን መፈፀም ቀጣይነት መኖሩን ገላጭ ነው በማለት ያብራራሉ፡ ጨምሮም ቆሮንቶሳውያንን በብቻ የሚመለከት እንጂ ዓለም አቀፉን ክርስትናም አያሳይምም፣ ይላሉ እንግዲያስ ሞቱን መናገር ምን የሚያመጣው ጥቅም አለ። ደግምም መከራውን፣ ሞቱን እንደ አይሁድ አማኞች ላልተከተሉ ምን ፋይዳ ይኖረዋል።

ሰባውያን የጌታ ራት መውሰድ እንደሌለበት ለማመላከትም ማቴ 26:26-27 *«... ራት ሲበሉም ኢየሱስ ሕብስት አንስቶ የምስጋና ፀሎት አደረገ ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው ብሎ ሰጣቸው ፅዋንም አንስቶ ...ሁላችሁም ከዚህ ፅዋ ጠጡ ይህ ስለብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው...»* አላቸው ይህ ደግሞ የቀደመው ኪዳን አልፎ አዲሱ ኪዳን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ መታሰቢነቱም ሆነ ስርዓቱ ተፈላጊነት አይኖረውም፤ ካሉ በሁዋላ ሲደረግ ቢታይ ግን የሚያወጋግዝ አይሆንም ይልቅ ኢየሱስ በማቴ 26:29 *«በአባቴ መንግስት አዲሱን የወይን ፍሬና ጭማቂ ከእናንተ ጋር እስከምጠጣበት ቀን ድረስ ከአንግዲህ ወዲህ ከዚህ ወይን ፍሬ ጭማቂ ዳግመኛ አልጠጣም አላቸው»* የሚለው ቃሉን በ70 ዓመተ ምህረት ላይ በመመለሱ አብሮአቸው በአባቱ መንግስት መውሰዱን ይገልፃሉ።

እነዚህ ከላይ ሊብራሩ የተፈለጉ ክፍሎች አውዳዊ ትንታኔያቸው ልክ የጌታ መምጣትን በ«ቅርበት» አንዳለ ለመቀበል እንደወደዱ ሁሉ ለዚህ ትንታኔ በገዛ አመለካከታቸው ላይ ትንሳኤንም፣ የጌታ ራትንም በክርስቲያኖች ሊሆን እንደሚችል ከግምት ባስገቡ ነበር።

## ሰባውያን እና የሞት ግንዛቤ

በመሰረቱ መጽሐፍ ቅዱስን በቅጡ ለመረዳት መጣር ጥቅም አለው፤ ጥቅሙ መናፍቃዊ እምነትን ላለመፍጠር ወይም ላለመከተል ማገዙ ነው፤ **መናፍቅ - መንፈቅ - ክፊል እውነት ክፊል ሀሰትን የያዘ እምነትን ያንፀባርቃል፤** መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ የያዛቸውን ጭብጦች ጊዜ ሰጥተን ባለመረዳት ኋላ ላይ «ይህም ነበረበት ወይ?» የሚሉ ሰዎች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ነው።

እውነትን ግን በማወቅ ሊገጣጠም እና ሙሉ ሆኖ ሊታይ ከሚገባው የእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር ካልተገጣጠመ ጥረቱ ዘላቂ እንዳልሆነ፣ ተጀምሮ ባልተጠናቀቀ ጭብጥ ላይ ራስን ማየትና ማኖርን ያመጣል።

ቤተክርስቲያን ላለፉት 2000 አመታት አዳምንና ሔዋንን እግዚአብሔር ሲፈጥራቸው ሟች ሰዎች አድርጎ አይደለም (immortalbeing) ኑዋሪዎች እንጅ ትላለች፤ ይህ ግን በሰባውያን ዘንድ ከግምት አይገባም ይልቅስ ዘፍ. 2:17 «ነገር ግን ደጉን ከክፉ ለመለየት የሚያስችል ዕውቀት ከሚሰጠው ዛፍ ፍሬ አትብላ ምክንያቱም ከዚህ ዛፍ ፍሬ በበላህበት ቀን በእርግጥ ትሞታለህ» ያለለትንመመሪያ በትንታኔያቸው በመንፈስ ሙት በመሆን ከእግዚአብሔር መለየትን ብቻ ያረጋግጣል፤ ይላሉ።የዚህም እውነት ባልታዘዘበት ቅፅበት የሆነበት ከጌታው ሙሉ ለሙሉ መለየት ነው፤ በአካል አቋሙ ግን በሕይወት አለ፤ አልሞተም፤ ይህ የሚያረጋግጠው ሰው የተፈጠረው ስጋዊ ሞትን በሚሞት ሁኔታ መሆኑን ያሳያል።





ይህም የሚያስገኘው ጥቅም:- አዳም የስጋ ሞት እንደማይሞት የሚያሳይ ጥቅስ ወይም ፍንጭ አለመኖሩን ይልቅስ ወድቆ የሚደማ፣ ተመቶ የሚሰበር፣ አርጅቶ የሚሞት መሆኑን ያመለክታል።

ቤተ ክርስቲያን የሰው ችግሩ ማርጀቱ እንደሆነ ስላሰበች ብቻ ለዚህ መፍትሄ ብላ ያሰበችው፡ - የኢየሱስን በአካል መምጣትና በአካል የሆነን የሙታን ትንሳኤ መጠበቅ ነው።

በአካል መሞትን በመንፈሳዊ ግንዛቤ አሳድጎ ማሰብ ግን ያስፈልጋል፤ ለዚህም መንፈሳዊ መፍትሄ መስጠት ተገቢ ነው፤ የቤተ መቅደሱ መፍረስ የኢየሱስን ከገዛ ሕዝቡጋር እንዲገናኝ፣ የሕይወት ዛፍንም አብረው ይካፈሉ ዘንድ የመነሻ ጊዜን ራሱ ኢየሱስ እንደመሰረተ ያም ቀድሞ እንደተጀመረ ያስተምራል።

ሰባውያን ፍጥረት ትታደሳለች፣ መርገሟ ይነሳል፣ ሕመም የሌለባት እና የሙሉ ደስታ ዘመን ይመጣል በማለት ብዙዎች የሚያምኑትን እምነት አይቀበሉም፤ ላለመቀበላቸው፤-

ሀ. ሀጢአት ወደ ዓለም ከመግባቱ በፊት ነው፤ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ፍጥረትን እንዲንከባከቡ ያዘዘው ትዕዛዝ ቀጣይነት አለው፤

ለ. አዳምና ሔዋን የነበራቸው ተፈጥሮ አደጋን በመከላከል ላይ ያተኮረ ነው፤ ከአደጋ ራሳቸውን የመጠበቅ አቅም አላቸው፤ እንደዚያም ቢሆን ይወድቃሉ፤ ይደማሉ፤ ይህ ግን ከውድቀት ጋር ግንኙነት የለውም፤ ራዕይ ሞት የለም ሕመም የለም የሚለው በመንፈሳዊ ልደት ዳግም በመወለድ የሚገኘውን ሕይወት ነው።

ሐ. እግዚአብሔር በአካል ለሚታየው የሰው ልጅ ኑሮ ቅድሚያ የሰጠ አምላክ አይደለም ይልቅስ ራሱን መንፈሳዊ ይዘት ባለው አቅም ገልጧል፤ በዚህም በሀጢአት ምክንያት የመጣውን መንፈሳዊ ችግር መፍትሄ ሰጥቷል፤ በዓለም ላይ:- እሾህ፣ ኩርንችት፣ ገደላገደል፣ ላብ፣ አቧራ እና የመሳሰሉ ገለፃዎች ከእግዚአብሔር የመለየትን ገፅታ ለማሳየት የተሰጡ ዘይቤዎች እንጂ እውን መገለጫዎች አይደሉም። ይላሉ።

## ሰባውያን እና ተካካፊ የሀጢአት ዘር ምንነት

ሰባውያን:- ውርስ ሀጢአት የለም የሚል አቋም አላቸው፤ የተወለዱ ህፃናት፣በማህፀን ያሉ ሽሎች ሀጢአት አልባዎች ናቸው፤ በአዳም ጥፋት ተጠያቂነት የላቸውም፤ ለዚህም:-

ዘዳ 1:35-39 «ህፃናት ክፋትን የመስራት አቅም (ችሎታ) እንደሌላቸው ይናገራል በገለፃውም

እግዚአብሔር ከነዓንን የማያወርሳቸው፡- አባቶቻቸው ከፉዎች ልበ ደንዳኖች መሆናቸውን በመግለፅ የእነርሱ ህፃናት ግን ልጆቻቸውም ጭምር ከፉና ደግ የማድረግ አቅም የሌላቸው ስለሆኑ ለእነርሱ ምድሪቱን አሳልፎ እንደሚሰጥ ያበስራል፤ከዚህም የተነሳ ህፃናት የውርስ ሀጢአት የለባቸውም።

ሌላው ኢየሱስ ራሱ ወደ መንግስተ ሰማያት ለመግባት እንደዋንኛ ቅድመ ሁኔታ ያዘጋጀው «እንደ እነዚህ ሕፃናት ካልሆናችሁ መንግስተ ሰማያት አትገቡም» ብሎዋል።ይንንም በማቴ.18፡3 ላይ እውነት እውነት እላችኋለሁ በማለት ያስተማረበት መሰረታዊ ምክንያት ህፃናት ሀጢአት አልባ ወይም ከአዳም የተላለፈባቸው ምንም ነገር እንደሌለ ማረጋገጡ ነው።

ሕዝቅኤል 18፡19-20 ገለፃ ማንም በገዛ ሀጢአቱ እንደሚጠየቅ ያብራራል፤ልጆች በቀደመው የወላጆቻቸው ስራ ወይም በደል ተጠያቂ እንደማይሆኑ ያረጋግጣል፤ይህም ሕፃናት(ልጆች) በውርስ ሀጢአት ተካፋይ ቢሆኑ ይህን ነብዩ ባልገለፀ ነበር፤ይላሉ።

ከዚህም በመነሳት የኢየሱስ ዳግም መመለስ ምድራዊ ጉዳዮችን መፍትሄ ለመስጠት ሳይሆን ጥልቅ ግንኙነትን ከእግዚአብሔር ጋር የማድረጊያ ሒደትን መግለጫ እንጂ አካላዊ ይዞታ ያላቸውን& ወደ ቀደመው ቦታ ለመመለስ፣አዲስ አካል በመስጠት ለማስነሳት አይደለም።

ሰባውያን ከዚህም የተነሳ ከ18ኛውክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ትኩረት የተሰጠው «ንጥቀት»ም ከኢየሱስ የወደፊት መመለስ ጋር በመያያዝ ትምህርት ሊሰጥበት አይገባም ይላሉ።

1ተሰ 4፡15-17ንም ሲያብራሩ ክፍሉ ንጥቀት መኖሩን ለመግለፅ የታለመ ፈፅሞ አይደለም ንጥቀትንምየሚመለከት ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ አልያዘም፤ ይልቅስ ክፍሉ አካላዊ ትንሳኤን ሳይሆን እንደ ዮሐንስ 5፡24 *«እውነት እላችኋለሁ ድምፄን የሰማ እና የላከኝን ያመነ የዘላለም ሕይወት አለው ወደ ፍርድ ሳይሆን ወደ ሕይወት የመጣ ነው»* ያለበትን የመንፈሳዊ ሕይወት ትንሳኤን አመልክቶበታል፡በክርስቶስ በመሆን የሞቱትን እና (ያንቀላፉትን) (ቁጥር 14)፣በሕይወት ኖረው ኢየሱስ እስኪመጣ የሚጠብቁትን (ቁ.15)፣ጌታ በሚወርድ ጊዜ (ቁ.18)፣በአካላዊሕይወት በመኖር ያሉት (ቁ.17)፣ በአንድ ላይ ይሆናሉ፤ ይህም በሕይወታቸው በተሰራው መለኮታዊ ስራ የመጣ ነው። ከዚህ ውጭ የሚጠበቅ «ንጥቀት» ሳይሆን 70 ዓመተ ምህረትን መነሻ አድርጎ የዘለቀው እግዚአብሔር ተኮር አኗኗር ቀጣይ መሆኑን መገንዘብ ተፈላጊ እምነት መሆኑን ያስተምራሉ።

## ሰባውያን ከሰማይና ምድር ማለፍ ጋር

ኢሳይያስ በ24ኛው ምዕራፍ፤- ይህ ሰማይና ምድር እንደሚያልፍ እንዲሁም ዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ፡ - ሰማይና ምድር እንደሚያልፉ ይናገራል፤ እስራኤል የቃል ኪዳን ሕዝብ ናት፤ በዚህም በሲና ተራራ





ለዚህች ዓለም መፍትሄ ትሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ህግ ተሰጥቷል፤ ግን አልሰራችበትም ኢሳ 5፡ 5-6 እንዳጠናከረው ይህ ሰማይና ምድር ያልፋል፤ ሲል እግዚአብሔር እንከን የለሽ አድርጎ የሰራውን የእጅ ስራ በማስወገድ አዲስ ያመጣል ማለት አይደለም።

ይልቅስ ከሲና የተቀበለችውን፣ ባለመታዘዝ የፀናችበትን ያንን የቀድሞ ቃል ኪዳን ጌታ በማስወገድ የቀድሞውን «ሰማይና ምድር» በማሳለፉ አዲስ ሰማይና ምድርን ይሰጣል፤ ያም በክርስቶስ የተሰራው ሀጢአትን በማሸነፍ አቅምና የዳግም መወለድ ገፅታ በአዲስ ሰማይና ምድር ተተክቷል፤ ከዚህ ውጭ ሊመጣ ያለውን መጠባበቅ ተገቢ አይደለም ይላሉ። በተያያዥ፡-

2ቆሮ 3፡10 የአሁኑ ታላቅ ክብር ካለፈው ክብር ጋር ሲወዳደር ያለፈው ክብር እንዳልነበር ሆኖ ይቆጠራል።

ዕብ 8፡13 እንግዲህ አዲስ ኪዳን ሲል የፊተኛውን ኪዳን አሮጌ አድርጎታል ማለት ነው፤ ስለዚህ የተሰራበትና አሮጌው ነገር ሁሉ የሚጠፋበት ጊዜ ተቃርቧል።

*ኤፌ. 3፡3 «አስቀድሜ በአጭሩ እንደፃፍሁላችሁ እግዚአብሔር የተሰወረ ሚስጢር ገልጦ አሳይቶኛልን»ማጥናት እና በቅጡ ማንበብ ይገባል ይላሉ።*

## የሰባውያን መሰረተ እምነት

ዝርዝር ነገሮችን ከኢየሱስ «ዳግም መጥቷልና ዳግም ይመጣል» ዝግጅት ጋር አደርጅቶ ለማቅረብ በርካታ ገፆች እና የሰፋ የመወያያ መድረኮች ሊዘጋጅ ይገባል። እንዲህም ቢሆን ግን በእውቀት አድገን ለመገኘት፣ ለሚጠይቁን መልስ ለመስጠት፣ ልንጠየቅ ላለንበት ምንም ጉዳይ ለመዘጋጀት፣ እንዲሁም የገዛ ሕይወታችንን ለማነፅ፣ በየጊዜው ልብ ልንልበት የሚገባ ርዕሰ ጉዳይ ሲመጣ እንደ ቤሪያ ሰዎች ልበ ሰፊ በመሆን ነገሮችን ማጤን ያስፈልጋል።

➢ ቤተክርስቲያን ማህበር ናት፡- በክርስቶስ የሆኑትን ሁሉ ወደ እርሱ ቁመት በማሳደግ የክብሩ መገለጫ መሆኗን ማረጋገጥ ዘላቂ ስራዋ ነው፤ የተለያዩ ጉባኤያት ባለፉት 2000 ዓመታት ውስጥ ተካሂደዋል፤ ጭብጦቻቸውን ልናስታውሰው በምንችለው መንገድ ቀርፀው እንዳስቀመጡ እኔም ከሰባውያን መሰረተ እምነት ውስጥ ለእኛ ዝግጅት የሚያግዙትን ብቻ ቅድሚያ ሰጥቼ አስተዋውቃለሁ፤

➢ኢየሱስ በ70 አመተ ምህረት በመንፈሳዊ ይዞታ ዳግም ተመልሷል፤

➢የአካል ትንሳኤ የለም፤

➢አዳም በአካል ኢሟች (የማይሞት) ተደርጎ አልተፈጠረም፤

➢እሾህ አሜኬላ፣ ሕመም፣ ከእግዚአብሔር የመለየት መገለጫ ቃላት እንጂ የሀጢአት ውጤቶች አይደሉም፤

➢የሀጢአት ዘር ወደ ሕፃናት አይተላለፍም፤

➢የአካል ትንሳኤ ሳይሆን ከመንፈስ ሙትነት የመነሳት ትንሳኤ ብቻ አለ፤

➢አዲስ ሰማይና ምድር በ70 የተመሰረተውን የአዲስ ቃል ኪዳን መፈፀም መገለጫ ነው

➢ሴጣንና አጋንንቱ በ70 ዓ.ም ወደ እሳት ባህር ተጥለዋል፤

➢ራዕይ ከ70 ዓ.ም በፊት የተፃፈ መፅሐፍ ነው፤

## የስነ መስተዳደራውያን መሰረታዊ እምነት በጌታ ዳግም መመለስ ላይ

በአማርኛ ስነ መስተዳድራዊ በመባል የሚታወቀው Dispensationalism ወይም Dispensnation ብለን የምንጠራው የስነ ፍጻሜ ዘርፍ፡- ቀድመን ስለ ጌታ ዳግም መመለስ ያለውን አቋም ከማየታችን በፊት ስለንቅናቄው አጀማመር ጥቂት መንደርደሪያ መስጠት ተገቢ ነው።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን ነበር፤ ስለ ጌታ ዳግም መመለስ ትኩረት የሚሰጥ እንቅስቃሴ በአሜሪካ እና በእንግሊዝ የተጀመረው ይህ ትምህርት ትኩረት ተሰጥቶት ሲስፋፋ ጀርመኖችንና የስካንድንቪያን ሀገራት አልነበሩበትም።

በአሜሪካና በእንግሊዝ ግን በቀዳሚነት ስለ ጌታ መመለስ የሚተርኩ ትናንሽ ፁሑፎች፣ የመድረክ ላይ ስብከቶች በረከቱ፤ ቅዱሳትመፅሐፍትን መተርጎም፤ አብይ ስራ ሆኖ ዘለቀ። ተሳካም።

በተያያዥነትም የጥናቱ ውጤት ወይም አመለካከት አብሮሆተ መንፈስ ቅዱስ ያመጣውና የእስትንፋሰ እግዚአብሔር ሁነኛ ውጤት ተደርጎም እስከ መወሰድ ደረጀ፡- እንዲህም ሆኖ እንዲወሰዱ አቅም ካገኘው ግንዛቤ ውስጥ አንዱ ዲስፔንሴሽናል/ Dispensnation በመባል የተጠራው ነው፤ ስያሜው እንደጥላ ሆኖ ለዚህ ዝግጅት ያገልግል እንጂ በስሩ ተቀራራቢ የሆኑ





በመጠን ለየት የሚሉ ግና ድንበራቸውን ወይም መለኪያቸውን ከጌታ ዳግም መመለስ ጋር ያደረጉ ልዩነቶች መኖራቸውንእንዘነጋም። ይህንንም በቀዳሚ የመግቢያ ምዕራፍ ላይ ጠቁሜያለሁ።

ይህ ፅሑፍ ግን ዋንኛ ባህሪያቱን እና ጥቅል አቋሙን ብቻ ስለሚገልጥ ዝርዝር ስራ ውስጥ አይገባም።

በ1826፡- መገኘት ወይም Advent በመባል የሚጠራ ኮንፍራንስ ተካሂዶ ነበር፤ ስፍራው ደግሞ የወንጌል አገልጋይ የነበረው የሔነሪ ድራሞንድ/HenryDrummond ሀገር ነበር በዚያ ስብሰባ ላይ እንደ ኤድዋርድ አይሪቪንግ/Edward Irving የመሰሉ «የመሲሁ መምጣትን The coming of the Messiah በሚለው እንዲሁም በ ማኑኤል ላኩንዛ/Manuel lacunza መፅሐፍ የተማረኩ ሰዎች ተገኝተው ነበር፤ በዚያም ስፍራ ዲስፔንሴሽን የተደጋገመ ቃል ሆኖ ለሰፊ አገልግሎት ወጣ ወይም ተለየ።

ኤድዋርድ ይህን ካስተዋወቀ በኋላ ፈለጉን የሚከተል ሰው አገኘ፤ እሱም J.N Darby ነበር፤ የእነርሱን ግንዛቤ ደግሞ በወቅቱ በመቃወም የቆመው አገልጋይ B.W.Newton ነበር፤እሱ በትምህርትም በዝግጅቱም **«ዲስፔንሴሽን ከእውነተኛው የክርስትና መንገድ አማኞችን ማራቅ ወይም ማውጣት ነው»** በማለት ትምህርቱን አጣጣለው።

ከ1848 በኋላ ግን የ J.N.Darby ትምህርቶች ከ Schofield Reference Bible ጋር ተጣጥሞ በመዘጋጀቱና በመውጣቱ ትምህርቱ **አመለካከት** ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል ተገመተ።

ስነ መስተዳድር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአብዛኞቹ አማኞች ዘንድ ማድረስ የፈለገው ትምህርት በተመጠኑ ጭብጦች ሲገለጥ፡-

**ሀ.** ትንቢቶች ሁሉ ቃል በቃል (በቁማቸው) ሊወሰዱ ይገባል፤ ይላል ለዚህም፡-

1. መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ እስትንፋስ ነው፤ ቃላት እና ነጥቦች አጠቃላይ በውስጡ ያሉ መገለጫዎች ከእግዚአብሔር የተሰጡ ስለሆነ የእርሱን መገኘት በትክከል መረዳት ማመንም ያስፈልጋል።
2. ሴጣን በሰንሰለት ይታሰራል ካለ መታሰሩንና እስረኛ ሊሆን መቻሉን፣ የኢየሩሳሌም ልኬት 1500 ስኬር ማይል ነው ሲለን በዚያ ልክ ለከተን ለመቀበል መዘጋጀት ተገቢ ነው። ትንቢቶች ሊገጣጠሙ የማይችሉ መስለው ቢታዩ ለጊዜው ነው ግን እግዚአብሔር በታሪክ መደምደሚው አገጣጥሞ ያቀርበዋል ይላሉ።

**ከ.** የዓለም ታሪክም በ7 ስነ መስተዳድራዊ መገለጫ ይከለላል፤ ያም የየራሱን ኪዳን ይይዛል ይላሉ።

1. ንፅህና/Innocency ከፍጥረት መጀመሪያ እስከ ሰው በሀጢአት መውደቅ ድረስ፣
2. ሕሊናዊ/Coscience ከውድቀት እስከ ውሃ ጥፋት (ኖህ) ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሰው ክፉና በጎውን ማወቅ ችሎአል፤ ሕሊናውንምይጠቀማል።
3. መንግስታዊ/Government ከታላቁ የውሃ ጥፋት እስከ ባቢሎን ግንብ ድረስ የሰው ልጅ ስለ መንግስት ያለውን ግንዛቤ ያዳበረበት፣
4. ቃል ኪዳናዊ/Promise ከአባቶች ዘመን እስከ ሙሴ (ከአብርሀም) የጀመረ ነው ህዝቡ ቃል በተገባበት ቦታ በመገኘት የእግዚአብሔርን ተስፋ ያገኘበት፣
5. ሕጋዊ/Lawከሙሴ እስከ ኢየሱስ መወለድ በተመሰረቱ ሕጎች መፅናት። (ሕጉ ተሰጥቷል ተብራርቷል፣ ተተርጉሟል ከመሲሁ መምጣትም ጋር ተጋምዷል)
6. ፀጋ/Grace ክርስቶስ የሰራውን ስራ በማመን በፀጋ መዳንን እና በፀጋ የመኖርን ዘመን ያመለክታል፡- ክርስቲያንና ቤተ ክርስቲያን ያለበት ዘመን።
7. መንግስቱ/Kingdom ኢየሱስ ክርስቶስ ይመለሳል መንግስቱንም ለዘላለም የሚመራበት የአስተዳደር ክልል በመባል ይለያል።

ይህን ክፍፍል አንዳንዶች ወደ 5 ያወርዱታል፤ በዚህ ክፍፍል ውስጥ የተለየ ስፍራ የሚሰጣቸው ሕዝቦች አሉ፤ ሀገርም አለ፤ ያም እስራኤላውያንና እስራኤል ናቸው።

**ጠ.** እስራኤልና ስነመስተዳድሩ/Dispansation

1. እስከ ዘመን መደምደሚያ ድረስ የእግዚአብሔር ምርጥ ህዝቦች ሆነው በመቆጠር ይኖራሉ፤
2. በቅጣት የተበተነው ሕዝበ እስራኤል አሁን አገር ይዞ ተሰባስቧል (ዮሐ 1፡11)፤
3. ሚሊኒየም ወይም ሺህ አመት እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባው ቃል መደምደሚያ ይሆናል በማለት ትኩረት ይሰጡበታል።

**መ.** ቤተ ክርስቲያን በስነ መስተዳደሩ ውስጥ ጊዜያዊ ተቋም ናት፡-





1. ብሉይ ኪዳን ስለ ቤተክርስቲያን ምንም የገለጠው ነገር የለም በዚያም አልነበረችም፤ ዛሬ የተፈለገችው የፀጋ ዘመን መገለጫ ሆና ትቀርብ ዘንድ ነው።
2. ቤተክርስቲያን ከቀደመው ያለፈ ዘመን ወይም ከሚመጣው ከእግዚአብሔር መንግስት ጋር ግንኙነት ወይም ንኪኪ የላትም የቤተ ክርስቲያን ስፍራዋ በገነት ነው፤
3. ትልቁ ተስፋ ሰዎቹ ወንጌልን ሰምተው ክርስቲያን መሆናቸው አይደለም፤ ከዚሁ የበለጠው ተስፋ ክርስቶስ ሲመለስ አይሁዶች በብዙ ቁጥር ወደ ኢየሱስ መመለሳቸው ነው።

**ሠ.** የኢየሱስ መመለስ ቅፅበታዊ/ድንገታዊ ነው።

1. ወደቤት እየሄድን፣ እያመለክን፣ እየበላን፣ እየተዝናናን ሳለ ድንገት ሊመጣ ይችላል፤ ከዚህም የተነሳ ድርሻችን ነቅቶ መጠበቅ ብቻ ነው።
2. በመጀመሪያ አመጣጡ የእርሱ ተከታዮች ብቻ ያዩታል፤ ይገኙበታል፤ ይህም ሚስጢራዊ አመጣጥ ነው።(ማቴ 24፡40-41 1ተሰ 4፡17)፤

**ረ.** ኢየሱስ ለገዛ ልጆቹ በሚስጥር ከመጣ በኋላ ተከታትለው የሚሆኑት፡-

1. ታላቁ መከራ ለ7 አመታት ይሆናል፤ (አንዳንዶች ይህን ለሁለት ይከፍሉታል)
2. በመከራው ዘመን አማኝ የሆኑ አይሁዶች ወንጌልን ይሰብካሉ፤ በሰማይ ክርስቲያኖች ይሸለማሉ፤
3. ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ጋር ለፍርድ ወደ ምድር ይመለሳል፤
4. ሀሰተኛውን ክርስቶስ አጥፍቶ ለ1000 ዓመት በምድር ላይ ይነግሳል፤ ንግስናው በኢየሩሳሌም በሚታይ ሁኔታ ይካሄዳል።
5. ዘላለማዊ መንግስት ቀጣይነት ይኖረዋል።

በስነ መስተዳድር፡- እነዚህ ከላይ የተነሱ መሰረታዊ ነጥቦች በተደጋጋሚ ተነሺ ናቸው። እነህ ጭብጦች ግን ተገቢ በሆነ የታ-ቃ-ስ ስልት ሲጠኑ፣ ሲፈተሹ ምን ያህል አዋጪ ናቸው? ምላሻቸውን መጥነን በተከታታይ እናጤናለን።

ሰባውያን የብሉይ ኪዳን ሕገ ደንብንና የእስራኤልን ሕልውና ከ70 ዓመት ምህረት ጋር በማያያዝ ታሪካቸው ዳግመኛ የማይነሳ ሁነቶች አድርገው ይወስዳሉ፤ ስነ መስተዳድራውያን ደግሞ ለእስራኤል እና ከእስራኤል ጋር ለተያያዙ ትንቢቶች ሰፊ ትኩረት ይሰጣሉ፤ ከዚህምየተነሳ በቀዳሚነት ስለ እስራኤል እናንብብ፡-

## በቀዳሚነት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገለፃን እናስቀድም ስለ እስራኤል ለመነጋገር መነሻችን አብርሀም ነው (ዘፍ 40፡ 15 ዘፀ 2፡11) ከዚያም የልጁ ልጁ የሆነው ያዕቆብን እግዚአብሔር እስራኤል ብሎ ጠራው (ዘፍ 32፡ 28) ከዘሩም 12 ነገድን አወጣ፤ እነዚህ ነገዶች ከዳዊትና ከሰለሞን በኋላ በተፈጠሩ ግጭቶች ሁለቱ ከደቡብ 10 ሩ በሰሜን ከልል በመለየት ራሳቸውን ማስተዳደር ጀመሩ።

የይሁዳ እና የቢኒያም ነገድ፡- ይሁዳ በመባል ሲጠሩ (ኤር 32፡12 2ነገ 16፡6) የተቀሩቱ 10 ደግሞ እስራኤላውያን በመባል ይጠሩ ነበር።

ይህ አኗኗር የሰሜኑን ግዛት አሶራውያን በ722 ዓ.ዓ. ወረው አጓዟቸው ከበርካታ ዓመታት በኋላም ባቢሎናውያን የደቡብን ሕዝብ በማጥቃት ማረኳቸው።

ይህም ኋላ ላይ የሰሜኑ ተበትነው ሲቀሩ የደቡቦቹ ግን ተጉዘው (ተማርከው) ከ70 ዓመታት በኋላ ተመልሰው በክልላቸው መኖር ጀምረዋል (ዳን 9፡2) ከዚያን ግዜ ጀምሮ በከነዐን የሚኖሩት በጥቅሉ ይሁዳውያን/Jewishnation በመባል ተጠሩ (ዮሐ 4፡9 ሐዋ 18፡2)

## በተከታይነት

ሕዝቅኤል 37 ላይ የተዘረዘረውን የትንቢት ቃል ዋንኛ በማድረግ በአሶራውያን ጥቃት ሊጠፉ ያላቸው እስራኤላውያን እንዲሁም በዓለሙ ሁሉ ላይ ተበትነው ያሉ ይሁዳውያን በአንድ ላይ በመሰባሰብ እንደ አንድ ህዝብና በአንድ ንጉስ የሚጠሩበትን ያመቻቻል፤ ከዚያም በሂደት እግዚአብሔር የገባላትን ተስፋ ሁሉ ተቀባይ ሆና ትኖራለች። ያንን ለመፈፀም ለሙታን የእግዚአብሔር መንፈስ ሕይወት መስጠት አለበት፤ ይህም ሆኗል፤ ይላሉ። ይህንንም በተለይ ከ1948 በኋላ ላለችው እስራኤል ሁነኛ መግለጫ መሆኑን ያምናሉ።

## በሦስተኛነት

የእንግሊዝ እስራኤል የግንኙነት መነሻ ነው፤ ይህ ታሪክ መነሻ የሚያደርገው አሶራውያን እስራኤልን





በወረሩ ጊዜ በርካቶች ሸሽተው በልዕልት ታፊ ጁዳ/PrincessTephi Judah መሪነት ወደ እንግሊዝ ሀገር ገብተዋል፤ ይህም ምስራቅ አውሮፓን እና ዴንማርክን እንደመተላለፊያ ተጠቅመው ነው፤ በእንግሊዝ የተገኙት እስራኤላውያን በዚያ መኖርና እምልኮ ማካሄድ ከሕዝቡም ጋር መጋባት ጀመሩ፤ ስደተኞቹ ታቦቱን ይዘዋል፤ ያዕቆብ መታሰቢያ አድርጎ አቁሞት የነበረውን ድንጋይ ሀውልትም ይዘው ነበር (ዘፍ 28፡18) ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የእንግሊዝ እስራኤል ግንኙነት ዘላቂ ሆኖ ቀጥሏል።

ከዚያ በፊት እንግሊዝ ጥቂት ህዝብን የያዘች ሀገር ነበረች ኋላ ላይ ግን ከእነዚህ ፈላሻዎች የተነሳ ስለበዛች እስራኤላውያን እንደሆኑ ይቆጠራሉ ወይም ያምናሉ፤ ይስሀቅ ከደማችን ጋር የተሳሰረ ነው የSaxons – Isaacsons ስያሜም አብሮ ተያያዥነት አለው የያዕቆብ ድንጋይ መለያችን ስለሆነ የኪዳኑ ወራሾች ነን (ዘፍ 49፡24) በማለት የእስራኤል ተዛማጅነትን ያራምዳሉ።

አያይዞም ኢየሱስን የሰቀሉት አይሁዶች እንጂ እስራኤላውያን አይደሉም። እነርሱማ በደስታ ተቀበሉት በራሳቸውም ላይ እንግሰውታል ይህም እኛን ያመለክታል ይላሉ።

እነርሱነታቸውን ከእስራኤል ጋር ለማጣመር ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረውንም ትምህርት በመረጃነት ይጠቅሳሉ፤ ማቴ 10፡5-6 አስራሁለቱ ሐዋሪያት «ወደ አረማውያን አትሂዱ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ ነገር ግን እንደ በጎች ወደ ጠፉት ወደ እስራኤል ሕዝቦች ሂዱ» ማለቱን ማቴ 15፡24 «እርሱም እኔ የተላኩት ከእስራኤል ቤት እንደ በጎች ለጠፉት ብቻ ነው» አላቸው ያለበትን እና፤ በማቴ 21፡43 «... እላችኋለሁ የእግዚአብሔር መንግስት ከእናንተ ተወስዳ ፍሬ ለሚያፈራ ህዝብ ተሰጣለች» የሚለውን እንዲሁም ዮሐ 7፡35 «አይሁዳውያን ባለስልጣኖች እንዲህ ተባባሉ «እኛ እንዳናገኘው ይህ ሰው ወዴት ሊሄድ ነው? ምናልባት በግሪኮች መካከል ወደ ተበተኑት አይሁዳውያን ሄዶ ግሪኮችን ያስተምር ይሆን?» ተባባሉ እነዚህን የመሰሉ ገለፃዎች ለBritish Israllites እንደ እምነት ሆኖ እስከ ዛሬ ያገለግላል።

## አራተኛው

እስራኤልን ከመንፈሳዊ መገለጫ አኳያ መገንዘብ ነው፤ ግልጥ ያሉ አባባሎች፣ አሻሚነት የሌላቸውን ነጥቦች በዚህ ውስጥ አሉ ወይም ይነሳሉ ተብሎ ይታመናል፤ ይህንንም ከኢየሱስ መጀመር ይገባል፤ መንግስቱ ከዚህ ዓለም እንዳልሆነች አስተማረ፤ ይህንንም ዘካሪያስ የእግዚአብሔር ህዝብ አንድ ነገድ ወይም ዘር ብቻ ሳይሆን ሕዝቦች ሁሉ መሆናቸውን አስቀድሞ ከተነበየበት በመነሳት መገንዘብ ተገቢ ነው ዘካ 2፡10-11 መሲሁ በኢየሩሳሌም ሕዝቦች መካከል ይገኝ እንጂ እሱ «የአህዛብ ነገዶች ከእግዚአብሔር ጋር ተባብረው ወገኖቹ ይሆናሉ እርሱም በመካከላቸው ይኖራል» የተባለለት ፍፃሜ ማግኘቱ እስራኤል ተኮር የሆነውን አጀንዳ አስፍተን እንድናስብ ያስገድዳል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል 4:21-24 «አንቺ ሴት ለእግዚአብሔር አብ በዚህ ተራራ ላይ ወይም በኢየሩሳሌም ስለ መስገድ ጉዳይ የማትጨነቁበት ጊዜ እንደሚመጣ እመኚኝ... በእውነትም የሚሰግዱ ለእግዚአብሔር አብ በመንፈስም በእውነትም የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ እንዲያውም አሁን መጥቷል...» የሚለው ገለፃው በተጨማሪም በገላ 4:26 «ከላይ ከሰማይ የሆነችው ኢየሩሳሌም ግን ነፃ ናት እርስዋም እናታችን ናት...» በማለት ከምድር ጋር በተያያዘ ጉዳይ ላይ ማተኮር ሳይሆን ሰማያዊቷ ላይ መታመን መሻሉን መግለፁ፤ እንዲሁም በዕብ 12:22-24 «...እናንተ ግን ወደ ፅዮን ተራራ ቀርባችኋል እርስዋ የሕያው እግዚአብሔር ከተማ የሆነችው ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ናት... ስማቸው በሰማይ ወደ ተፃፈው የቤተክርስቲያን የበኩር ልጆች ወደ ሆኑት ወደ አማኞች ጉባኤ የሁሉ ፈራጅ ወደ ሆነው አምላክም ፍፁምነት ወዳገኙት የፃድቃን ነፍሳት ቀርባችኋል...» በማለት ማብራራቱ እስራኤልን (ኢየሩሳሌምን) ከሰማይቱ ጋር እንጂ ከምድሪቱ ጋር እንዳናስብ ያደርጋል።

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የያዕቆብን ቤተሰብ በመውሰድ እስራኤል ወይም አይሁድ በሚል መጠሪያ የእግዚአብሔር ስራ እንዲሰሩ ተለይተው ነበር፤ ይህም ሙሉ ለሙሉ በእምነት የሆነ እንጂ ሙሉ ለሙሉ ከመውደድ ብቻ ጋር የተያያዘ አልነበረም፤ ዕብራውያን ምዕራፍ 11 ይህን በትክክል ያበስራል፤ የፅድቅን ተስፋ የምንጠባበቀው በእግዚአብሔር መንፈስ አማካኝነትና በእምነት ነው፤ - ምክንያቱም የሚጠቅመን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ስንተባበር በፍቅር አማካኝነት በሥራ ላይ የሚውል እምነት እንጂ መገረዝም ሆነ አለመገረዝ አይጠቅመንም» ማለቱ ከትወልድ እስራኤል ጋር በተያያዘ ብቻ እግዚአብሔር ስራውን የሚሰራ ብቻ ሳይሆን በእምነት መፅደቅን ዋንኛ ያደርጋል።

እስራኤላውያን በመንፈሳዊ ሕይወት የሞቱ ሆነው በነገድ አስራ ሁለት መሆን ግን ከአሶራውያን ወረራ በኋላ ከባቢሎናውያን ምርኮ መልስ በአንድ ላይ በመገናኘት ወይም በየውክልናቸው ለእግዚአብሔር መስዋዕትን በጋራ አቅርበዋል። ይህም ደግሞ እንደ ሆሴዕ አገላለፅ 1:4 «...የእስራኤል መንግስት እንዲያከትም አደርጋለሁ...የልጅህንም ስም «ኢይዝራኤል» ብለህ ጥራው» የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጦት ነበር፤ ይህም በአሶራውያን ተፈፅሟል፤ግና ለዘር የተረፈ የለም ማለት ግን አይቻልም፤ በዕዝራ 7:13 እና 8:35 ላይ ከባቢሎን መልስ በኋላ የሆነው ንጉስ አርጤክስስ ዕዝራን «እኔ በማስተዳድረው የንጉስ ነገስት መንግስት ግዛት ውስጥ የሚገኙና ከአንተ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ የሚፈልጉ እስራኤላውያን፣ ካህናትና ሌዋውያን ሁሉ እንዲመለሱ ፈቅጃለሁ» በማለት የነፃነት አዋጅ አወጣ ከዚያም «እነዚያ ከስደት የተመለሱት ሕዝብ ሁሉ ለእስራኤል አምላክ የሚቃጠል መስዋዕት ሆኖ የሚቀርበውን መባ ሁሉ አምጡ፤- በዚህ ዐይነት በመላው እስራኤል ሕዝብ ስም አስራ ሁለት ኮርማዎችን... እንዲሁም ስለ ኃጢአታቸው ስርየት አስራ ሁለት አውራ ፍየሎች አቀረቡ...» ይላል ይህም የእስራኤልን ሕልውና አመላካች መሆኑን ያሳያል።





እንደ ዮሐንስ 1:13 «እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከሰው ዘር ማለትም ከስጋ ልማድ ወይም ከሰው ፈቃድ አልተወለዱም» በማለቱ እስራኤላዊ በመሆን ለእግዚአብሔር መወለድን ሳይሆን ዳግም በመወለድ ልጅ መሆንን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል፤ እንግሊዞች በመወላለድ የእስራኤል መገለጫ እኛው ነን ማለታቸው አዋጪ ላይሆን ነው፤ እስራኤላዊነት ከእግዚአብሔር የመወለድና የመንፈሳዊ ሕይወት መገለጫ እስካልሆን ድረስ።

በመሰረቱ የኢየሱስን የስቅለት ዘገባ ያቀረበልን ሉቃስ በሐዋሪያት ስራ መጽሐፍ እሱን የሰቀሉት አይሁዶች ሆነው ሳለ እስራኤላውያን በማለት ጠርቷል፤ ተመልሰም አይሁዶችን አካቷል።

ሐዋ 2:23፣26፣14 እንመልከት «...የእስራኤል ሰዎች ሆይ ይህን ቃል አድምጡ እናንተም እንደምታውቁት የናዝሬቱ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ መለኮታዊ ስልጣን ያለው ነው... እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታና መሲህ እንዳደረገው የእስራኤል ህዝብ ሁሉ በእርግጥ ይወቅ...» አለ፤ ይህ አገላለፅ በዚያው ምዕራፍ ቁጥር 14 ላይ ጴጥሮስ... ቆመና... ሕዝቡን...«እናንተ የይሁዳ አገር ሰዎችና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁሉ ይህን የሆነውን ነገር ለማወቅ ንግግሬን ስሙ...» ማለቱ አንባቢ ሁሉ ልብ ሊለው ይገባል፤ ኢየሱስን በመስቀል ሁሉም ሐላፊነት ነበረባቸው፤ ከዚህም የተነሳ እስራኤላውያን ነን ብለው በፅድቅ ለመሞገት የሚያበቃ አቅም የላቸውም።

በተያያዥ መጥምቁ ዮሐንስ በማቴ 3:9 ላይ «እኛ የአብርሀም ልጆች ነን እያላችሁ አትመኩ እግዚአብሔር ከነዚህ ድንጋዮች ለአብርሀም ልጆችን ሊያስገኝለት ይችላል» አላቸው፡- ይህ ገለፃ እስራኤላዊ መሆን አለማስመካቱን ይገልፃል። በማቴ 21:43ም ኢየሱስ «የእግዚአብሔር መንግስት ከእናንተ ተወስዳ ፍሬ ለሚያፈራ ሕዝብ ተሰጥታለች» በማለቱም ከዚህ በኋላ ያለው አጠቃላይ ትኩረት በዘር በዘመድ ባልደረጀው በመሲህይቷ ማህበር በቤተክርስቲያን ይሆናል ማለቱ ነው።

ሐዋሪያው ጳውሎስም መንፈሳዊነት በሀገር፣ በደም፣ ወይም በዘር ሳይሆን በውስጥ ልደት መሆኑን አብስሯል፤ ይህም እስራኤልን በአካላዊ ገፅታው ሳይሆን በመንፈሳዊ እይታው መረዳት ሳይሻል አይቀርም፡- ሮሜ 2:28-29 «እንግዲህ በስም ብቻ አይሁዳዊ የሆነ እውነተኛ አይሁዳዊ አይደለም እንዲሁም በውጭ የሚታይ የስጋ መገረዝ እውነተኛ መገረዝ አይደለም» በማለት አብስሯል።

ጳውሎስ በገለፃው የራሱ አይሁዳዊ (ዕብራዊነት፣) የአብርሀም ዝርያ መሆን ምንም ዋጋ እንደሌለው ሲገልፅ «እነርሱ ዕብራውያን ናቸው? እኔም ዕብራዊ ነኝ እነርሱ እስራኤላውያን ናቸውን? እኔም እስራኤላዊ ነኝ። እነርሱ የአብርሀም ዘር ናቸውን? እኔም የአብርሀም ዘር ነኝ....እያለ 2ቆሮ 11:22

ካብራራ በኋላ በአዲሱ ኪዳን እነዚህ ሁሉ መመኪያዎች አለመሆናቸውን አስተማረ።

በመጨረሻም ጴጥሮስ በማያወላውል ሁኔታ ኢየሱስ የመሰረተው ማህበር ሁሉን አቀፍ መሆኑን ሲገልፅ 1ጴጥ 2:5-10 «...እናንተ ግን ከጨለማ ወደ ሚያስደንቅ ብርሀን የጠራችሁን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ሥራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ፤ የንጉስ ካህናት፤ እግዚአብሔር ለራሱ ያደረጋችሁ፤ ቅዱስ ሕዝብ አልነበራችሁም፤ አሁን ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ ናችሁ ቀድሞ ምህረት አላገኛችሁም ነበር፤ አሁን ግን ምህረት አግኝታችኋል» አለ።

ይህ ገለፃ ልበ ሰፊነትን በሥጋ ለተወለዱ እስራኤላውያን መስጠት አዋጪ እንዳልሆነ ይጠቁማል፤ ስነ መስተዳድራዊ ግንዛቤ (እምነት) ግን ከነዚህ በበለጠ የእርሱ ምርጫ ቀዳሚ፤ ቃሉንም በቀጥታ መውሰድ ተገቢ ነው፤ በማለት አፍቃሪ እስራኤል የመሆን ዝንባሌን ይፈጥራል።

## ትንሳኤ እና የዳግም መመለስ ይዘት

እንደ ሰባውያን ግንዛቤ ኢየሱስ በ70 ዓ.ም ቢመጣም እንደ ስነመስተዳድራውያን ኢየሱስ ገና ወደ ፊት ሊመጣ ያለው ቢሆንም በሁለቱም ተንታኞች ዘንድ **«ትንሳኤ»** የራሱን ገለፃ ይዞ ይገኛል።

ትንሳኤ ያለ ልዩነት መደብን፣ ፆታን፣ ሁኔታዎችን፣ ሳያማክል በጌታ በሆኑ እና ባልሆኑ ሁሉ ላይ የሚገለፅ ክስተት ነው፤ በሰባውያን ትምህርት ላይ ትንሳኤ ከመንፈሳዊ ሙትነት በመነሳት ሕያው መንፈስን ማግኘት ወይም ዳግም መወለድ በብቻው ትንሳኤ ነው።

ስነ መስተዳድራውያን የጌታ ዳግም መመለስ ማረጋገጫው የቅዱሳንም ሆነ የሀጥአን በአካል መነሳት መሆኑን ያሳውቃሉ፤ ግና ከሁለቱም አካሄድ ወጣ ብሎ ለማየት 66 ቱን ቅዱሳት መጽሐፍት በየአውዶቻቸው ያሉትን፣ የፃፉትን፣ ማጥናት ያስፈልጋል። እንግዲያስ የትንሳኤ ፍቺ ምን ሊሆን ይችላል? ትንሳኤ «መነሳት ለመቆም ብቃት ማግኘት ሕያው መሆን ማለት ነው» ይኸው ገለፃ ሞተው የነበሩ እንደገና በሕይወት ቢገኙ እነርሱ የዚህ የትንሳኤ መገለጫ ይሆናሉ።

ለዚህም ደግሞ ኤልያስ 1ነገ 17:21-22 *«ኤልያስ በሞተው ልጅ ላይ ሦስት ጊዜ ተዘርሮ «እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ እባክህ ይህን ልጅ ከሞት አስነሳው» ሲል ፀለየ እግዚአብሔርም የኤልያስን ፀሎት ሰማ የልጁም እስትንፋስ እንደገና ተመልሶለት ዳነ... ወስዶም ለእናቱ ሰጣት»* ይላል

የኤልሳዕ በድን በመቃብር ነበር፤ ግና ቀባሪዎቹ ወንበዴዎችን ፈርተው እያለቀሱ ይሸኙት የነበረውን አስከሬን ጥለው ሸሹ ሲጥሉ ግን ሳያውቁ ያነካኩት ከኤልሳዕ መቃብር ላይ ስለነበረ ማቹ ተነስቶ ቆመ 2ነገ 13:21 *«...ያም ሬሳ ከኤልሳዕ አስከሬን ጋር በተገናኘበት ቅፅበት ወዲያውኑ ከሞት*





*ተነስቶ ቆመ»* በማለት ሕያውነቱን አረጋገጠ።

በማቴዎስ ወንጌል 9:25-26 የምኩራብ አለቃው ልጅ ሞታ ነበር፤ ኢየሱስ አንቀላፍታለች ቢላቸውም እንኳን አላመኑም መሞቷ እርግጥ ስለነበረ እሱ ግን «...*እጅዋንም ሲይዛት ተነሳች የዚህም ነገር ዝና በዚያ አገር ሁሉ ተሰማ»* ይላል።

ሉቃ 7:15 «በናይል የአንዲት መበለት ልጅ ሞቶ ነበር፤ በዚህ ግዜ ኢየሱስ አንተ ወጣት ተነሳ እልሀለሁ» አለ፤ የሞተው ቀና ብሎ ተቀመጠና መነጋገር ጀመረ ከዚያም በኋላ ኢየሱስ ለእናትየዋ «እነሆ ልጅሽ ብሎ ሰጣት»።

የአላዛርም ጉዳይ ተመሳሳይ ነው። በዮሐንስ 11:43-44 «አልአዛር ና ውጣ» ብሎ ተጣራው ማቹም እጆቹና እግሮቹ በመገነዣ እንደተገነዙ ከመቃብር ወጣ ፊቱም በጨርቅ እንደተጠመጠመ ነበር፤ ኢየሱስም «ፍቱና ተዉት ይሂድ» አላቸው እነዚህን የመሰሉ ከሞት በአካል የመነሳት ታሪኮች በተጨማሪም ከደርብ ወድቆ በሞተው እና በተነሳው በሐዋ 20:9 እንዲሁም ሐዋ 9:40 ከዶርቃ ጋር የተያያዙት ታሪኮች ሁሉ ተመሳሳይ ገለፃ አላቸው፤ ከነዚህ ሁሉ የትንሳኤ ገለፃዎች ከፍ ብሎ የሚታሰበው ግን የራሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት በአካል መነሳቱ ነው፤ ጳውሎስ ይህን በሐዋ 26:23 ላይ ሲተርከው «መሲህ መከራ ይቀበላል፤ ከሞት በመነሳትም የመጀመሪያ ሆኖ የደህንነትን ብርሀን ለእስራኤል ሕዝብና ለአረማውያን ይገልጣል» የሚለውን ምስክርነት አቀረበ።

የኢየሱስ ትንሳኤ ከሙታን በኩር የመሆን መገለጫ ስላለውና በእርሱ የሆኑ ሁሉ ፈለጉን የተከተለ ትንሳኤ እንደሚገጥማቸው የቆሮ 15:20-23 ገለፃ ያበስራል፤ ከፍሉ «...*ነገር ግን ክርስቶስ ለሞቱት ከሞት የመነሳት የመጀመሪያ ምሳሌ ሆኖ በእርግጥ ከሞት ተነስቷል፤ ሞት የመጣው በአንዱ ሰው በአዳም ምክንያት እንደሆነ ከሞት መነሳትም የሚመጣው በአንዱ ሰው በክርስቶስ ምክንያት ነው። በአዳም ምክንያት ሰው ሁሉ እንደሚሞት እንዲሁም በክርስቶስ ምክንያት ሰው ሁሉ ሕይወትን ያገኛል ይህም የሚሆነው በየተራ ነው፤ ክርስቶስ ከሞት የመነሳት የመጀመሪያው ምሳሌ ነው በኋላም ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ የእርሱ የሆኑት ከሞት ይነሳሉ...»* ይላል።

ይህ አነሳሳቸው ከኢየሱስ ትንሳኤ ጋር መቀራረብ አለው። ከዚህም የተነሳ ኢየሱስ በአካል እንደነበረ የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ፃፈልን፤-ኢየሱስ

- ማቴ 28:9 በንግግር በቃል፣ ራሱን ይገልፁ ነበር፣
- ሉቃ 24:15 ይራመድ ነበር፤

*ዮሐ 11:24 በመጨረሻው ቀን በትንሳኤ ጊዜ ከሞት እንደሚነሳ ዐውቃለሁ አለችው።*

*ሐዋ 4:2 ሁለቱ ሐዋሪያት የኢየሱስን ከሞት መነሳት በማስተማራቸውና በዚህም የሙታን ትንሳኤ መኖሩን በማስረዳታቸው ተቆጡ...።*

*2ቆሮ 4:14 ጌታ ኢየሱስን ከሞት ያስነሳ አምላክ እኛንም ከኢየሱስ ጋር እንደሚያስነሳንና ከእናንተም ጋር በፊቱ እንደሚያቀርበን እናውቃለን።*

*ራዕ 20:5-6 የመጀመሪያው ትንሳኤ ተካፋይ የሆኑ የተመሰገኑና ቅዱሳን ናቸው።*

በአጠቃላይ እነዚህን ክፍሎች የሞቱ በአካል መለሳታቸውን ያረጋግጣሉ። ከትንሳኤም በኋላ አንዱ ሌላውን ሊለየው የመቻል አቅም እንዳለው ጴጥሮስ በደብረዘይት ተራራ ላይ ሙሴን ለይቶ ለማወቅ መቻሉን እንደ ሁነኛ መረጃማንሳት ይቻላል።

## ፀረ የአካል ትንሳኤ አቋም

ከላይ የተዘረዘሩትን መረጃዎችንና የአካል ትንሳኤን እንደማይኖርና እንደማይሆን የሚያስተምሩ የስነ መለኮት መምህራን አሉ፤ ከእነርሱ መሰረታዊ ምክንያት ውስጥ ጥቂቱ:-

**ሀ.** ሰዱቃውያን፣ የግሪኮችንና የሮማውያንን አስተሳሰብና ዕውቀት በጊዜው ይጋሩ ስለነበረ ትንሳኤ በመኖሩ አያምኑም፤ ከዚህም የተነሳ በማቴ 22:23 «በትንሳኤ ጊዜ ለማንኛቸው ሚስት ትሆናለች?» የሚል ጥያቄ ይዘው መጡ፤ ሐዋ 23:8 የአካል ትንሳኤ የለም አንዱ እምነት ሆኖ ቀርቦ ነበር።

**ከ.** ፍልስፍና፣ ፈላስፎች የአካል ትንሳኤን እንደ «ፌዝ» ይቆጥሩታል፤ ለዚህም ሐዋ 17:18,32...ፈላስፎችም ወደ እርሱ እየመጡ ይከራከሩ ነበር... ይህ ለፍላፊ ምን ማለት ይፈልጋል? አሉ...ይህንንም ያሉበት ምክንያት ጳውሎስ የኢየሱስን የትንሳኤውን መልካም ዜና ስላበሰረ ነው...» እነርሱ...«ከሞት መነሳት» የሚለውን ቃል በሰሙ ጊዜ አንዳንዶች አፌዙበት ሌሎች ግን «ስለዚህ ጉዳይ ስትናገር ሌላ ጊዜ እንሰማለን» አሉት። ይላል። በዚህ ገለፃ መሰረት ትንሳኤ አለ ብሎ ማመን ጅልነት ነው፤ አእምሮን ማሰራት የቻለ እና አመክኖአዊ አቋም ያለው የትኛው ሰው የፈረሰ እና አመድ የሆነ ነገር ሕያው ሆኖ ማንነቱን በመጠበቅ ትንሳኤ እያገኝም የሚለው ግንዛቤ የፈላስፎች እና የሰዱቃውያን አቋም ነበር።

**ጠ.** ስንሞት በቀጥታ ወደጌታ ገቢ ነን፤ ከዚህም የተነሳ የአካል ትንሳኤን የምንመኝበት





ወይም የምንጠብቅበት ምንም ምክንያት የለም የኢየሱስ ትንሳኤ ለዚህ እምነታችን መሰረትን ጣይ ነው። እናም በአካል ስንሞት በቅፅበት ጌታ ባለበት እንሆናለን ይህ ገለፃ አግባብ ቢሆንም ግና የአካል ትንሳኤን ቸል በማለቱ ይወቀሳል። ጳውሎስ ግን ለዚህ ግንዛቤ በ1ቆሮ 15:12-13 ነገር ግን ክርስቶስ ከሞት እንደተነሳ የምናስተምር ከሆነ ከእናንተ አንዳንዶቹ «ከሞት መነሳት የለም» እንዴት ይላሉ ከሞት መነሳት ከሌለማ ክርስቶስ ከሞት አልተነሳም ማለት ነዋ!» በማለት በቃለ እግዚአብሔር ይቃወማል።

**መ.** ትንሳኤ ለአማኞች ብቻ ነው፤ ይህም ትንሳኤ ክርስቶስን ሰዎች ባመኑ ጊዜ ከሙትነት ወደ ሕያውነት የተሸጋገሩበት ቅፅበት ነው፤ ያለዚህ ትንሳኤ ድነት የለም፤ ከዚህ የበለጠ እና በአካል የሚገለፅ ትንሳኤም የለም የሚለው ሙግትም ከቅድመ ውሳኔ ጋር በማጣጣም የእርሱ የሆኑ ምርጦች ኢየሱስ ስራውን ጨርሶ በአብ ቀኝ ሲቀመጥ እነርሱ ሁሉ ከእርሱ ጋር ተሰውረው ስላሉ ድርጊቱ «ድሮና ዘንድሮ» ነው፤ ይላሉ ይህ ግንዛቤ ግን ጥንትም መኖሩን ጳውሎስ ሲገልፅ ሄርሜኒዮስና ፊሊጦስ እንዲህ ያስተምሩ ነበር «የሙታን ትንሳኤ ገና ድሮ ሆኖአል እያሉ በመከራከር ከእውነት መንገድ ወጥተዋል። የአንዳንዶችንም ሰዎች እምነት ያናውጣሉ» ያለበትን ማስተዋል ተገቢ ነው።

እንግዲህ እነዚህ ከ«ሀ» እስከ «መ» የአካል ትንሳኤ የሌለ ያህል ለማስቆጠር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ናቸው።

ስነ መስተዳድራውያን ከሰባውያን በትንሳኤ ጭብጥ ላይ ይለያያሉ፤ ሰባውያን የሰው ዳግም የመወለድ ቅፅበትን ትንሳኤ ብለው ሲጠሩና ሲያምኑ ስነ መስተዳድራውያን ግን ዳግም ልደትን የተካፈሉም ሆኑ ያልተካፈሉ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ግዜ እነርሱን ከሙታን ዓለም በማስነሳት እና አካል በመስጠት እንደሚያኖራቸው ያምናሉ።

በተያያዥ ስነ መስተዳድራውያን እስራኤልን ማዕከል አድርገው ዘላቂ የስነመለኮት ትምህርት አደርጅተዋል፤ ቤተክርስቲያንንም ጊዜያዊ ተቋም በማድረግ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለውን ቃል ኪዳን ለዘላለም እንደሚጠብቅ ያምናሉ ግና እስራኤልን ከመጨረሻው ዘመን ጋር ሲያስተሳስሯት ኢየሱስ ዳግም በአካል ከመመለሱ በፊት በኢየሩሳሌም በሚሰራው ቤተመቅደስ እንደገና የብሉይ ኪዳን ስርዓት እንደሚካሄድ አጥብቀው ያስተምራሉ።

በቀለ ወልደኪዳን «ከሌሊቱ ስንት ሰዓት ነው?» በማለት በ2003 ባሳተመው መፅሐፍ ይህው ሊሆን በጣም ቅርብ መሆኑን አመላክቷል (በቀለ <u>ከሌሊቱ ስንት ሰዓት ነው?»</u> ገፅ 181-185)

በዚህ ጉዳይ ሊታሰብበት የሚገባ ነጥብ አለ፤ ቤተመቅደስ ሊሰራ ወይም ሊገነባ የማያስችል

መግለጫዎችን የእግዚአብሐር ቃል አስፍሯል፤

*ማቴ 12:6 ኢየሱስን በተመለከተ «ነገር ግን ከቤተመቅደስ የሚበልጥ እነሆ እዚህ አለ እላችኋለሁ...»*

*ማቴ 24:1-2 ቤተመቅደሱንም አይቶ «...ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተነባብሮ ሳይፈርስ የሚቀር የለም» አላቸው።*

*ማቴ 26:61 ይህ ሰው «የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ አፍርሼ በሦስት ቀን ልሰራው እችላለሁ» ብሎአል ሲሉ ተናገሩ (ዮሐ. 2:19)*

*ማር.15:38 «...የቤተመቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተቀዶ ለሁለት ተከፈለ...»*

*ሐዋ 7:48 «ሆኖም ልዑል እግዚአብሔር በሰው እጅ በተሰራ ቤት ውስጥ አይኖርም...»*

*ሐዋ 17:24 «...እርሱ ዓለምንና በዓለም ያለውንም ሁሉ የፈጠረ ነው፤ የሰማይና የምድርም ጌታ ነው፡ እርሱ በሰው እጅ በተሰራ ቤተ መቅደስ አይኖርም...»*

*1ቆሮ 6:19 «ሰውነታችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁትና በውስጣችሁም የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ መሆኑን ታውቁ የለምን?»*

*2ቆሮ 6:16 «.የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ከጣዖት ጋር ምን ስምምነት አለው... እኛ የህያው እግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነን።»*

*ኤፌ 2:11-22 «.በሐዋሪያትና በነቢያት መሰረት ላይ ታንፃችኋል... እናንተም እግዚአብሔር በመንፈሱ የሚያድርበት ሕንፃ ለመሆን በክርስቶስ ትታነፃላችሁ።»*

*ዕብ 3:6 «...ቤቱም እኛው ነን፤-ቤቱ የምንሆነውም የምንተማመንበትን ነገርና የምንመካበትን ተስፋ አፅንተን ብንይዝ ነው...»።*

*1ጴጥ 2:5 «ወደጌታ ኢየሱስ የምትቀርቡትም እንደ ሕያዋን ድንጋዮች መንፈሳዊ ቤት ሆናችሁ ለመታነፅ ነው»*

*ራዕ 21:22 «...ሁሉን የሚችል ጌታ አምላክና በጉ የእርሰዋ መቅደስ ስለሆነ በከተማይቱ ውስጥ መቅደስ አላየሁም»*





ከላይ የተዘረዘሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ልብ ላለና የዕብራውያንን መጽሐፍ ያጠና ማንም ወደፊት ሦስተኛው ቤተ መቅደስ ይሰራል በማለት ተስፋ አያደርግም፤ እግዚአብሔር የድነት መንገድን እስካልቀየረ የመሲሀይቷ ሕብረተሰብ ማንነት በአረጀውና ባፈጀው የቀደመው ኪዳን ሳይሆን በክርስቶስ ላይ የተመሰረተ እስከሆነ ድረስ ስነመስተዳድራውያን አቋዋማቸውን እንደገና ማጤን ይጠበቅባቸዋል።

## መጥራት ያከበት ኬካው ገፅታ

ሰባውያን ማቴ 24ን በሙልዐት ከ70 ዓመተ ምህረት ጋር ተጠናቋል። የሚል አቋም በመያዛቸው:- የኢየሱስ በግልም ሆነ በስውር መምጣት ከግምት አይገባም፤ በስነ መስተዳድራውያን ዘንድ ግን ከመከራው በፊት በስውር መጥቶ ቤተ ክርስቲያኑን ይወስዳል ከዚያም ከ7 ዓመት በኋላ ዳግም በመመለስ ፍርዱን ይገልፃል የሚሉት ሁለት ጫፎች የየራሳቸው ሕፀፆች አሏቸው፤ በመሰረቱ ከፍት ሆኖ የተተወ አስተምህሮ ከመሆኑ የተነሳ እና የሰው ልጅ የነገን መልክ ለማወቅ ጉጉ ስለሆነ በኢየሱስ መመለስ ላይ የጊዜን ተመን በመቁረጥ ተደጋጋሚ ሙከራ ማድረጉ አይዘንጌ ነው።

በ1914እ.ኤ.አ. የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በጀመረበት ጊዜ ኢየሱስ ይመጣል ተብሎ ነበር፤ ግን አልመጣም፤ በ1923እ.ኤ.አ.ም ተመሳሳይ ጥበቃ ተደርጓል ግን አልሆነም፤ በግንቦት2011እ.ኤ.አእንዲሁ የኢየሱስ መምጣትን በማመላከት ጥበቃ ተካሂዷል ግን ኢየሱስ አልመጣም። ይህ የሆነበት ዋንኛ ምክንያት የምልክቶች ተፈፃሚነት መጨመርን ከግምት በማስገባት አልያም የሰው አለመርካትና የዓለም ፍፃሜን ይዞታ ለማወቅ ያለው ጉጉት ጠንክሮ መዝለቅ ያስከተለው ጫና ሊሆን ይችላል።

ለማንኛውም «ኢየሱስ ዳግም መጥቷል? ወይ ኢየሱስ ዳግም ይመጣል» በማለት መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት አድርጎ እንደገለጠው ከአውዳዊ ትርጉም አኳያ አብረን እንፈትሽ።

እንደ ሩሽ ወርዝ ጥናት ጉዳዩን ከሦስት መድቦ መመልከት ያስፈልጋል/RushWorth Smith The final return of the Lord Jesus 1990 P.51።

### ምድብ አንድ

### «ኢየሱስ ሁሌ ጊዜ ይመጣል፤ ዛሬም ይመጣል»

ኢየሱስ ባላመኑት አይሁዶች ላይ በ70 ዓ.ም መጥቷል፤ በፍርድም በመገናኘት ድምጥማጣቸውን በማጥፋት «እፎይታ» አግኝቷል። በዚህም የእግዚአብሔርን መምጣት ከፍርድ ጋር በማገናኘት መተርጎም መቻሉን ያመላክታል። በተመሳሳይ አካሄድ የጌታ መምጣት ለበረከት፣ ለተሀድሶ ለከፍተኛ

ንቅናቄ ምክንያት በመሆን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ብዙዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት በመግባት የእርሱ ሆነዋል።

ዮሐ. 14፡17-18 እንዲሁም ራዕይ 3፡20 «እርሱም የእውነት መንፈስ ነው፤ ዓለም ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው አይችልም፤ እናንተ ግን አብሮአችሁ ስለሚኖርና በውስጣችሁም ስለሚሆን ታውቁታላችሁ። ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም ወደ እናንተ እመጣለሁ...» «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ሰምቶ በሩን ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ ገብቼ ከእርሱ ጋር እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል» እንዲሁም «ሁለት ወይም ሶስት ሆናችሁ በስሜ በተሰበሰባችሁት ስፍራ ሁሉ እኔ በመካከላችሁ አለሁ» የሚለው ቃል ኢየሱስ ሁል ጊዜ ሊመጣ አብሮን ሊሆን፣ አብሮን ሊሰራ እንደሚችል ያስረዳል።

**ምድብ ሁለት**

**«መምጣትን በተለያዩ አገላለጦች ማሳየት»**

ኢየሱስ እየመጣ ነውንና ይመጣልን ለማብራራት የጊዜ አጠቃቀም ከግምት እንደሚገባ ሁሉ መምጣትን አመልካቹ የተለያዩ ገለጣዎችን መጠቀምን በአግባቡ በማጤን ምድብ ምድባቸውን መለየት ተገቢ ነው።

ሀ. 1ጢሞ. 6፡14 «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገለጥ ድረስ ይህን ትዕዛዝ ያለ ዕድፍና ያለ ነቀፋ ሆነህ ጠብቅ» (Appearance)

ለ. ማቴ 24፡27 «መብረቅ ከምስራቅ ወጥቶ ምዕራብ ድረስ እንደሚያበራ የሰው ልጅ አመጣጥም እንደዚሁ ይሆናል» (Presence)

ሐ. 2ተሰ 1፡6-7 «እግዚአብሔር ፃድቅ ስለሆነ መከራን ለሚያመጡባችሁ መከራን ይከፍላቸዋል መከራን ለተቀበላችሁት ለእናንተም ሆነ ለእኛ ደግሞ ዕረፍት ይሰጠናል፤ ይህም የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ በሚንበለበል እሳት ከኃያላን መላዕክት ጋር ከሰማይ በሚገለጥበት ጊዜ ነው።» (Revelation)

መ. 2ተሰ 2፡2 «በመንፈስ መገለጥ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደተላከ መልዕክት የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ ፈጥናችሁ ከአእምሮአችሁ አትናወጡአትደንግጡ...» (The Lord's Day)

ሠ. 1ቆሮ 15፡23 «ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል መጀመሪያ በኩራት የሆነው ክርስቶስ ከዚያም በኋላ እርሱ ሲመጣ የክርስቶስ የሆኑት ከሙታን ይነሳሉ» (መምጣቱ ሲሆን/Coming)





ከላይ በተዘረዘሩት መገለጫዎች የኢየሱስን መመለስ በተለያዩ የቃላት አጠቃቀምን እና ሁኔታዎችን በማከል ቅዱሳን ፀሐፊያን በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው መፃፋቸውን ልብ ልንል ይገባል።

**ምድብ ሶስት**

**«የስውሩ እና የግልፁ መገለጥ ምንነት»**

ቅዱሳን መጽሐፍት ኢየሱስን በተመለከተ በስውር የሚመጣ አስመስለው ተናግረዋል፤ በተይዩም በግልፅ አይታም መምጣቱን የሚያውጁ በርካታ ክፍሎች አሉዋቸው። ግና ከሁለቱ ደምቆ እና ትኩረት ተሰጥቶት የተላለፈው ምልክት የትኛው ይሆን?

ራዕ 1፡7 «እነሆ በደመና ይመጣል፤ የወጉት እንኳ ሳይቀሩ ዐይን ሁሉ ያየዋል፤ የምድርም ህዝቦች ሁሉ ከእርሱ የተነሳ ዋይ ዋይ ይላሉ አዎ ይህ ሁሉ ይሆናል» አሜን።

ይህ አገላለፅ አለምአቀፍ ገፅታ አለው፤እይታው ለሁሉም መሆኑን ያመለክታል በተያያዥም ሐዋሪያው ጳውሎስ በ1ኛ ተሰ 4፡17-18 «...እኛ የቀረነው በሕይወትም የምንኖረው ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን በዚህም መሰረት ለዘላለም ከጌታ ጋር እንሆናለን ስለዚህ በዚህ ቃል እርስ በርሳችሁ ተፅናኑ» ይላል።

ይህ አባባል አማኞች እሱን ለመቀበል ወደሚመጡበት አቅጣጫ ሲሄዱ እሱም በመምጣት መሀል ላይ ይገናኛል እንደ ማለት ነው፤ ይህም ስውር አመጣጥን ሊያመላክት ይችላል፤ በዚህም ከማቴ24፡40-41 አንዱ ይቀራል ሌላው ይወሰዳል ጋር ሊቀራረብ ይችላል።

እንግዲያስ ሁነቶቹ እንዴት ይጣጣሙ!

ስነ መስተዳድራዊ አቋም ያላቸው ሁለት መምጣቶች መኖራቸውን በማወቅ ይፀናሉ፤ ዕናቱ ግን የሚሸበርከው በስውር ኢየሱስ አማኞችን ሲወስድ የቀረው ዓለም ከአማኞች መወሰድ የተነሳ እና ከሰባት አመት በኋላ ዳግመኛ ሊመለስ እንደሚችል መታወቁ «የመምጫውን ጊዜ ማንም ሊያውቅ አይችልም» የተባለበት መለኪያ ያከሽፋል። ይህ ደግሞ ምላሽ አልባው ፈተናው ነው።

## በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መመለስ ላይ መመካከር የሚያመጣው ጥቅም እና ጉዳት

### ጥቅም አንድ:- ጉጉት

**መጓጓት**:- መጠባበቅን ይዞ የሚገኝ ቃል ነው፤ የሚጠበቀውም ሊጠቅመን አቅም ያለው ስለሆነ ነው።

ማቴ 24፡44 *«የሰው ልጅ ባላሰባችሁት ሰዓት ይመጣልና ዝግጁ ሁኑ»*

ሉቃ 12፡34-40 *«ልባችሁ ንብረታችሁ ባለበት ቦታ ነውና ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ»*

1ቆሮ 1፡7 *«የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ በጉጉት በመጠባበቅ ላይ ሳላችሁ ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታ አይጎድልባችሁም።»*

ቲቶ 2፡13 *«ይህም የተባረከ ተስፋችን የሆነውን የታላቁን የአምላካችንንና የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ በመጠባበቅ ነው።»*

### ጥቅም ሁለት:- ደስታ (ፈንጠዝያ)

በሰው ኑሮ ውስጥ ከሚፈለጉ የሕይወት ማጣፈጫዎች ውስጥ ደስታ ዋንኛው ነው፤ መደሰት ቋሚ እና ፅኑ «ነገርን» በማግኘት ሲገለጥ እና በግላችንና በጋራ ተጠቃሚ ስንሆንበት የሚገኝ እርካታ ነው። በዚህም:-

ሀ. የቃሉ እውነት መሆን ተፈፃሚነቱ ያስደስታል፤

ለ. ከአዳኝን ጌታ ጋር ለዘላለም መሆን ያስቦርቃል፤

ሐ. የጉስቁልና መንስኤዎች ሴጣንንም ጨምሮ መወገድ ያስደስታል።

ራዕ 19፡7 «የበጉ ሰርግ ስለደረሰ...ደስ ይበለን ሐሴት እናድርግ።»

ራዕ 20፡10 «ያሳታቸው ዲያብሎስ፣ አውሬውና ሀሰተኛው ነብይ ወዳሉበት... ሴጣን ተጣለ»

### ጥቅም ሦስት:- ተስፋ

ሰዎች ያለምግብ በርካታ ቀናት ያለውሃ ጥቂት ቀን ይኖራሉ፤ ያለ ተስፋ ግን ለአፍታም መኖር አይችሉም፤ ክርስትና በፅኑ ተስፋዎች የተሞላ ነው፤ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር እነዚህ ነዋሪዎች መሆናቸውን ሐዋሪያው ገልፁዋል። በ1ኛ ጴጥ 1፡13 ስለዚህ ልባችሁን አዘጋጁ፤ ራሳችሁንም ግዙ





ተስፋችሁን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለእናንተ በሚሰጠው ፀጋ ላይ ሙሉ ለሙሉ አድርጉ።

1ዮሐ 3፡2-3 እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለን፤ እርሱን እንደምንመስልም እናውቃለን፤ በእርሱ ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንፁሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነፃል።

### ጥቅም አራት:- ንቁነት- ቅንነት

የክርስቶስ የሆነው ማህበረሰብ የሚገጥመው ጥቃት ብዙ ዐይነት ነው፤ ችግሮች ከቤተክርስቲያን ይወጣሉ፤ ከውጭም ወደ ውስጥ ይገባሉ፤ የሁሉም አመጣጥ ማታለል አለበት፤ በዚህ ወቅት መፍትሄው ንቁ መሆን ብቻ ነው።

ማቴ 24፡4 ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ...ብዙዎችንም ያስታሉ።

1ጴጥ 4፡7 የሁሉ ነገር መጨረሻ ተቃርቦአል፤ ስለዚህ መፀለይ እንድትችሉ ንፁህ አእምሮ ይኑራችሁ ራሳችሁንም የምትገዙ ሁኑ።

### ጥቅም አምስት:- ዝግጁነት

ዝግጁነት ብዙ ነገሮች በውስጡ አሉት፤ አቅምን ማደርጀት፣ ሀላፊነትንና ተጠያቂነትን ማሟላት እንዲሁም ለታለመለት ግብ መጓዝን በውስጡ ይይዛል፤ ይህም የጌታን ዳግም መመለስ በመጠባበቅ ይገለጣል።

ማቴ 22፡11 *«ንጉሱ...የሰርግ ልብስ ያልለበሰውን አየ...»*

ማቴ 24፡44 *«የሰው ልጅ ባላሰባችሁት ሰዓት ይመጣልና እናንተም እንደዚሁ ዝግጁሁኑ»*

1ዮሐ 2፡28 *«እርሱ ሲገለጥ ድፍረት እንዲኖረን በሚመጣበትም ጊዜ በፊቱ እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ።»*

### ጥቅም ስድስት:- ትዕግስት

ትዕግስት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው፤ የዚህ ባለቤት ለመሆን በቃሉ መታመንና የሚመጡ ተከታታይ ፈተናዎችን በመቋቋም በእግዚአብሔር ላይ የመፅናት መገለጫ ነው።

1ቆሮ 4፡5 *በእኔ ላይ የሚፈርድ ጌታ ነው፤ ስለዚህ ጊዜው ሳይደርስ በምንም ነገር አትፍረዱ ጌታ እስኪመጣ ጠብቁ።*

ያዕቆብ 5፡8 *እናንተም እንዲሁ ታገሡ፤ ልባችሁንም አፅኑ ምክንያቱም የጌታ መምጫ ተቃርቦአልና...*

**ጥቅም ሰባት: አገልጋይነት**

ሉቃ 12፡35-38 *«...ጌታው ሲመለስ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው አገልጋይ እርሱ ብፅህ ነው»*

ዮሐ 9፡4 *«ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ መሥራት አለብኝ...»*

**ጥቅም ስምንት ራስን መግራት**

1ተሰ 5፡4-8 *«እንግዲህ እንንቃ ራሳችንንም እንግዛ እንጂ እንደሚያንቀላፉት... እንሁን»*

1ጴጥ 1፡13 *«ስለዚህ ልባችሁን አዘጋጁ፤ ራሳችሁንም ግዙ፤ ተስፋችሁን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ በእናንተ በሚሰጠው ፀጋ ላይ ሙሉ ለሙሉ አድርጉ»*

እነዚህ ክፍሎች ራስን በመግራት ለውጤት የሚበቁ ናቸው፤ የግባቸው መነሻ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን በመጠባበቅ ይመጣል፤

**ጥቅም ዘጠኝ:- ክርስቶስን መስሎ መኖር**

ፊሊ. 4፡5 *«ገርነታችሁ በሁሉ ዘንድ የታወቀ ይሁን ጌታ ቅርብ ነው»*

1ተሰ 5፡23 *«የሰላም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁን፤ ነፍሳችሁንና ሥጋችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ያለነቀፋ ይጠበቁ»*

1ጢሞ 6፡14 *«ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገለጥ ድረስ ይህን ትዕዛዝ ያለ ዕድፍና ያለ ነቀፋ ሆነህ እንድትጠብቅ ነው»*

1ዮሐ 3፡3 *«በእርሱ ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንፁህ እንደ ሆነ ራሱን ያነፃል»*

ከላይ የተዘረዘሩት ዘጠኝ ያህል ጥቅሞች ከኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት ጋር በመያያዛቸው ክርስቲያኖች ተስፋቸውን በፅናት ይጠብቁበታል፤ ግብ ተኮር ሕይወት ይኖሩበታል፤ እያንዳንዱን ሰከንድ ውጤታማ ለሆነ ተግባር ያውሉበታል።





ክርስትና በእምነት፤ በተስፋ እና በፍቅር የተገለጠ እምነት ነው። የዚህ ውጤታማነት አማኞች ብርሀንና ጨው በመሆን ራሳቸው የሚኖሩበትን የሕይወት ፈለግ ይፈጥርላቸዋል። ይህም ለሰው ልጆች ጥቅም ሁሉ ይውላል።

በመሰረቱ ክርስትና ሕብረተሰብ ለዋጭ ሕይወት ነው፡፡ አንዳንዶች በእምነቱ ተጠቃሚ ባይሆኑም እንኳ ከክርስቲያኖች በሚመጣ የበጎ ስነምግባር ምላሽ ዓለም የተረጋጋ እና ሚዛናዊ ሆና ትኖራለች፤ ይህም ከጌታ ዳግም መመለስ ጋር ይተሳሰራል።

## ምዕራፍ 4

## ከታቃስ ስልትና ከቤተክርስቲያን ታሪክ ተገዢ የሆነው ግንዛቤ

በየትኛውም አስተምህሮ ላይ ተነጋግሮ ውጤታማ የሆነ ማጠቃለያ የሚደረስበት ዘዴ አልያም ጥረትን በሚጠይቅ ስራ ላይ አቋራጭ መንገድን ብቻ በመጠቀም መንፈሳዊ መስሎ መታየት፤ አልያም በተሟላ ሁኔታ የሶስቱን አካሄዶች በአግባቡ ካለመጠቀም የተዛባ ማጠቃለያ ላይ ይደረሳል።

ከዚህም የተነሳ የ ታ.ቃ.ስ ምንነትን መጥኘ ላመላከት ከዚያም ሰባውያንም ሆኑ ስነመስተዳድራውያን የተጠቀሙበትን አካሄድ አብረን እንመልከት:-

**ታ- ታሪካዊ ዳራ:-** የ**«መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ከመረዳት»** ደራሲ ስቴሬት በገፅ 65 ላይ ያብራራበትን መነሻ ቀንጥሬ በማስተዋወቅ ልጀምር «ሊታወቅ እስከተቻለ ድረስ በቀድሞው ታሪካዊ፤ መልከአምድራዊና ባህላዊ ሁኔታ መሰረት ትርጓሜ ይስጡ» ይላል ከዚህም የተነሳ መጽሐፍ ቅዱስ የተፃፈበትን ወቅት ማጥናት፤ የሕዝቡን ታሪክ መመዘን፤ አጠቃላይ መልከዓ ምድራዊ ገፅታን፤ ወቅታዊ፤ ፖለቲካዊ፤ ማህበራዊ፤ሃይማኖታዊ እና መሰል መገለጫዎችን ማወቅ አስፈላጊ ነው።

የአይሁዶች ባህል በአብዛኛው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይታያል፤ የፍልስጤሞች ባህልና እምነት እንዲሁም በኢየሱስ ዘመን የነበሩ ኃያላን እንደ ሮም፤ ግሪክ የመሰሉሕዝቦች በተላከው ወይም በተፃፈው መልዕክት ላይ የነበራቸውን አስተዋፅኦ ማጥናት ተገቢ ነው።

እንደ ተከሉ መንገሻ ፁሑፍ «Homely» በእንግሊዞች ዘንድ የቤት ልጅ፤ የተወደደች የተከበረች የሚል ፍቺ አለው በአሜሪካኖች ይኸው «Homely» አስቀያሚነትን» ተፈላጊ አለመሆንን በማገርዳት ለመጥፎ መገለጫ ይውላል።

እንግዲህ ድርሰቱ በማን እይታ ምን ትርጉም ሰጠ ማለት ታሪክን ይመለከታል፤ ብዙዎች

ኤልሳዕ ኤልያስን እጥፍ መንፈስ ወይም እጥፍ መንፈስ ቅዱስ እንደጠየቀ ሲያስተምሩ ይስተዋላል፤ ይህ ግን በዘዳ 21፡17 በእስራኤላውያን የበኩር ልጅ ድርሻ ላይ ይወሰናል፤ ኤልሳዕ ጥያቄው የበኩር ልጅ የሚገባውን ውርስ ኤልያስ እንዲሰጠው ወይም የእርሱ ቀዳሚ ወራሽ መሆኑን ገላጭ ነው፤ ይህን ለመገንዘብ የወቅቱን ታሪክ ማወቅ ተገቢ ነው።

ለምሳሌ ዳንኤልን በተመለከተ ንጉሱ ሦስተኛ ገዢ አድርጎ ሾመው ይላል፡- ይህ ምን ማለት ነው? የእርሱ ምክትል አደረገው ማለት አይቀልምን፤ ልንል እንችላለን ዳሩ ግን ዳን. 5፡7-16 ዳንኤል 3ኛ ሆኖ የተሾመው ቀድሞውኑ ብልጣሶርና አባቱ በአንድነት ይገዙ ስለነበረ ነው። ከዚህም የተነሳ 3ኛ ሆኗል መባሉ ልክ ነው።

ታሪካዊ ዳራ፡- ታሪክን በቅጡ በማወቅ የዚያን ግዜውን አጠቃላይ መገለጫዎችን ሁሉ መፈተሽ፣ ከዚያ ግንዛቤ ላይ በመድረስ ለእኛ ለወቅቱ ሰዎች ተገቢ ትርጓሜ ማውጣት ያስችላል።

**ቃ- ቃሉን በቃሉ መፍታት** ነው፤ የአንድን ደብዳቤ ትክክለኛ ፍቺ (መልዕክት)ለመረዳት ደብዳቤውን ሙሉ ለሙሉ ማንበብ ተገቢ ነው። ልክ እንዲሁ የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት አንዱን መጽሐፍ በወጉ ማንበብ፣ ጥያቄ የሚኖር ቢሆን ተቀራራቢ መፅሐፍትን አመሳክሮ ማጥናት፣ ከዚህ ካለፈ ከ66ቱ ቅዱሳን መጽሐፍት እይታ እና ግንዛቤ አኳያ በመፈተሽ ወደ መደምደሚያው መምጣት ይቻላል።

በመሰረቱ «...መጽሐፍ ቅዱስ ከራሱ ጋር አይቃረንም ስለ እግዚአብሔር አንድ መልዕክት የሚሰጥ መሰረታዊና አንድ ወጥ መገለጥ ነው...» ከዚሁ ጭብጥ ጋር የሚስማማው ዘላለም መንግስቱ **«መጽሐፍ ቅዱስ እና የአፈታት ስህተቶች»** በሚለው መፅሐፉ የመግቢያ መግለጫውን የጀመረው በሳሙና ማስታወቂያ ነው «የምናመርተው ሳሙና ከዚህ በላይ ሊሻሻል የማይችል በመሆኑ እነሆ ሽፋኑን ብቻ አሻሽለን አቅርበናል» ይላል፤ በዚህም የሳሙናውን የይዘት በላጭነት ሊያመላክቱበት ፈልገዋል።

እውነተኛ ሆኖ ይህን አይነት ማስታወቂያ ሊሰራ የሚችለው ለመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ከሽፋን ለውጥ ውጪ ምንም ሊጨመርበት የማይገባና ሊሻሻልም የማይችለው የሕያው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው እንዲህ ሆኖ ሳለ ግን ቃሉን ቅድሚያ በመስጠት በቃሉ ለመፍታት ካለመሞከር የተነሳ የተሳሳተ ትርጓሜና የተሳሳተ አደራረግ በዝቷል።

ጴጥሮስ ግን በ2ኛ ጴጥ 1፡19 «ከጌታ ለተሰጠን የትንቢት ልክ በጨለማ ላለ መብራት እንደምንጠነቀቅ ሁሉ ለቃሉም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል» ይላል።





መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ዘላለም አገላለፅ (ገፅ 21) በውስጡ ብዙ መጽሐፍትን ይዟል፤ 66። ይህም ሆኖ ግን አንድ መጽሐፍ ነው፤ አንድ ያሰኘው አንድነት አለው፤ እርስ በራሱ አይጋጭም፤ ስለዚህ ማንም አንድን ክፍል ሲያጠና ወይም ሲሰብክ በሌላ ቦታ የተፃፈውን ተቀራራቢ ሀሳብ በቃሉ ውስጥ በመፈተሽ በማስተያየት ማጥናት አለበት።

ቃሉን በቃሉ የመተርጎም ወይም የመገንዘብ አቅም ከሊቅነት የተነሳ የሚመጣ ውጤት አይደለም፤ ከጥረት ጎን የመንፈስ ቅዱስ አብርሆት አብሮት አለ፤ ከዚህም የተነሳ በትሁት መንፈስ፣በፀሎት ተገቢ ጊዜን በመስጠት ማጥናት ወደ እግዚአብሔር ዘላቂ ሀሳብ ያመጣል።

**ስ- ስርዓተ ቋንቋ፡-** መልዕክቶች ሁሉ የተላለፉት በቋንቋ አማካኝነት ነው፤ አንባብያን፣ አድማጮች በሚረዱት ቋንቋ የሚተላለፈውን መልዕክት የመረዳት አቅማቸው ጠንካራ ነው፤ ቋንቋ በተጠቃሚዎቹ ዘንድ አገልግሎቱ ማግባባት እና የመልዕክቱ ተጠቃሚ ማድረግ ነው።

ቋንቋ ሁሉ ግን ስርዓት አለው፤ ደንብ፣ ሕግ አግባብ፤ አለው ይህንን ማወቅ የግድ ነው።

የቋንቋው ቃላት የአሳብ፣የንግግርና የግኙነት፣ መገንቢያ መሳሪያዎች ናቸው፤ ትርጉም ባለው ሥርዓት የተቀነባበሩ ቃላት የሰው ልጆች መግባቢዎች ናቸው (ተከሉ 44) ይህ ለእግዚአብሔር ቃልም ያው ነው።

ቃላት አንድ እና ከአንድ በላይ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል፤ አንዳንዶቹም የተለያዩ ቃላት አንድ ትርጉምን ይዘው ሊገኙ ይችላል፡-ቃላት ወደ ሐረግ ወደ ዐረፍተ ነገር፣ ወደ አንቀፅ እንዴት እንደተሸጋገረ ማጤን ተገቢ ነው፤ ስርዓተ ቋንቋ የቋንቋውን ሰዋሰው በትክክል በመገንዘብ መፍትሄን ያመጣል። ይህም የቋንቋውን ስም- ቅፅል- ግስ- ተውሳከ ግስ፡- የስምገላጭ- የግስ ገላጭ ምንነትን በቅጡ ማወቅ ወሳኝ ነው።

በምሳሌ እንመልከተው 1ቆሮ 11፡27 «ስለዚህ **ሳይገባው** ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ፅዋ የጠጣ ሁሉ...» የሚለውን «ሳይገባው» የሚለው ቃል የግስ ገላጭ መሆኑን በመዘንጋት አንድ ሰው የጌታ ራት መውሰድ የሚከለከል ወይም የአእምሮ እና የመንፈሳዊ ብቃት እና የህሊና ዝግጅት ከሌለው አይውሰድ በሚል ትርጉም ብዙዎች በጌታ ራት ወቅት ቀሰስተኞች እና አልቃሾች በመሆን ይውላሉ፤ አንዳንዶች ጭርሱኑ ይህን በማዛባት ሀጢአተኛውን የጌታ ራት በመከልከል መቅጫ ያደርጉበታል፤ ይህ ሁሉ የሆነው «ሳይገባው» የሚለውን ቃል በሰዋሰው አገባቡ ባለመረዳት ነው፤ አገባቡ ግን የግስ ገላጭ በመሆን የሚያመለክተው መብላትንና የመጠጣትን ከንውን እንጂ ሰውየውን አለመሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው።

አንዳንድ ገር ሰው "ፍቅር እግዚአብሔር ነውን" ና "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" የሚለውን አገላለፅ አንድ አድርገው ይጠቀማሉ፤ ይህ ግን የባለቤትና የሙያ ለውጥ ስላለው የተለያዩ ናቸው እንግዲህ ሥርዓተ ቋንቋ የጊዜ ጥያቄን፣ የቁጥር ገለፃን፣ የተውላጠ ስሞች ድርሻን፣ መስተአምሮችንና መስተፃምሮችን በማወቅ የእግዚአብሔርን ቃል መረዳት በ**ታቃስ** ስልት ውስጥ ወሳኝ እና ተፈላጊ ነው።

ከዚህ አኳያ ሰባውያን ምን ያህል ይህን ፈለግ መከተላቸውን እንዲሁም የስነመስተዳድራውያን ገለፃ እንዴት እንደ ተብራራ እናጤናለን።

ሰባውያን የኢየሱስ ዳግም መመለስ በ70 ዓ.ም መከናወኑን ለማገለጥ ጥረት አድርገዋል ግና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በታሪክ ውስጥ ያለፉትን 2000 አመታት ስትዘልቅ ምን አድርጋ ነበር።

የቤተክርስቲያን ታሪክ ከሚያረጋግጣቸው መረጃዎች ውስጥ አንዱ ክርስቶስ ዳግም ይመለሳል የሚለው ትምህርት በአንደኛው ክፍለ ዘመን በስፋት ነበረ ነገር ግን የተጠባበቁት ጌታ ስላልመጣ በርካታ አማኞች ተስፋ የመቁረጥ ዝንባሌ ነበራቸው፤ (Church History. SehaffVol 2 P.418) እንዲሁም ቢሆን ግን በየጊዜው የክርስቶስን ዳግም መምጣት በቅርቡ ሊሆን እንደሚችል የሚሰብኩና በንቅናቄው መሪ በ ሞንዳኑስ መጠሪያ «ሞንዳኒዝም» የሚል ትምህርት ከ155 ዓ.ም ወዲህ በመካከለኛው ምስራቅ፣ በሮምና በሰሜን አፍሪካ በስፋት ተስፋፍቶ ነበር።

እነዚህ አማንያን ራሳቸውን «መንፈሳውያን ክርስቲያኖች» ብለው ሲጠሩ ሌላውን «ሥጋውያን ክርስቲያኖች» በማለት ይለዩ ነበር፤ ሥጋውያኑ «የዓለም መጨረሻ መድረሱንና የክርስቶስ ዳግም መመለስን በመዘጋጀት የማይጠብቁትን ሁሉ በሙሉ ልባቸው አልተቀበሏቸውም ነበር።

በመሰረቱ ይህ ታሪክ ሰባውያንን ይፈታተናል፡ የጌታ ዳግም መመለስ በ70 ሆኖ ቢሆን ከ100 ዓመታት በኋላ ይኸው እንቅስቃሴ እንዴት ትኩረት ተሰጠው ያሰኛል።

## ኢቴናጎራስ

ኢቴናጎራስ ከ161-180 ባለው የጊዜ ክልል ውስጥ የሰራቸው ስራዎች ተፅፈው ተናኝተዋል፤ ሰውዬው በአቴንስ የነበረ ታላቅ የእምነት አቃቤ እና ክርስቲያን ፈላስፋ ነበር፤ ይህ ሰው ትንሳኤ ሙታን የለም የሚለው የግሪክ አስተሳሰብን በብርቱ በትር የመታ እና በክርስቲያኖች መካከል አርሾ ሆኖ በወቅቱ ይብላላ የነበረውን የዳግም መወለድ ምንነትን እንዲሁም የትንሳኤን እርግጠኝነት በሚገርም ሁኔታ ለግሪክ ፈላስፎችና ለአማኞች በሚጠቅም መንገድ ፅፏል።





መፅሐፉ «**ስለ ትንሳኤ ሙታን**» የሚል ሲሆን ምንም ዐይነት የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ሳይካተትበት ተፅፏል፡- ይህን ያደረገውም የግሪክ ፈላስፎች መፅሐፍቱን ስለማይቀበሉት ነው፤ በትይዩ ግን የአዲስ ኪዳን መፃሕፍትንና አመክንዮአዊ መግለጫዎችን በመጠቀም ለክርስትና የቆመ ስመጥር ሰው ነው።

ሰባውያን የክርስቶስ ዳግም መምጣት በሰባ ሆኗል ከማለት ባሻገር የሙታን ትንሳኤን በዳግም ልደት በመተካት በአካል ከመነሳት ከመንፈስ ሙትነት መንቃት ይሻላል ብለው ያስተምራሉ። አቴናጎራስ ግን ከክርስቶስ ዳግም መመለስ ጋር በተያያዘ ሙታን እንደሚነሱ ፅፏል፤ ይህም በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተገለጠ እውነት ነበር (ምክረ **<u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u>** ቅፅ I ገፅ 270)

## የኒቂያ ጉባኤና የዳግም መመለሱ ቀኖና

በ260 ዓ.ም በሊብያ የተወለደው አርዮስ አድጎ በከፍተኛ መንፈሳዊ ኃላፊነት ላይ ሆኖ እያለ አመክንዮያዊ አቀራረብ ይታገለው ነበር፤ በትምህርተ መለኮት ትንታኔው የነቃ አእምሮና አመክንዮያዊ አካሄዱ ካነሳበት ጥያቄ አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ሊባል አይገባውም ፍጡር እንጂ የሚልን አስተምህሮ አደረጀ፤ ይህንንም አሰራጨ፤ ዘመኑ ቆስጠንጢኖስ የሮምን መንግስት በሚመራበት ጊዜ ስለነበረ ጉዳዩ የሮምን ዓለም በመከፋፈል ጉልበት እንዳያሳጣም ጭምር በማሰብ በ325 በኒቂያ ጉባኤ ጠርቶ አወያየ ከብዙ ቀናት ምክክር በኋላ መሰረታዊ ድንጋጌዎች ወጡ ከወጡት ውስጥ፡-ኢየሱስ ክርስቶስ፤-

- ሰው ሆኖ ስለ እኛ የታመመ፣
- በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሳ፣
- ፍፁም ሰው፤ ፍፁም አምላክ መሆኑን፣
- ወደ ሰማይ አረገ፣
- በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ ዳግመኛ የሚመጣ መሆኑን፣
- በመንፈስ ቅዱስም አማኞች ማመን እንደሚገባቸው የሚያጸኑ ድንጋጌዎች ፀደቁ።

ጉባኤው ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም ሰው ብቻ ሳይሆን ፍፁም አምላክ መሆኑን ካወጀ በኋላ በዚያው ዝርዝር የኢየሱስ ዳግም መመለስ፣ በመመለሱም በህያዋንና በሙታን የሚፈርድ መሆኑን ድንጋጌው

አፅንቷል። ታሪክ የሰከኑ ጭብጦችን በማንጠር ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርግ የጥናት ዘርፍ ነው። ከዚህም የተነሳ በ4ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ የምስራቅና የምዕራብ ቤተክርስቲያናት በአንድነት የክርስቶስ ዳግም መመለስን በፅናት መጠበቅ መገለጫቸው ሆነ፤ እምነቱ በ70 ዓ.ም መልስን አግኝቶ ቢሆን ይህ ውሳኔ ባልመጣ ነበር።

## የ381 የቁስጥንጥንያ ጉባኤ እና ዳግም መመለስ

ይህ ጉባኤ ተከታትለው የመጡ ኑፋቄ አስተሳሰቦችን መስመር ያስያዘ ሲሆን ጉባኤው ትኩረት ሰጥቶ መክሮ ካወሳቸው ቀዳሚ አስራ ሁለት ዝርዝሮች ውስጥ፡-

- 7ተኛው በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ ዳግመኛ ይመጣል፤
- 11ኛው የሙታንንም መነሳት ተስፋ እናደርጋለን፤
- 12ኛው የሚመጣውንም ሕይወት እንጠባበቃለን የሚሉ ነበሩበት።

በዚህም ሰባውያን የኢየሱስን መመለስ እና የትንሳኤውን ምንነት በዚያው ሳያስቀር ተጓዥነቱን በማዝለቁ ተስፋው ተጠባቂ እምነቱም በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የፀና መሆኑን ያረጋግጣል።

## 431 የኤፌሶን ጉባኤ፡- ሞት እና የውርስ ሀጢአት

የ431 ጉባኤን ያሰባሰበው የእንግዳ ትምህርቶች መምጣት ሲሆን በግዜው የነበረው ጉባኤ በርካታ ውሳኔዎችን አሳልፏል። ለማሳለፉም ምክንያት ከሆኑት የስሁተት ትምህርቶች ውስጥ ሶስቱ

1. አዳም ሲፈጠር ሟች ሆኖ ነው እንጂ ህያው ሆኖ አልተፈጠረም ስለዚህ ሞት በተፈጥሮ ያለ እንጂ በኃጢአት ምክንያት የመጣ አይደለም ስለዚህ አዳም ባይበድልም ይሞት ነበር።
2. የአዳም በደል ራሱን እንጂ የአዳምን ዘር አልጎዳም ስለዚህ ጥንተ አብሶ (የውርስ ኃጢአት) የለም።
3. ሕፃናት ወደዚህ ዓለም ሲመጡ ወይንም ሲወለዱ አዳም በኃጢአት ከመውደቁ በፊት እንደነበረው ሆነው ያለ ምንም የውርስ(የበደል) ኃጢአት ይወለዳሉ፤ ሰው በተፈጥሮው ሀጢአት የመስራትም ሆነ ያለመስራት ችሎታ ኖሮት ይወለዳል።

እነዚህን ከላይ የተቀመጡትን ዝርዝር አቋሞች ሰባውያን ይጋሩታል። በወቅቱ የቀረበው መፅሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ ግን *«እነሆ በዓመፃ ተፀነስሁ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ»* (መዝ 51፡5 እንዲሁም





*«በአንድ ሰው ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ምክንያት ሞት መጣ ይኸውም ሰው ሁሉ ኃጢአት ስለሰራ ሞት በሰው ሁሉ ላይ መጣ»* በማለት ጉባኤው፡- **ሰዎች ሁሉ ሀጣን ትልቅ ሳይል ደንካሮች** መሆናቸውን ወሰነ። በሰባውያን ዘንድ ግን እነዚህ ሁሉ በእምነትነት ከ1500 ዓመት በኋላ ይዘከራሉ።

## 397 ውሳኔና ቅዱሳን መጽሐፍት በካርቴጅ

የአዲስ ኪዳንን 27 ቅዱሳን መጽሀፍትን ያስገኘ አመት ነው፤ በመጀመሪያ በ367 በአትናትዮስ የአሌክሳንድሪያው መጋቢ አሳሳቢነት፣ ኋላም በ393 በሰሜን አፍሪካ በ ሂፖ በተደረገ የአስፈላጊነቱ ውሳኔ በመጨረሻም በ397 በካርቴጅ በተደረገ ጥንቃቄ የተሞላበት ውይይትና የእግዚአብሔር መለኮታዊ ርዳታ ተጨምሮበት በእግዚአብሔር መንፈስ አማካኝነት ለሕዝበ ክርስቲያን መመሪያው የሚሆኑቱ ተለዩ።

እንዲህ ለመለያየታቸው መንስኤ በየጊዜው የሚነሱ እንግዳ ትምህርቶችና ልምምዶች መበርከትና ለማመሳከሪያ በርካታ ክርስቲያን ተኮር ግን እርስ በርስ መጣረስ የበዛበት መፅሐፍት በርከተው መገኘታቸው ነበር እንዲወሰኑ ያስገደደው። እንደ ምሳሌ፡- በመንፈሳዊ ቅንዓት በመሞላት ጌታን መስለው ለመኖር ይጓጉ የነበሩት ሞንታኒስቶች ከ156-172 ዓ.ም «...የክርስቶስ ዳግም መመለስ በቅርቡ እንደሚሆን አስጠንቀቁ ከዓለም መለየትም ለዚህ የግድ መሆኑን አስተማሩ።(ስሜ <u>**የቤተ ክርስቲያን ታሪክ**</u> ቅፅ አንድ ገፅ 116) ይህን መሰል ቀድሞ የተፈጠረን ክፍተት ለመድፈን እንዲሁም በ144 ዓ.ም እንደቀራጭ የቆጠርነው ማርሲዮን የፈፀመው ስህተት የቅዱሳት መጽሐፍት ካለመለየት የተነሳ የመጣ ነበር። እነ ማርሲዮን ካስተማሩት ውስጥ አንዱ «... ኢየሱስ ከሰማይ ወደ ምድር የመጣው ሁለት ጊዜ ነው፤ የመጀመሪያው ለመሰቃየትና ለመሞት መጣ ሁለተኛውም ጳውሎስን ለመገናኘት ኢየሱስ ወደ ምድር ተመለሰ...» ይሉ ነበር

እነዚህን ለመሰሉ ችግሮች መፍትሄን ለመስጠት የካርቴጅ ስብሰባ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍትን ለየ። እንግዲያስ ከተለዩ በኋላ ያሉት መልዕክቶች በሙሉ ሰባውያንን ይገዳደራሉ፤ መፅሐፍቱ የእግዚአብሔር መለኮታዊ መጽሐፍት እስከሆኑ ድረስ ሊታመኑና የእምነት መግለጫዎች መሆን ይገባቸዋል። በመሰረቱ እንደ ሰባውያን መጽሐፍቱ ከ70 ዓ.ም በፊት ተፅፈው ተጠናቀዋል ሳይሆን ቁም ነገሩ በካርቴጅ በ397 ተለይተው ተወስነዋል። ትኩረት ሊሰጠው የተገባ በላጩ እውነት ነው። በእነርሱም ውስጥ የኢየሱስ ዳግም መመለስ እውነተኛ ተስፋ ሆኖ ዘልቋል። (ስሜ <u>**የቤተ ክርስቲያን ታሪክ**</u> <u>ቅፅ</u> <u>አንድ</u>118-119)

## የ ዌስት ሚኒስቴር የ1646 የእምነት መግለጫ

## (West Minster confession of faith 1646)

የዌስት ሚኒስቴር አጠቃላይ ጉባኤ ለቤተክርስቲያን ጥቅም በመግባባት ከወሰናቸው ውሳኔዎች ውስጥ አንዱ እንዲህ ይነበባል፡-

«...በስጋው በተሰቃየ፣ በሞት ጥላ ውስጥ ባለፈ፣ በሶስተኛው ቀን የሞትን ሀይል አጥፍቶ በአካል በተነሳ፣ወ ደ ላይም በማረግ በአባቱ ቀኝ በሚገኝ፣ አማላጃችን የሆነና በሰዎችና በመላዕከት ላይ ሊፈርድ እና የአለምን ታሪክ ሊጠቀልል ዳግም በሚመለስ...» እናምናለን። ከዚያም አዝልቆ «...በመጨረሻው ቀን በሕይወት ያለን አንሞትም በሞት ያሉት ግን ይነሳሉ በአካልም ይሆናሉ ለዘላለምም ይኖራሉ» በማለት የዌስት ሚኒስቴር ጉባኤ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ይህን መግለጫ አፀና። ይህ ለሰባውያን መልዕክት ነው። እርግጥ ነው ጉባኤያት የእግዚአብሔርን ቃል በመተካት አያገለግሉም ግና የእግዚአብሔር ሰዎች በፍቅር፣ በትህትና፣ በመንፈስ ቅዱስ እገዛ ባደረጓቸው ውሳኔዎች ላይ ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው።

## ደቂቀ እስጢፋኖስ እና 15ኛው ክፍለ ዘመን

በኢትዮጵያ ከማርቲን ሉተር መነሳት በፊት ተሀድሶን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ ለማካሄድ ጥረት ያደረጉ ቡድኖች መጠሪያ ነው ደቂቀ እስጢፋኖስ።

እስጢፋኖስና ተከታዮቹ በንጉሡ ፊት ከተከሰሱበት አንዱ «...ስለ ክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት እንዲሁም ከፃድቃን ጋር ስለሚኖረው አንድ ሺህ ዓመት መንግስት ምንነት ላይ ከስ ተመስርቶባቸው ነበረ፤ ምላሻቸውም የክርስቶስ ዳግም መምጣት የማያጠያይቅ ሲሆን የሺው ዓመት መንግስትን ግን በተመለከተ ዘርዓ ያዕቆባውያን «ደብረ ፅዮን» ክርስቶስ ከፃድቃን ጋር የሚገዛበት የአንድ ሺህ ዓመት ዘመን ነው» ሲሉ እስጢፋኖሳውያን ደግሞ «የክርስቶስ መንግስት የክርስትና ዘመን ስለሆነ የክርስቶስን ሕግ ለሚጠብቅ ሁሉ ዘመን ሳይለያይ ሁል ጊዜም አለች» የሚል እምነት ነበራቸው (ስሜ <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቅፅ አንድ.</u> 357-359)

ይህ ገለፃ ለሰባውያን ግንዛቤ ከ1400 ዓመታት በኋላም ዳግም መመለሱ የሚጠበቅ ክስተት መሆኑ ሺህው ዓመትም ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሰራው ስራ ከተከናወነበት እስከ አሁን ያለውን ጊዜ ገላጭ መሆኑ ላይ ማተኮራቸውን ልብ ማለት ተገቢ ነው፡ በታሪክ የተከታታይ መቶዎች ጉዘት መካከል ዳግም መምጣቱ ተወስቷል።





በተያያዥ ኢየሱስ ክርስቶስ *«ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላዕክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም»* (ማቴ 24:36) ማለቱ አንድን መሰረታዊ እውነት ያነሳሳልናል፤ እሱም ምልክቶችንና የምልክቶቹን ጡዘት በመመልከት ጊዜው ቀርቧል የማለት አቅምን አማኞች እንዲያስተምሩ እንዲሰብኩ ታዘዋል፤ ከዚያ ውጭ ግን ቀን ቆርጠው ዓመት ወስነው የኢየሱስ ዳግም መምጣት በዚህ ጊዜ ነው ማለት አለመቻሉን ማመን ተገቢ ነው።

በአንደኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች የጌታን መመለስ በገዛ ዘመናቸው ጠብቀው ነበር ግን አልሆነም፤ ጭርሱኑ አንዳንዶች ስራ ፈት ሆነው *«የጌታን መምጣት እጠባበቃለሁ»* በማለት «ሊሸወዱ» ያሉትን፣ ዘመናቸውን በከንቱ ሊመሩ ያላቸውን ሐዋሪያው ጳውሎስ በተለይም ለተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን *«የጌታ ቀን ደርሷል ብላችሁ ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡ»* 2ተሰ 2፡1-2 *በማለት ጊዜው ደረሰ ያሉትን ሁሉ ተረጋጉ ማለቱን ልብ እንበል፤ ጭራሽ የጌታ መዘግየት ሊድኑ ያላቸው ሁሉ ወደ ንስሀ እስኪመጡ መሆኑን ሐዋሪው ጴጥሮስ ነገረን «ጌታ ኢየሱስ ይመጣል ተብሎ ተስፋ ተሰጥቶ አልነበረምን? ታዲያ የትአለ? የቀድሞ አባቶቻችን ከሞቱበት ጊዜ አንስቶ ሁሉ ነገር ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እንደነበረው ነው? ይላሉ ይልቅስ... ጌታ ኢየሱስ የተናገረው የተስፋ ቃል ለመፈፀም አይዘገይም ነገር ግን ሰው ሁሉ ለንስሀ እንዲበቃ እንጂ ማንም ሰው እንዳይጠፋ ፈልጎ ስለ እናንተ ይታገሳል»* (2ጴጥ 3፡4-9) በማለት የዘገየ የመምሰሉን ምክንያት ያብራራል።

እነዚህ ሁለት ክፍሎች ቀን እንዳንቆርጥ ያመለክታሉ፤ ዳግም መመለሱ ለጥሪው የተዘጋጁትን ሁሉ እስኪያካትት የወደፊት መሆኑን ይናገራሉ።

እንዲህ ሆኖ ባለበት ግን ብዙዎች የጌታን ዳግም መምጣት ከመናፈቅ የተነሳ አልያም ዳግም ይመጣል የሚለውን መፃኢ ቀን በነበራቸው ቅድመ መረዳት ላይ ብቻ በማተኮር፣ አልያም ያለፉት ዘመናት በኢየሱስ አለመምጣት ብቻ ትንቢቶች እንዳልተጠናቀቁ በመቁጠር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ቀን በዚህ ዓመት ይመጣል ማለት ይቀናቸዋል።

ቀን በመቁጠራቸው ተሳስተዋል፤ ዳግም መምጣቱን ከግምት በማስገባታቸው ተመስግነዋል። በዚህ ዝግጅት ግን የኢየሱስን ዳግም መመለስ ተስፋ በማድረግ መስመር ውስጥ የተገኙ ስለሆኑ ለጥናቴ ተፈላጊዎች ናቸው።

ክርስቶፎር ኮሎምቦስ ጉዞውን ሲጀምር አብሮ ያሰበው ወይም ያመነው ነገር በ1650 ክርስቶስ ይመጣል ብሎ መነሳት ነበር። በ1850 ዊሊያም ሚለር የስብከቱ ሁሉ ዋንኛ የኢየሱስ ዳግም መመለስ በዚያው ዓመት እንደሚሆን ነበር። ከዚህም የተነሳ አማኞች ሁሉ ያላቸውን ሸጠው ተሰናድተው ነበር።

በ1914 የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ሲቀጣጠል በርካታ አማኞች በተለይም የይሕዋ ምስክሮች ኢየሱስ ይመጣል ብለው ተሰባስበው ነበር፤ ሳይመጣ ሲቀር ግን «ከማፈር» በሚል መንፈስ «መምጣቱንስ መጥቷል የመጣው ግን በስውር ነበር» ማለት ጀመሩ፣ በ1982 የባህረ ሰላጤው የጦርነት ፍጥጫም ላይ የዓለም መጨረሻ መቃረቡን ወስነው ነበር።

አሁን በቅርቡ በ1994 የዓለም መጨረሻ ይሆናል ያለው ሐሮልድ ካምፒንግ ያኔ የተሳሳትኩት በቆጠራ ስህተት ነው ብሎ ግንቦት 21/2011 ለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ ቀጠሮ አስይዞ ነበር።

በግንቦት ወር በ2003 ዓ.ም የተመረቀው «<u>ከሌሊቱ ስንት ሰዓት ነው» ም</u> ይመስለኛል በሚል ማባበያ የዛሬ 37 ዓመት ኢየሱስ እንደሚመለስ አጣቁሟል።

ከ1950 መጀመሪያ ላይ የገላውዲዮስ ትምህርት ቤትን ንጦ የነበረውም በተቆረጠው ቀን ኢየሱስ ይመጣል የተባለለት እንቅስቃሴ በናዝሬት ተጠብቆ መክሸፉ ልብ ይባላል፤ በዚህ ጊዜ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እና በሁለተኛና በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ዘንድ ሁሉ «ወሬው» ተዳርሶ:- ከዚህች ምድር ለመለየት ከጌታም ጋር ለመገናኘት ጥረት ተደርጓል።

ሁሉም ግን አልሆነም። እነዚህ ሁሉ የተሳሳቱት የመምጣቱ ተስፋ የት አለ? የሚል ጥያቄ ተፈጥሮባቸው ይሆናል። በጥቅሉ ግን የሁሉም ጥረት በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የኢየሱስ ዳግም መመለስ ቀሪ ተስፋ ስለሆነ የሆነ ነበር።

## የምስክርነት ፅኑነት

ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የኢየሱስ ዳግም መመለስ ተጠባቂ ተስፋ ሆኖ ዘልቋል። ዛሬ 2007/2015 ላይ ኖረንም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም እንደሚመለስ ይፃፋል። ይሰበካል።

በርካቶች መፅሀፍ ፅፈዋል፤ በቁም ነገር የተሞሉ ስብከቶችን አደርጅተዋል። እነዚህ ስመጥሮች ዳግም ምፅአቱን እንዴት እንደተረዱትና እንደገለፁት እናብብ፤-

### ቻርለስ ስፐርጂን/Charles H.Spurgeon

አስራሁለቱን ነገድ የጠቀለለው የእስራኤል ታሪክ የኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ ሲጠብቅ ኖረ ሆነም። አሁን ደግሞ ላለፉት 1900 ዓመታት የኖርን አማኞች እንደመጀመሪያው እርግጠኝነት ሁለተኛውም





እውን ይሆናልና የርሱን ዳግም መመለስ በመጠባበቅ እንኖራለን።

### ማርቲን ሊዮድ ጆንስ/D.Martyn Llord.Jones

ያለ ምንም ጥርጥር ተስፋ አድርጌ የምጠባበቀው የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም መመለስ ነው፤ መመለሱ የ66 መጽሐፍት ፈርጥ ነው፤ እሱን መጠባበቅ የሁሉ ነገሮች ግቡ ይሆናልና።

### ጄ. ግሪየር/ w.J.Grier

አዲስ ኪዳናችን ኢየሱስ በአካል እንደሚመለስ ይነግረናል፤ ያስተምረናል፤ መጽሀፍ ቅዱስ:- መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ህምሳ መውረድን እንዳበሰረ ኋላም በ70 ዓ.ም ቤተ መቅደስ እንደፈረሰ ሁሉ በእርግጠኝነት ልንጠብቀው የቀረልን ተስፋ የድላችን መደምደሚያ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ ነው።

### ሌት ሳሙኤል/Lelth Samuel

ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ኢየሱስ በታሪክ መካከል እንደተወለደ ሁሉ በታሪክ የዘመናት መገለጫ መካከልም ኢየሱስ ዳግም ይመጣል።

### ኤም. አር. ዴሀን/M.R.Dehaan

«መቼ ይመለስ ይሆን? ምላሹ በብሉይ ኪዳን ተስፋ እና ትንቢት መሰረት ኢየሱስ ክርስቶስ ከ2000 ዓመት በፊት ተወለደ፤ አሁን ደግሞ ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን የተስፋ ቃላት የተነሳ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ይመለሳል።

### ኤሮል ሁልስ/ErrollHulse

ታሪክ መደምደም አለበት፤ መደምደሚያውም የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ ነው፤ የተጀመረ ሁሉ ሊጠናቀቅ አለውና።

### ጆን ኪገር/John A.Caiger

የእግዚአብሔር መንግስት በሙላት መገለፅ አለባት፤ ይህ ሙላቷ የሚታየው በኢየሱስ ዳግም መመለስ ነው፤ ይህ ተስፋ እውን እስኪሆን ራሳችንን በቅድስና በማኖር የተሰጠንን ሐላፊነት በወቅቱ እንፈፅም።

### ኤርማን ሆክስማ/HermanHoeksema

ኢየሱስ ይመጣል፤ እንዴት እንደሚመጣም ነግሮናል፤አመጣጡ ጦርነቶችን፣ ረሀቦችን፣ ጥፋቶችን በቁጥር እያስጨመረ ሲሄድ ያን ጊዜ በእምነት መጠባበቅን ስራችን ልናደርግ ይገባል። ይህ ማለት ግን ምልክቶቹ ላይ ያተኮረ ሕይወት እንኑር ማለት አይደለም።

### ቡካርትስ ፒንች/E.BuckhurstPinch

በሞት በተለዩን ወንድሞችና እህቶች የቀብር ስነስርዓት ላይ ተገኝተን የሰበክነው ወይም ያደመጥነው «ኢየሱስ ሲመለስ ይህ በስባሽ አካል ሕያው ይሆናል» ብለን ነው፤ የዚህ እውነተኛነት ካለፉት ጊዜዎች በበለጠ አሁን ላለነው ቅርብ ነው።

### ጊልበርትስ ኪርቢ/Gilbert W.Kirby

በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የጋራ ስምምነትን የያዘው አስተምህሮ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የዳግም መመለስ ተስፋ ነው። ሁሉም የአመጣጡ ሂደት ምን ይመስላል ላይ ጥቃቅን ልዩነት ቢኖራቸውም ግን ደግሞ በመመለሱ ላይ ሁሉም አንድ ናቸው።

### ጂ. ማንሊ/G. T. Manley

ብዙ የትንቢት ቃሎችን ለመረዳት ብዙዎቻችን ይቸግረን ይሆናል፤ ሳንልመጠመጥ በፅናት የምንረዳው አስተምህሮ ቢኖር «ኢየሱስ ይመጣል» ብቻ ነው።

### ፍሬድሪክ ታትፎርድ/FrederickA.Tatford

ኢየሱስ የነገስታት ንጉስ፣ የጌቶችም ጌታ የተባለበት ሚስጢር እሱ ዳግም በመመለሱ ወቅት ይፈፀማል። ይህን ተስፋ እንደማድረግ ምን ዕድል አለና።

## ታቃስን ያልተከተለው የሰባውያን አመለካከት

1. *በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ላይ ያተኮረ አስተምህሮ ማደርጀት፦* ታቃስ በመንፈሳዊ ትምህርት ላይ ስህተት ላለመፈፀም አቅጣጫን ከማሳየት በላይ «እውነቱ ይህ ብቻ ነው» ለማለት ብቃትን የሚፈጥር የአጠናን ስልት ነው።

ይህን ሊያደርስ የሚችል ስልት «ነጥሎ መምታት ወይም የተናጥል አቅም» የመፍጠር እንቅስቃሴ ነው፤ ማቴ 24 ሙሉ መልዕክት መነሻውን፣ የመምጣቱን ግዜ እና የመምጣቱን ምልክቶች





በመጠየቁ ለእነዚህ ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች በተሰጡ መልሶች ላይ ያጠነጥናል።

ይህንም ምዕራፍ ስነ መስተዳድራውያን ሁሉን እንደወረደ በቀጥታ ፍቺው በመውሰድ ትንታኔያቸውን እንደሰጡ ሁሉ ሰባውያን አብዛኛውን ተምሳሌታዊ ትርጉም ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ።

ማቴ 24 «ይህ ትውልድ አያልፍም» የሚልን የመልዕክት አንጓ አንስቷል፤ ከዚህም የተነሳ ያ ትውልድ ማን? ምን? እንዴት? መቼ? የሚለውን በጠበበውና እና በሰፋው አውድ ሳይመለከት ያ ትውልድ በወቅቱ የነበረውን ማህበረሰብ ብቻ ይመለከታል፤ የሚል የድምዳሜ ውሳኔን ይፈጥራል።

ማቴዎስ 24 ሰባውያን እንደሚያብራሩት ቤተመቅደስ ተኮር ምዕራፍ ነው፤ የዘመን ቀመርን ከቤተመቅደሱ መፍረስ በፊትና በኋላ በመከፈል የዋንኛ መነሻ መጀመሪያው ነው ብለው ያምናሉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ድንጋይ በድንይ ላይ ሳይፈርስ አይቀርም ማለቱ ቤተመቅደሱ እስካለ ድረስ የብሉይ ኪዳን ስርዓት እንዳለ አለ፤ የክርስቶስም የመስቀሉ ስራ፣ ትንሳኤውና ድሉ ሙሉ መሆን አይችልም ማለቱ አይደለም።

የኢየሩሳሌም በከፍተኛ ቅጣት ውስጥ መውደቅ፤ እንዲሁም የቤተ መቅደሱ መውደም በታሪክ ውስጥ አዲስና የመጀመሪያ ትዕይንት አይደለም። ሰባውያን ትምህርታቸውን በማቴ 24 ላይ ትኩረት ሰጥተው ሲያስተምሩ ያላስተዋሉት የቀደሙ የታሪክ ገለጣዎች መኖራቸውን ነው።

መስዋዕት ማቅረብ፣ ወደ ቤተመቅደሱ ውስጠኛ ክፍል በሊቀ ካህኑ አማካኝነት መግባት፣ ከተቋረጠ ብዙ ዓመታት አልፈዋል። ቤተመቅደሱ ለብዙ መቶ አመቶች ያለ ፅላቱ/ታቦቱ ነበር፣ ያለመስዋዕት አገልግሎትነበር፤ ቤተመቅደሱ በመቆሙ ብቻ ያለ ያህል ያኔም አይቆጠርም።

ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ፡- ኢየሩሳሌም በጠላቶቿ መወረሯ፣ በተለያዩ ጊዜያትም ቤተመቅደሷ መርከሱ፤ መፍረሱ ሁነኛ ምክንያቱ ነው።

ሔሮድስ 42 ዓመታት ፈጅቶ ያጠናቀቀውይህ ቤተመቅደስ የነበረው አገልግሎት፡- እምነትን በጋራ ለመካፈል፣ቃሉን ለመስማት፣እምልኮተ እግዚአብሔር ለመፈፀም እንዲሁም ሀገርን በአንድነት የመምራት ሐላፊነት ለመወጣት መሰረት በመሆኑ መኖሩ ተወዳጅ እና ተፈላጊ ነው።

እርግጥ ነው የቤተ መቅደሱ አሰራር፣ ክብሩና ማዕረጉ በእስራኤላውያን ብቻ ሳይሆን

በመላው ዓለም ታዋቂ እንደነበረ የተፃፈለት ታሪክ ያረጋግጣል (Flavious Josephus Jewish Antiquites)

በቅድስተ ቅዱሳን ውስጠኛ ክፍል የአሮን በትርና ታቦቱ/ፅላቱ ባይኖርም እንኳ ከቅድስት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚለየው ታላቅ መጋረጃ ግን እንዳለ ነበረ።

እግዚአብሔር አብ መድህኒት ይሆነን ዘንድ ኢየሱስን በመስቀል ላይ በጠረቀው ጊዜ እና ተፈፀመ ባለበት ቅፅበት ከተፈፀሙት መለኮታዊ ክስተቶች አንዱ የተዘጋው መጋረጃ ለሁለት መከፈል ወይ መሰንጠቅ ነው ይህን ማለት ግን የብሉይ ኪዳን ስርዓት በመካሄድ ላይ ነበር ማለት አይደለም።

ይልቅስ ቤተመቅደሱ ከ70 ዓመተ ምህረት በፊት ከ35-36 ዓ.ም ላይ ኢየሱስ ስለ በጎቹ ሕይወቱን አሳልፎ በሰጠበት ወቅት፣ በትንሳኤውና በዕርገቱ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ተፈላጊነቱ ዝቅ ብሎዋል። ሰባውያን ይህን የፀጋ መነሻ በመዝለል አዲሱ ኪዳን በገሀድ ከ70 ዓ.ም በኋላ ጀመረ በማለት ያስተምራሉ።

ማቴዎስ 24 አይሁዳዊ በሆነው በማቴዎስ የተፃፈ እና ቀዳሚ መልዕክቱን ለአጠቃላይ እስራኤላውያን ማድረጉ የሚዘነጋ ጉዳይ አይደለም። ያ ማለት ግን ለእነርሱ ብቻ የተፃፈ ለእነርሱ ብቻ የሚሰራ መሆን አለበት ብሎ «መገገም» ተፈላጊ አይደለም። ተሸጋሪነት ያላቸውጭብጦች ውስጡ አሉ፤ የመምጣቱን ጊዜ ማንም አለማወቁ፣ ምልክቶቹን ተከትሎ የሰው ልጅ የሚመጣ መሆኑን ማስተማሩ፡- ማቴዎስ ከዕብራውያን የስነ ፍፃሜ አመለካከትም ጋር የተያያዘ በቂ ዕውቀት እንዳለው ያስረዳል፤ የዚህን የመልዕክቱን አንጓ ዳንኤል እንደ ሁኔታው፣ ራዕይም እንደ ሁኔታው ተጋርተውታል።

ማቴዎስ 24 «ይህ ሁሉ እስኪሆን የሰው ልጅ አይመለስም» የማለቱና «ይህ ሁሉ እስኪሆን ይህ ትውልድ አያልፍም» የሚለው ገለፃ በቀላሉ «ይኸው» ብለን መልሱን አገኘነው የምንለው ሳይሆን ገለፃውን በዙሪያ ገቡ ማጤን በቅርብ ሩቅ አውዱ መገንዘብ ቀዳሚው ስራ ይሆናል።

በዚህም «ይህ ትውልድ አያልፍም» የሚለው ቁም ፍቺ አዎ በዚያ ትውልድ ውስጥ ሆኗል፤ ያስብላል ግን ምልክቶቹ ሁሉ ከ70 እና ከዚያ በፊት ሙሉ ለሙሉ ባለመፈፀማቸው ያ ትውልድ ብቻ ሮማውያን ያደረሱትን ጥፋት በዐይኑ ያየውንና የሆነበትን ሊመሰክር ይችል ይሆናል እንጂ ከዚያ ባለፈ ግን እማኝነቱ ምንም ነው።

ሌላው «ትውልድ» ተብሎ የተጠራው ሙሉውን የቤተክርስቲያን ዘመን የሚወክል ሊሆን ስለሚችል፡- የትውልድ ስፋት «መጨረሻው» ከሚለው አገላለፅ ጋር ሊዛመድ ይችላል፤ የኢየሱስ





መወለድ፣ መሞት እና መነሳት በብሉይ ኪዳን ሲጠበቅ የነበረው ተስፋ ነው፤ ያም በዕብ.1፥1፣በገላ 4፡4 የመጨረሻው ስራ በኢየሱስ መጠናቀቁ እስከተገለጠ ድረስ፡- የመጨረሻው መጀመሪያ የጌታ ስራ ተግባራዊ መሆን ነው። የዚህም መጨረሻ የሰውልጅ ታሪክ ድምዳሜና የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ ነው።

እርግጥ ነው «ይህ ትውልድ አያልፍምና ሞትን የማይቀምሱ አሉ» የሚለው ገለፃ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ባስተማረ የሳምንት ጊዜ ውስጥ ያዕቆብን፣ ዮሐንስንና ጴጥሮስን ይዞ ወደ ተራራው በወጣ ጊዜ በታላቅ ክብር ውስጥ ሆኖ ነበር፤ ታላቅ ደመና፣ ፀአዳ እይታ፣ አስገራሚ ገፅታ በዚያ ሆኖአል፤ ኢየሱስም በታላቅ ክብር ውስጥ ተገኝቷል፤ ይህ ከዚህ በፊት አልሆነም፤ ከዚያ በኋላ የሚከሰት ከሆነ ከዳግም ምፅዐቱ ጋር ብቻ ሊያያዝ ይችላል።

ይህን ከተመለከቱት አንዱ የሆነው ጴጥሮስ በ2ጴጥ 1፡16-18 «ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይልና ስለ መምጣቱም በነገርናችሁ ጊዜ ራሳችን ግርማውን አይተን እንጂ በሰው ብልሀት የተፈጠረውን ተረት ተከትለን አይደለም *«በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» የሚል ድምፅ ከታላቁ ክብር በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ምስጋናን ክብርን ተቀብሏል ከእርሱ ጋር በተቀደሰው ተራራ ላይ በነበርንበት ጊዜ ይህን ከሰማይ የመጣውን ድምፅ እኛ ራሳችን ሰምተናል»* በማለት ሞትን ካልቀመሱት ጋር ተሰልፎ ይህን እንዳስተዋለ ፅፏል በዚያው ምዕራፍም ይህን ቀድሞ ያስተላለፈው *«ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደገለጥልኝ በቶሎ ከዚህ ዓለም በሞት እንደምለይ አውቃለሁ እኔ አሁን የምተጋው በሞት ከተለየኋችሁ በኋላ እንኳ እነዚህን ነገሮች ዘወትር ማስታወስ እንድትችሉ ነው* (14-15) በማለት የማያቋርጥ ሐላፊነትን በትጋት ይፈፅም ዘንድ ይመክራል።

እንኪያስ ማቴዎስ 24 ከአጠቃላይ የስነ ፍፃሜ አተያይ ጋር ሊጠና ይገባል።

## የእስራኤል እርምተ ጥቅም ከዳግም መመለስ ጋር አለመያያዝ

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ሕዝቤ ያላቸውን እስራኤላውያንን ለተልዕኮ ሲያደራጃቸው ግቡ አድርጎ የጠራበት መሰረታዊ ምክንያት አሕዛብ ከእነርሱ ፍሬያማነት የተነሳ እሱን ልዑል የሆነውን ያውቁ ዘንድ ምስክር ማድረግ ነው፤ በአዲስ ኪዳንም መሲሀይቷ ማህበረሰብ (ቤተክርስቲያን) ዓለም እግዚአብሔርን በክርስቶስ በኩል በማወቅ ውጤታማ ትሆን ዘንድ አዘጋጅቷታል።

በዚህ ዝግጅት ውስጥ እስራኤልም ሆነች ቤተክርስቲያን ፍሬያማ ስራን ይሰሩ ዘንድ

ይማራሉ፤ ይገሰፃሉ፤ ይቀጣሉ፤ ዲቃላ ያልሆነ ማንም በአባት በእናቱ በአግባቡ ተቀጥቶ እንደሚያድግ እግዚአብሔርም ሕዝቡን እየቀረፀ አኑሯል፤ ያኖራል።

በዚህ አካሄዱ በብሉይ ኪዳን እስራኤል በጥፋት ላይ ብትሆን ፈጥና መመለስ፣ አልመለስ ብላ በዙሪያዋ ባሉት ሕዝቦች የአኗኗር ስርዓት ልሂድ ብትልና የእግዚአብሔር የሆነውን ፈቃዱን ባትፈፅም ደረጃ በደረጃ እየገሰፃት ወደ ልከኛው መስመር ያመጣታል።

ከእነዚህ ደረጃዎች ውስጥ የመጨረሻው በባዕዳን ኃያላን መንግስታት ማስማረክ ለግዞት ማብቃት እና በዚያ ውስጥ የፀጋን አቅም በመረዳት ወደ ንስሀ ማምጣት ፈቃዱ በመሆኑ ይህን በስራ ላይ ያውላል። መንገዱም ነው። ይህም በዝርዝር በዘዳግም 28 ተቀምጧል፤ መታዘዝ በረከትን ያመጣል አለመታዘዝ መርገምን ያስከትላል፤ ቁጥር 36-37 *«እግዚአብሔር...ወዳልነበራችሁበት ባዕድ አገር አፍልሶ ይወስዳችኋል፤ በዚያም ከእንጨትና ከድንጋይ የተሰሩ ባዕዳን አማልክትን ታመልካላችሁ እግዚአብሔር በሚበትናችሁ አገሮች የሚኖሩ ሕዝብ ሁሉ በእናንተ ላይ የደረሰውን ነገር አይተው ይደነግጣሉ፤ መቀለጃና መዘባበቻ ያደርጓችኋል።»* ይላል።

ይህ በሙሴ አማካኝነት የተሰጠ መመሪያ በሕዝበ እስራኤል ታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚ ተፈፅሟል፣ በግብፃውያን፣በአሶራውያን፣ በባቢሎናውያን፣ በግሪኮችና በሮማውያን ተፈፃሚ በመሆን ታይቷል፤ ተረጋግጧል፤ ይልቁኑ የመጨረሻው መልዕክተኛ፣ ራሱ መድሀኒትና ተስፋ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላቸው በተገኘ ጊዜ የፈፀሙት ተግባር እግዚአብሔር ባዘጋጀው የእርምተ ጥቅም አካሄድ በሮማውያን በ70 ዓመተ ምህረት ላይ ተፈፃሚ ሆኗል። «ደሙ በልጅ ልጆቻችን ላይ» ይሁን ብለዋል፤ ያም በዘመናቸው በገዛ ልጆቻቸው ላይ ተፈፃሚ ሆኗል። ይህን ለማድረግ ኢየሱስ በሰውርም ሆነ በግልጥ መመለስ አልነበረበትም የመምጣቱ ተስፋ እና ተልዕኮ እስራኤልን ያማከለ ሳይሆን የዓለምን ህዝብ የጠቀለለ ነው። ከዚህም የተነሳ የ70 ቅጣት ተገቢ እና የተለመደ የእግዚአብሔር መግሪያ መሆኑን ከወዲሁ ማየት አስፈላጊ ነው።

## የ «በቅርብ፣ በቶሎ፣ ፈጥኜ እመጣለሁ» አንፃራዊነት

ሰባውያን እነዚህን አገላለፆች ከ70 ዓመተ ምህረት ድንበር ጋ ብቻ እያይዘው አቁመዋቸዋል፤ ይልቁኑ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ሁሉ ከ70 ቀድመው ተፅፈው እንደተጠናቀቁ አምነዋል። ይህ ግን የሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት መገለጫ አይደለም።

በቋንቋ ትምህርት የቃላት አገልግሎት ልከኛ ፍቻቸውን የሚይዙት በተፈለጉበት አውድ ውስጥ ሲሰጡ የተገባቸው ትርጉም ምን ነበር? በማለት ብቻ ነው የሚታወቀው፤ የሚረጋገጠው።





የአንድ ቃል አገልግሎት በአካባቢው ባሉት አጃቢዎቹ አስተዋፅኦ ይታወቃል፤ ይህ አካሄድ በቅዱሳን መጽሐፍትም ላይ ይሰራል።

**በቅርብ፣ በቶሎ፤ ፈጥኜ፡**-በተለያዩ ስፍራዎች በተለያዩ ጊዜዎች የኢየሱስን ዳግም መመለስ በሚያመላክት ጭብጥ ውስጥ በእርግጠኝነት ሰፍረዋል።

ያ ቅርብ ግን መቼ ነው? የዚያ የፈጥኜ ልከስ ስንት ነው? ቶሎስ ድርጊትን እንዴት ነው የሚገልፀው? በእግዚአብሔር ልዑልነት ላይ ለምንደገፍ ለእኛ «እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በገዛ ፈቃዱ እና በራሱ ጊዜ ያከናውናል ይፈፅማል» ይህ ከንውኑ ደግሞ ሰዎች ሊገነዘቡት በሚችሉበት ደረጃ ላይ እየወረደ በአቅም ልክ ይገለፃል። ሲገለጥም የሰባውያን የቋንቋ ቃላት ቦታ አላቸው፤ የእግዚአብሔር እይታ ከሰው ልጅ የታሪክ መነሻ እስከ መጠቅለያው ድረስ ይጓዟዛል፤ በዚያ የታሪክ ሂደት ውስጥ ትውልድ ይመጣል፤ ትውልድ ይሄዳል። እንደ ሰንሰለት የሰው ልጆች እየተማማሩ እየተቀባበሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈፅማሉ ወይም የራሳቸውን ምኞት ያራምዳሉ።

ሁሉም ግን በሚኖሩበት በየገዛ ዘመኖቻቸው ሙሉ መረዳትን በአብዛኛው መሰረታዊ ጉዳይ ላይ ሊኖራቸው ይገባል። ከዚህም አንዱ ለአማኞች የጌታ ኢየሱስ ዳግም የመመለስ ሁነት ነው፤ ይህ ደግሞ እያለፈ ባለው ትውልድ ላይ የሚገለፀው የአዳናቸው ጌታ የሰጣቸውን ሐላፊነት እየተወጡ ሁሉም እንደተዘጋጁ በመዝለቅ የየገዛ የተወሰነላቸው የዕድሜ ጣሪያ ላይ መድረስ ነው፤ ለዚህ ደግሞ የጌታ መምጣት፣ **በቅርቡ፣ በቶሎ፣ እና ፈጥኖ** እንደሚሆን መረዳት የተገቢ ተገቢ ነው፤ እርግጥ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ይመለሳል ግና በየዘመኑ የነበሩ የመሲሐይቷ ማህበረሰብ አባላት ሁሉም ጌታ እንደሚመለስ ብቻ ሳይሆን በቅርብ እንደሚመጣ አድርገው ይኖሩ ዘንድ ያስፈልጋል፤ ያ ደግሞ የጋራ የሆነ የቤተክርስቲያን ግንዛቤ ይሆናል። በዚህ ውስጥ አንድ አይቀሬ እውነት በተግባር ላይ ይውላል፡- እሱም የትናንቱ ትውልድ ከትናንት ወዲያ ከነበረው ትውልድ ይልቅ ለጌታ ዳግም መምጣት ቀርቧል፤ የዛሬው ትውልድ ደግሞ ትናንት ከነበረው ትውልድ በተሻለ ሁኔታ ለጌታ ዳግም መምጣት የቅርብ ቅርብ የጊዜ ፍፃሜ ላይ ደርሷል።

ዮሴፍ በግብፅ ኖሮ በ110 ዓመቱ ሲሞት፡- እነርሱ ወደ ከነዓን ምድር የሚመለሱበት ጊዜ በቅርብ እንደሚሆን በመረዳት ወገኖቹን ከሞቱ በፊት ጠራቸው *«እግዚአብሔር በረድኤቱ በቅርብ ጎብኝቶ ለአብርሀም፣ለይስሀቅና ለያዕቆብ ለመስጠት በመሀላ ቃል ወደ ገባላቸው ምድር ይመልሳችኋል... በዚያን ሰዓት አፅሜን ይዛችሁ ውጡልኝ»* በማለት ነበር ያስማላቸው።

የዮሴፍ ቅርብ ግን 300 ዓመታትን ከሸፈነ በኋላ ነበር የተፈፀመው፤ እስራኤላውያንም ምንም ጊዜው እየራቀ ቢመስላቸው ጊዜው ሲመጣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላለፉትን

*«በቅርቡ» ወደ ለአብርሀም፣ ለይስሐቅ፣ ለያዕቆብ በተሰጠው ርስት ላይ እንኖራለን»* የሚለው ተስፋ ሲመጣ ዮሴፍን አልረሱትም። ያልረሱት በመሀላ ቃል «በእኛ ይሁንብህ» ያሉት አይደለም፤ እነርሱማ አፈር ሆነዋል። ያስታወሱት ግን የእግዚአብሔርን ተስፋ የተቀባበሉቱ ናቸው።

ዘፀ 12፡40 «እስራኤላውያን በግብፅ ምድር የኖሩት 430 ዓመት ነበር አራት መቶ ሰላሳው ዓመት በተፈፀመበት ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነገዶቹ ሁሉ የግብፅን ምድር ለቀው ወጡ...13፡19-20 «ዮሴፍ አስከሬኑን እንዲወስዱ እስራኤላውያንን በመሀላ ቃል ኪዳን ባስገባቸው መሰረት ሙሴ የዮሴፍን አስከሬን ይዞ ሄደ፤ ምክንያቱም ዮሴፍ «እግዚአብሔር ታድጓችሁ በምትወጡበት ጊዜ ዐፅሜን ከዚህች ምድር ይዛችሁ እንድትወጡ» በማለት ተናግሮ ነበር» ይላል።

«ቅርብ» በእግዚአብሔር አጠቃላይ እይታ ሲመነዘር መጠኑ ከአጠቃላይ መርሀ ግብሩ ጋር ሂያጅ ነው፤ ከዚህም የተነሳ አማኞች በቶሎ መምጣቱን በማመን እንዲሁም «ስጋም ወደ አፈሩ ነፍስም ወደ ጌታ ሳይመለስ ቶሎ ቶሎ ብዬ ስራዬን ልጨርስ» ጋር መተያየት አለባቸው።

## የሰባውያን አኩታዊ ግንዛቤ በቤተመቅደሱ ላይ

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን ህጉ አስፈላጊ ነው፤ ቤተመቅደሱ ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘት ኪዳኑን ማፅኛ ነው፤ ስርዓቶቹም በሙሉ ጠቃሚዎች ናቸው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ *«ሕግንና ነቢያትን ሊጠብቅ መምጣቱን አሳወቀ» ኢየሱስም የሙሴን ሕግና የነቢያትን ትምህርት ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ እኔ ፍፁም እንዲሆን ላደርጋቸው መጣሁ እንጂ ልሽራቸው አልመጣሁም»* ማቴ 5፡17 የማለቱ መንስኤ የተፈላጊነታቸውን መለኪያ ያረጋግጣል።

ቤተመቅደሱ ተገቢውን አገልግሎት እስከሰጠ ድረስ መኖሩ አይቀርም፤ ለእስራኤላውያን ክብር ነው፤ ለዓለም ሕዝብም መስህብ ነው፤ ሰባውያን በዝርዝር አስተምህሮአቸው ሁሉ «ቤተመቅደሱ መፍረስ እንደሚገባው፤ መፍረሱየቃል ኪዳን ለውጥ መነሻ መሆኑን፤ የመስቀሉ ስራም በፍሬያማነት ጅማሮን ማግኘቱን በማብሰር «እሱ እስካለ ኢየሱስ ቢሞትም በትንሳኤው ቢያርግም» ምንም ትርፍ የለው በማለት ይፅፋሉ። ይህ ግን አንድን ፅንፍ በመከተል ወደ ተሳሳተ ማጠቃለያ መድረስ ነው፤

በ70 ዓመተ ምህረት ቤተመቅደሱ ባይፈርስስ ብሎ ማሰብ ተፈላጊ ነው፤ የሮማውያን መሪዎች ከሚፀፀቱባቸው *ሥራዎቻቸው* ውስጥ አንዱ እልህ በተሞሉ ወታደሮቻቸው ቤተመቅደሱን ማፍረሳቸው ነው፤ታይተስ ቁጣቸው ገኖ ቤተመቅደሳቸውን ሊያፈርሱት ይችላሉ በማለት ስለ ሰጋ ፈጣን መልዕክተኞችን በመላክ ቤተመቅደሱን እንዲታደጉ ወትውቶ ነበር። ግን አልተሳካለትም። ዓለምን ለተከታታይ አመታት ለመሳብ እንዲመች የታመነበት የወርቅ ሽፋን በእሳት ተንቦልቡሎ



አመድ ሆነ፤ ቅርሱ እንደኖረ ቢዘልቅ ከግብፅ ፒራሚዶችና ከናቡከደናፆር የአትክልት ስፍራ በበለጠ በጠቀመ ነበር። ቤተመቅደሱ ቢኖር «ትናንት ምን ይመስል ነበር» ለሚለው ምላሽን በሙልዐት በሰጠ ነበር።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ አይቀርምም፡- እነርሱ ቤተመቅደሱን ስላሳዩት የተነሳ ምላሽ እንጂ የቤተመቅደስ መኖር የክርስትናን አስተምህሮ የሚያዛባ አለመሆኑን ዓለም ሁሉ በተረዳው ነበር። በዚህም በዚያም አርባ ሁለት ዓመታት የፈጀው ቤተመቅደስ በሮማውያን ፈርሷል። ያ መፍረስ ግን ቅርስን የዓለም ህዝብ አጣ ከማለት ውጭ የቤተመቅደሱ አገልግሎት እውነተኛውን ስራ ከመስራት ከዘገየ ዓመታት አስቆጡሯል።

ሕዝበ እስራኤል ከእግዚአብሔር በመራቃቸው እና የእሱ የሆነውን መልዕክት በመካከላቸው ማኖሩን ከነፈገ ከ400 ዓመታት በላይ ሆኗል፤ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን የዘመን ክፍተት ውስጥ እግዚአብሔር ከትንቢተ ሚልኪያስ በኋላ ድምፁን ያሰማው በመጥምቁ ዮሐንስ በኋላም በኢየሱስ *«የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለችና ንስሀ ግቡ»* ንበማስማት ነው።

በዚህ ሁሉ ግዜ ውስጥ ቤተመቅደሱ ገዝፎ አንዳንድ ስርዓቶች ከሞላ ጎደል ቢፈፀሙም በሙሉ ብቃት ያለውን ስራ ሲሰራ ግን አልነበረም በወቅቱ የነበረው ታሪክ ፀሐፊ «ፅላቱና ታቦቱ» በዚያ እንዳልነበሩ ፅፏል። እንግዲህ ያለ «ታቦቱ» የነበረ ቤተመቅደስ አቅሙ ምን ያህል ይሆናል?።

ለነገሩ «ፅላቱ» በኢትዮጵያ አለ ተብሎ አይደል የሚታመነው። ያም ገለፃ **«ፅላተ ሙሴ በኢትዮጵያ ናት ን»** የሚለው የሳህለ ጥላሁን መፅሐፍም ሆነ የ Graham Hancok «The sign and The seal»መፅሐፍ ይህንኑ ለማረጋገጥ ይሞክራሉ። እንግዲህ በእስራኤል ምድር ለእስራኤላውያን ካህናት በየጊዜ ሐላፊነታቸውን በከፊል ቢወጡም ቤተመቅደሱ ግን ሙሉ አልነበረም።

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተጠየቀው ጥያቄ ተገቢ መልስ ሰጠ ማለትም፡- የመስቀሉ ስራ በ70እ.ም.ላይ የመጨረሻውን መጀመሪያ አገኘ ማለት አለመሆኑን ልብ ማለት ተገቢ ነው። የዚህም ምክንያቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከ70 ዓመተ ምህረት ቀድሞ በ33-36 ዓ.ም ላይ ራሱን ለመሲህይቷ ሕብረተሰብ ሰጥቷልና ስራውም ተጠናቆ «ተፈፀመ» በማለት የቤተመቅደሱን መጋረጃ ለሁለት ተርትሮታል።

አዲስ ኪዳን ከመስቀሉ ስራ ማግስት ጀምሮ ክርስትና ጠባብ እምነት ሳይሆን «ለዓለሙ ሁሉ ኢየሱስ መስዋዕት መሆኑን የሚገልፀው ወንጌል ነው የተተረከው» እስራኤልና እስራኤላውያን ምንም አይደሉም፤ አንድ ሕዝብ ከመሆን ባሻገር ለዚህ ሕዝብ ብቻ ኢየሱስ በመመለስ ራሱን ይገልጣል

ማለት ከማይወጡት ተግዳሮት ጋር መገናኘት ነው። ምክንያቱም በክርስቶስ የተመሰረተችው ማህበረሰብ፡- ሁሉን ጠርታለች። ሁሉን ይዛለች። ለእነርሱ ሁሉ ነው፡- የኢየሱስ መመለስ ትርጉም የሚሰጠው። ለዚህም ነው የዮሐንስ ራዕይ፡- ስብስቡን ሲገልጠው፡-

> *«መፅሐፉን ለመውሰድና ማህተሞቹን ለመክፈት የተገባህ ሆነሀል፣ ምክንያቱም አንተ ታርደሀልና፣ በደምህም ከየነገዱ፣ ከየቋንቋው፣ ከየወገኑ፣ ከየሕዝቡ ሁሉ ሰዎችን ለእግዚአብሔር ዋጅተሀል ለአምላካችንም የካህናት መንግስት እንዲሆኑ አድርገሀቸዋል በምድርም ላይ ይነግሳሉ» ራዕ. 5፡9-10 አለ።*

ይህን የመሰሉ ገለፃዎች ናቸው፤ አዲስ ኪዳንን የሞሉት ከዚህም የተነሳ የኢየሱስ ዳግም መመለሱ እነዚህን ሁሉ በጠቀለለ መልክ የሚሆን እንጂ ለሕዝበ እስራኤል ብቻ ሆኖ ጠቦ አይቀርም።

## አጠንፍፎ የመገናኘት አዝማሚያና
## የፀጋ ስጦታዎች የድምዳሚ ጭብጦች

ሰባውያን የኢየሱስ መመለስ እርግጥ ስለነበረ ነበር፡- አማኞች ያላቸውን ሁሉ የሸጡት የሚል ትንታኔን በሐዋሪያት ስራ ገለፃ ላይ ተነስተው ያስተምራሉ።

እርግጥ ነው፤-ሐዋ 4፡32-33 *«አማኞች ሁሉ አንድ ልብና አንድ ሀሳብ ነበራቸው ማንም ሰው «ይህ የእኔ ነው» የሚለው ነገር አልነበረውም በመካከላቸውም ሁሉ ነገር የጋራ ነበር፤ ሐዋሪያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሳኤ በታላቅ ሀይል ይመሰክሩ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ የእግዚአብሔር ፀጋ ነበር፤ መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ ገንዘቡን ያመጡ ስለነበር በመካከላቸው አንድም ችግረኛ አልነበረም»* ይህ ገለፃ አማኞች ኢየሱስ በቶሎ ይመጣል በማለት ያደረጉት እርምጃ እና የመጠባበቃቸው መለኪያ ነው ብሎ ማመን አያዋጣም።

ይልቅስ ወንጌል በገንዘብ አቅም ተደግፎ በአንድ ልብ መሆን «ትንሳኤውን» በቅጡ ለማብሰር፣ ሁሉም ያለውን በመሸጥ ለጋራ አገልግሎት ማዋሉ የወቅቱን ችግር ለመቅረፍ ሁነኛ መንገድ ነበር፤ ክርስትና ገና ጨቅላ ሆኖ መንቀሳቀስ ባለበት ወቅት የሚያዘልቁ እና የማያዛልቁ አተገባበሮች በጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ ታይተዋል። ይህ ሀብትን ሸጦ በአንድ መሆን ግን ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ውጭ በሌሎች ዘንድ ተግባራዊ መሆኑ አልተፃፈም፤ አልተነበበም፤ ይልቅስ፤- ከሐዋሪያት ስራ በኋላ እንደተፃፉ የሚታመንላቸው ቅዱሳት መጽሐፍት የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም መምጣትና በቅድስና በትጋት የመጠበቅ ሐላፊነትን ገለፁ፤ ፃፉም። በዚህም የኢየሩሳሌም አማኞች በገዛ ዘመናቸው ኢየሱስ ይመጣል በሚል ውጥረት ውስጥ አልገቡም።





በተያያዘም በ1ቆሮ 1፡7-8 *«ስለዚህ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ በመጠባበቅ ስትኖሩ ምንም ዐይነት መንፈሳዊ ስጦታ አይጎድልባችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ቀን ያለነቀፋ ሆናችሁ እንድትገኙ እርሱ እስከ መጨረሻ ፀንታችሁ እንድትኖሩ ያደርጋችኋል»* የሚለው የሐዋሪያው ጳውሎስ መልዕክት ለቆሮንቶስ ይደርስ ዘንድ አድርጉዋል፤የዚህን አውዳዊ ትርጉም ስንመለከት፡- በ15 ምዕራፎች ውስጥ መደናገርን ከፈጠሩት የፀጋ ስጦታዎች አጠቃቀም ላይ ማረሚያ መስጠት ዋንኛ ተግባሩ መሆንን ያሳውቃል። ለዚህም ከምዕራፍ 12-14 ሰፊ ገለፃውን አኖረ። በዚህም መግለጫ «ለአማኞች ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እንደ ወደደ የፀጋ ስጦታን እንደሚሰጥ ያንንም በአግባቡ ለአካሉ መገንባት ማዋል የእያንዳንዱ አማኝ ሐላፊነት መሆኑን በማረጋገጥ ይጠናቀቃል።

ሰባውያን ግን ገና ከደብዳቤው መነሻ ላይ በመገኘት የፀጋ ስጦታዎች ውጤታማ ሆነው ያገለገሉትና የታሰቡት እስከ 70 ዓ.ም ድረስ ያሉት ስራዎች በአግባቡ እንዲፀኑና እንዲረጋገጡ ነበር፤ ኢየሱስ ከተመለሰ በኋላ ያለው የቤተ ክርስቲያን ሥራ ከተፈጥሮ ስጦታ የተነሳ ይቀጥላል ይላሉ። ይህ ግን የክርስቶስን ቤ/ክ ሕያው ሆና ላለፉት 2000 ዓመታት የመዝለቋን አቅም መርሳት ነው።

## ሰባውያንና የተሰሎንቄ አማኞች

ጳውሎስ በተለያዩ ጊዜያት ሁለት የተለያዩ ችግር ፈቺ መልዕክቶችን በተሰሎንቄ ላሉት አማኞች ፅፏል።

በ1ተሰ4፡16-18 ላይ «የትዕዛዝ ድምፅ፣ የመለከት አለቃ ድምፅ፣ የእግዚአብሔር መለከትም ይሰማል፤ ጌታ ራሱም ከሰማይ ይወርዳል፤ በክርስቶስ አምነው የሞቱትም አስቀድመው ይነሳሉ፤ ከዚህ በኋላ እኛ በሕይወት የምንገኘው ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን ለዘላለምም ከጌታ ጋር እንሆናለን ስለዚህ በዚህ ቃል እርስ በርሳችሁ ተፅናኑ» ይህ ቃል ኢየሱስን በዳግም መመለሱ በመጠባበቅ ይፅናኑ ዘንድ ያደርጋል። ይህ የጳውሎስ ገለፃ ግን በአንዳንድ አማኞች ዘንድ ኢየሱስ ዛሬ እንደሚመለስ በማስቀጠር ብዙዎች ስራ ፈቶች ሆኑ፣ ብዙዎች አግባብነት ያለውን የሕይወት አኗኗር በተሳሳተ ሁኔታ ተረጎሙት፤ ከዚህም የተነሳ ማረሚያ መስጠት ተገቢ ነበር፤ ማረሚያው ኢየሱስ ቶሎ እንደሚመጣ በመቁጠር ቀኑን ለመወሰንና ለማቅረብ ወይም በዚህ ጊዜ ይመጣል ማለታቸውን ትተው የአኗኗር ስልታቸውን በብዙ አቅጣጫ እንዲያዩት እንዲህ ሲል መከራቸው 2ተሰ 2፡1-3 *ወንድሞች ሆይ ስለጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱም ስለ መሰብሰባችን ይህን እንለምናችኋለን በመንፈስ መገለጥ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደተላከ መልዕክት የጌታ ቀን ደርሷል ብላችሁ ፈጥናችሁ ከአእምሮአችሁ አትናወጡ አትደንግጡም ማንም ሰው በምንም መንገድ አያታላችሁ...»*

እንግዲህ ከዚህ መልዕክት በሁዋላ መደናገጥ፣ ትጥቅን መፍታት አያስፈልግም፤ ይልቅስ ኢየሱስ የሚመጣበትን ቀን ማንም አያውቅምና ምልክቶቹን በመከታተል፤ በፍቅር ኢየሱስን በማሰብ መኖር ምርጫቸው ሊሆን መገባቱን አበሰራቸው።

ይህ ገለፃ እውን ኢየሱስ እንደ ሰባውያኑ በ70 ዓ.ም የመመለሱ እምነት ልክ ቢሆን ኖሮ የእግዚአብሔር መንፈስ ሐዋሪያውን ተጠቅሞ ይህን መልዕክት ባላስተላለፈ።

## ሰባውያኑና 70 ዓ.ም

እስራኤላውያን በስደት፣ በግዞት፣ በምርኮኝነት በመኖራቸው ይታወቃሉ፤ ዛሬም ቢሆን እስራኤላውያን መከረኞች ናቸው፤ ስነ መስተዳድራውያን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜን «እንደ ወረደ» ያለ ታቃስ ስልት በመተርጎም የእስራኤልን ግዛት ፍልስጤማውያን መቶ በመቶ ሊጋሩት አይገባም በሚል አቋም የእስራኤላውያን መከረኝነት እያስቀጠሉዋቸው ይገኛል።

ሰባውያን ግን እስራኤላውያን በታሪክ ዘመናቸው የመከራን ቁንጮ የቀመሱት እና ገፈቱን የጠጡት በ70 ዓ.ም ብቻ ነው ይላሉ። ይህንንም ሲገልፁት በጊዜው ሮማውያን የፈፀሙትን ግፍ በዓለም ታሪክ ውስጥ የማይደገም መሆኑን በማረጋገጥ ነው።

ልኩ ግን በዓለም ታሪክ ከ70 ዓመተ ምህረት በፊትም ሆነ በኋላ ባሉት የታሪክ ገለፃዎች ከ70 ዓ.ም የበለጡ ጥቃቶች በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ተደጋግሟል። ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት በ6ኛው ክፍለ ዘመን አሶራውያንና ባቢሎናውያን ከባድ ጥፋት በእስራኤላውያን ላይ ፈፅመዋል፤ ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ጀርመኖች አይሁዳውያንን ለማጥፋት ባደረጉት ጭፍጨፋ ስድስት ሚሊዮን እስራኤላውያን ሕይወታቸውን አጥተዋል።

ይልቅስ 70 ዓ.ም በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ልክ እንደ በዐለ ሀምሳ የሚታይ ዓመት አይደለም፤ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በተለያዩ ዘመኖች የተካሄዱ ጉባኤዎች ከ70ዓ.ም.በበለጡ ታሪካቸው ሊነሳ ይገባል፤ ከእነርሱም ውስጥ በእግዚአብሔር መንፈስ አማካኝነት የተፃፉትን በመለየት ስልጣናዊ መፅሐፍትን መወሰን የተቻለበት ጊዜ 70 ን በልጦ መቆም አለበት።

## የቅዱሳት መጽሐፍት ውሳኔ ከ70 ጋር ሲተያይ

የአሌክሳንድሪያ ቤተክርስቲያን መሪ የነበረው አትናትዮስ በታሪክ ውስጥ የፈፀመው ተጋድሎ ብዙ ነው፤ በ323ዓ.ም.በኒቂያ በተደረገው ጉባኤ ላይ በመገኘት አርዮስን በቅዱሳት መጽሐፍት እና በአመክንዮ አገላለፅ በመጠቀም ረትቷል። ኢየሱስ ክርስቶስም ፍፁም ሰው ብቻ





ሳይሆን ፍፁም አምላክ መሆኑን ተንትኗል ይህም በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ አለው።

ይኸው ሰው በእግዚአብሔር እስትንፋስ የተፃፉትን፣ መለኮታዊ ስልጣን ያላቸውን መጽሐፍት በመለየት ወደ ውሳኔ የመድረስ ተፈላጊነትን ያጣቆመ ይህንንም ከውሳኔው በፊት ለተግባራዊነቱ ያመቻቸ የእግዚአብሔር ሰው ነው።

ሀያ ሰባቱ የአዲስ ኪዳን መጽሀፍት በብዙ ጥንቃቄ፣ በመለኮታዊ ምሪት እና ባዘጋጁት የመለያ ድንጋጌ በመጠቀም መጽሐፍቱ ተለይተዋል።

## የመነሻ መጠቅለያ

እንግዲህ እነዚህ የተለዩት መፅሐፍት በቤተክርስቲያን አባቶች ሲለዩ በ70 ኢየሱስ ስለመመለሱ እና ተስፋው ስለመጠናቀቁ ምንም የሰሙትና የተረዱት አልነበረም ማለት ነው፤ በመረጧቸው በ27 ቱም መጽሐፍ የኢየሱስ ዳግም መመለስ የሚጠበቅና የሚናፈቅ፣ የሚዘጋጁበትና የሚጓጉለት መሆኑን የሚገልፁትን ሁሉ ሳያርሙ የተዉት ወይም በእግዚአብሔር መንፈስ እንዳልተፃፈ ያልቆጠሩት በቂ ምክንያት ኖሯቸው ነው። ልብ እንበል የቅዱሳቱ መጽሐፍት በ4ኛው ክፍለ ዘመን መደርጀት፣ በየጊዜው የተካሄዱ ጉባኤያት በኢየሱስ ዳግም መመለስ ላይ በማተኮር ቀኖናዎችን ማደርጀታቸው በእርግጥም ኢየሱስ ዳግም ሊመለስ ያለው ጌታ መሆኑን ያበስራል፤ ይህ ደግሞ ዳግም መጥቷል ላይ ሳይሆን ዳግም በመመለሱ ላይ በማተኮር እንኖር ዘንድ ያነቃቃል።

## የመድረሻ መጠቅለያ

የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥሪ አንድ ቀን በስራ ላይ ዋለልኝ፤ ሙት መንፈሴን እግዚአብሔር ሕያው አደረገው፤ በሕያውነቱ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስን ብሩህ አድርጎ አሳየኝ፤ የዳግም መወለዴም ሚስጥር ከዚሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ብቻ ተያይዞ ፍፃሜ ማግኘቱን መንፈስ ቅዱስ አሳወቀኝ።

ከዚያን ግዜ ጀምሮ እየተነሳሁ እየወደቁ፤ እየወደቁ እየተነሳሁ፤ ሙሉ ሰው በክርስቶስ ለመሆን ደፋ ቀና እላለሁ፤ የዚህ ደፋ ቀና ማለት መነሻው የአስራ ዘጠኝ ስድሳዎቹ የመጨረሻ አመታት ነበሩ፤ ዛሬ ላይ ተቁሞ አመቱ ሲሰላ የምዕተ ዓመቱን አንድ አራተኛ አጠናቆ በላዩ ላይ በርካታ ዓመታትን ይጨምራል።

በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ተያያዥነት ያላቸውንና የሌላቸውን መሰረታዊ አስተምህሮዎች በወጉ ለመረዳት የአቅሜን ሁሉ አድርጌያለሁ፤ በአስተምህሮተ እግዚአብሔር፣ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በመንፈስ ቅዱስ፣ በሰላሴ፣ በሀጢአት፣ በድነት፣ በቤተክርስቲያን እና በመሳሰሉት ሁሉ የእግዚአብሔር የሆነውን ሀሳብ ለመረዳት በቀዳሚነት ከቅዱስ መፅሐፍ ከዚያም በአጋዥ መፅሐፍት እና ከመሰል ዘርፎች ሁሉ ዕውቀትን ሸምቻለሁ፣ ገናም እሸምታለሁ።

በዚህ ሽመታ ውስጥ በ«አለፍገደም» በ«መለስቀለስ» ነካከቼ የምተወው ርዕሰ ትምህርት አሁንም በክፍል አንድ እንደገለፅኩት **ስነ-ፍፃሜ ነው፡** በጊዜው ስለ መጨረሻው ዘመን ብዙ አልጨናነቅም ነበር። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ በተብራራ መልኩ እንዳላስቀመጠው በመቁጠር ይሁን፣ ወይም ብዙዎች የእግዚአብሔርን ሀሳብ ሳይሆን የልባቸውን ፈቃድ ዘርዝረው ተርተው «እመኑ» በሚል መንፈስ በመነሳሳታቸው ይሁን፣ ወይም በሌላ ትኩረት አልሰጠሁትም፤ እንዲህም ብል አንድን ቁም ነገር ሳልዘነጋ ነው፤- እሱም **«ጊዜው ሲሞላ ኢየሱስ ክርስቶስ በአካል ሲያርግ በነበረበት ይዞታ አንድ ቀን ይመለሳል»** እላለሁ፤ የት? ለምን? በሚሉ ሞጋች ተያያዥ ጥያቄዎች ላይ አተኩሬ አስተምህርውን ከሌሎቹ ጋር ተሳሳሪነት ወይም ተያያዥነት እንዳለው በመቁጠር ዓመታቴን ለዚህ አልገበርኩም።

አሁን አሁን ግን ከሰው የሚፈልቁ ምላሽ የሚፈልጉ ጥያቄዎች ሲመጡ «ትውልዱም» ተገቢ መልስን ከቱባ ሰነድ ጋር ሲፈልግ ስለ እራሴና ስለ እነርሱ ስል እንደአቅሚቴ መዘጋጀት ጀምሬያለሁ፤ ታዲያ በዚህ ዝግጅትና አደረጃጀት አንዱ ሁነኛ ፅኑ መርህ አለኝ፤ እሱም የሰው ልጅ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ስለኖረ በ16ኛው፣ በ10ኛው ክፍለ ዘመን ከኖረው አማኝ ወይም የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ከነበረው የክርስቶስ ተከታይ ያኔ ተሰውሮ የነበረ ዛሬ ደግሞ የሚያገኘው መንፈሳዊ መገለጥ አይኖርም» በማለት እፀናለሁ።

የዚህ መተማመኛም፡- ሰው ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ አፈጣጠሩ አዝጋሚ ለውጥ ወይም ሒደታዊ ሳይሆን እግዚአብሔራዊ በመሆኑ በሁሉም ሰው ላይ የእግዚአብሔር ማህተም በራሱ ላይ ኖሮ በማለፉ፣ ሰው በእግዚአብሔር በገዛ አምሳል መልክ ከመፈጠሩ የተነሳ የሰለጠነ ያልሰለጠነ፣ ኋላ ቀር ዘመናዊ የሚባል ሰው እንዳይኖር ሆኗል።

ሌላኛው መተማመኛ የክርስቲያኖች ምስስል ነው፤ ክርስቲያን መሆን የሚቻለው ክርስቲያን ለመሆን በመፈለግ ወይም በመመኘት ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር አብርሆተ መንፈስ ቅዱስንና መለኮታዊ ጥሪን በማገጣጠም በሰው ሕይወት ውስጥ የሚያደርገው የታምሩ ውጤት ነው፤ ይህም በክርስቶስ የሆኑትን በሙሉ የጋራ የሆነ ሀብትን ያስገኝላቸዋል፤ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ በመሆን ቅዱስ ቃሉን በእርሱ እገዛ ይረዱታል፤ ይማሩታል፤ ያምኑታል፤ ይኖሩበታል፤ከዚህም የተነሳ የጋራ ዕውነትን ሕዝበ ክርስቲያን በእኩል አቅም ወይም በተመጣጠነ ሁኔታ ይረዱታል፤ ይህ ደግሞ ከ100 ዓመት በፊት የነበሩ አማኞች ያላዩት ያልተገለጠላቸው ድንገት በእኛ ዘመን መጣ እንዳንል ያግዘናል።

የመጨረሻው መተማመኛ ለእግዚአብሔር ቃል፣ ለታሪክ እና ለተገጣጠመው ሙሉ ምስል መስራት የተገቢ ተገቢ መሆኑን ማመኔም በዚህ የስነ ፍፃሜ ትምህርት እና ዝግጅት ላይ ትኩረት እንድሰጥ አስገድዶኛል።





ይህ ዝግጅት የእግዚአብሔር መንፈስ በወጥነት በአማኞች ሁሉ ዘንድ መስራቱ እርግጥ መሆኑን ያረጋግጣል፤ በዚህም በስነመለኮት ትምህርት ቤቶች በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ለማመሳከሪያ ወቅታዊ ፅሑፎችን ማጣቀሳቸው ተቀባይነት በስራቸው ላይ የመስጠቱን አቅም ያፈዛል፤ በእግዚአብሔር ጉዳይ ላይ ጥንታዊ ስራዎችም ከወቅቱ ፅሁፎች የተሻለ አቅም ሊኖራቸው ይችላል።

ከዚህም የተነሳ በ1937 እ.ኤ.አ ለህትመት በበቃው መፅሀፍ ላይ እፀናለሁ፤ ፕሮፌሰር ኩነር ምን ብለው ነበር? እላለሁ ከ70ዓመታት በፊት በተፃፈውየChristian Doctrine ስራቸው W.t. Conner ስነ ፍፃሜን በዋናነት አካቷል።

ሌላው በዚህ ዝግጅቴ ዋቢ አድርጌ የማቀርበው የ1884ን ስራ ነው፤ ይህ ደግሞ ከ120 ዓመት በፊት ተፃፈ፤ ታትሞም ለንባብ በቃ፤ Frederiw.Farrar በ «The Early Days of Christianity «The Apocalypse»የሚለው የስነ ፍፃሜ ምዕራፍ ዝርዝር ግንዛቤያቸውን አኑረው በጊዜው፤- ሁለቱም ወደ ጌታቸው ተሰብስበዋል።

እኔ ደግሞ የድካማቸውን ፍሬ ለብዙዎች ሊጠቅም በሚችል ሁኔታ እንደሚከተለው መጥኜ በማጠቃለያነት አቀርባለሁ፤ አቅርቦቴ መነሻን በዋናነት እነርሱን ያድርግ እንጂ ተሳሳሪ እና ተያያዥ አይቀሬ ጭብጦችንም ለምክክርና ለውይይት በሚረዳ ሁኔታ አሰነዳዳለሁ።

***

ክርስትና የውጀት ታሪክን ማዕከላዊ ያደረገ እምነት ነው፤ መቤዠት፤ ይህም ሰውን ከሀጢአት ለማዳን እግዚአብሔር የሰራውን ስራ ያፀናል፤ ድነት በባርነት ተይዞ የነበረውን ሰው ነፃ አውጥቶታል።

በእርግጥም ክርስትና መቤዠትን ወይም ውጀትን ማዕከል ያደርጋል ሲባል በክርስቶስ የተሰራው የሞቱና የትንሳኤው ጉልበት ቀጣይነት ኖሮት መደምደሚያው ከስነ ፍፃሜው ጋር ይተሳሰራል።

ድነታችን በመዳን ይቀጥላል፣ እንድናለን ብለንም ሙላቱን ያስናፍቀናል፤ መናፈቁም «ላም አለኝ በሰማይ ወተቷን የማላይ» በሚል ባዶ ተስፋ ላይ ተንጠላጥሎ ሳይሆን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከመሰረተው አብሮነት ጋር በመዝለቅ ወደ ዳርቻው የሚመጣ አኗኗር ነው፤ ከዚህም የተነሳ ስነ ፍፃሜ ተያያዥና ቀጣይነት ያለው ክርስቲያናዊ ህይወት እንጂ ድንገት የመጣ አዲስ መገለጥ አይደለም።

***

እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግስት ምንነት ላይ በመነጋገር ስለመጨረሻ ዘመን ወይም ስለ ስነ ፍፃሜ ለመዘከር የመንግስት መቤዠትን (The Kingdom of redemption) ተፈላጊነት ቅድሚያ እንስጥ ይህም ስለቀጣዩ ሕይወት ለመነጋገር ለቀጣዩ ኑሮ መነሻ የሆነውን የዛሬውን አኗኗርና ህይወት ማወቅ ያስፈልጋል፤ ይህ ደግሞ ነገ የዛሬ ተከታይ መሆኑን ያፀናልናል።

በመሰረቱ እንዲህ ተብሎ ሁሉን አቀፍ የእግዚአብሔር ልዐላዊነት በአግባቡ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተቀምጧል «በምድር ሁሉ ላይ ታላቅ የሆነው ንጉስ ልዑል እግዚአብሔር የሚያስፈራ ነው» (መዝ 47፡25 አመት) «...እግዚአብሔር የምድር ሁሉ ንጉስ ነውና ምርጥ ዝማሬ አቅርቡለት» (መዝ 47፡7) «እግዚአብሔር በህዝቦች ሁሉ ላይ ነግሶአል» (መዝ 27፡8 አመት) በማለት የመላው ዓለም ኑዋሪ ሕዝብ እሱ ብቻ ንጉስ መሆኑን ያረጋግጣል።

የ150 ምዕራፍ ባለቤት የሆነው መዝሙረ ዳዊት የእግዚአብሔርን በሁሉ ላይ ገዥነት በአግባቡ ያመላከተ መሆኑን «...እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አፅንቶአል መንግስቱም ሁሉን ትገዛለች...» (መዝ 103፡19) ካለ በኋላ «...እናንተ በግዛቱ ሁሉ የምትኖሩ ፍጥረቱ ሁሉ እግዚአብሔርን ባርኩ» በማለት ያዛል። (መዝ 103፡22 አመት)

ከዚህም የተነሳ በእርሱ ንግስና ስር ያልሆነ አንድም ሰው አንድም ሕዝብ አንድም ሀገር የለም፤ እሱ እግዚአብሔር ስለሆነ በሁሉ ቦታ ተገኝቶ ገዥነቱን ያፀናል፤ በእርሱ አምሳል የፈጠረው የሰው ልጅም በውስጡ በኖረው የስነ ምግባር ሕግ የተነሳ ራሱን አስገዝቶ ይኖራል፤ እግዚአብሔር ንጉስ ስለሆነ ግብፃውያንን ቢሆን፣ ባቢሎናውያንን፣ አሶራውያንን ቢሆን እስራኤልን ይቀጣል፤ ይፈርዳል፤ እሱ በሙሉ ዕውቀትና ዳኝነቱን ሁሉ ያበጃጃል፤ ከዚህምየተነሳ ንጉስነቱ ትናንትም ዛሬም ነገም ይኖራል።

***

በእስራኤል ላይ እግዚአብሔር ንጉስ ሆኖ መገለጡንም ልብ ማለት ተገቢ ነው፤ በቀደመው ኪዳን እግዚአብሔር አንድን ሰው በመምረጥ በእርሱ ዘር አማካኝነት ፈቃዱን ለመግለጥ ወስኗል። አብርሀም ተጠሪው ሰው ነበር፤ ከእርሱ ጋር እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገባ። ከዚያም ከነዓንን በመውረስ ለዓለም በረከት ሊሆኑ የሚችሉበትን ስራ ሰራ፤ (ዘፍ. 12፡1-3) ...እግዚአብሔር አብራምን እንዲህ አለው «አገርህን፣ ወገንህንና የአባትህን ቤት ትተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ሂድ ታላቅ ሕዝብ አደርግሀለሁ፤ ደግሞም እባርክሀለሁ፤ ስምህንገናና አደርገዋለሁ፤ ለሌሎችበረከት ትሆናለህ...





በምድር የሚኖሩ ህዝቦች በአንተ አማካኝነት ይባረካሉ» መነሻው ነው፤ ይህን ተፈፃሚ ለማድረግ በባርነት ከ400 ዓመታት በላይ የኖረውን ሕዝበ እስራኤል በሙሴ አማካኝነት በማውጣት በከንዓን ይኖሩ ዘንድ አደረጋቸው፤ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ንጉስ መሆኑን በአግባቡ የገለፀልን ሳሙኤል እስራኤላውያን የሚመራን ንጉስ አንግሰልን በማለታቸው አዝኖ ጉዳዩን ወደ እግዚአብሔር አመጣው በዚህ ግዜ እግዚአብሔር «ንጉሳቸው እንዳልሆን የናቁት እኔን እንጂ አንተን አይደለምና ሕዝቡ የሚልህን ሁሉ አድምጥ...» (1ሳሙ 8፡6-8) ካለው በኋላ እነርሱ ሰውን በላያቸው ላይ እንዲነግስ በመምረጣቸው ሊመጣባቸው የሚችለውን ክፉ ነገሮችን ሁሉ እንዲነግራቸው አስጠነቀቀው፤ እሱም ነግሮአቸው ሲያበቃ «ይቅርብን» እንደማለት «አይሆንም ንጉስ እንዲነግስልን እንፈልጋለን...» ብለው ፀኑ፤ እሱም ሳኦልን አነገሰባቸው።

ይህ ገለፃ እስራኤላውያን በጎረቤቶቻቸው ሀገራት ተፅዕኖና በዘመኑ በነበረው ዓለም አቀፍ የአኗኗር ስልት ጋር ለመኖር በመፈለጋቸው በፍቅር ያስተዳድራቸው እና ይመራቸው የነበረውን እግዚአብሔርን ትተው በሌሎች ነገስታት ተፅዕኖ ስር ወደው ወደቁ፤ ከዚህም የተነሳ የእግዚአብሔር ንጉስነት በእስራኤላውያን ላይ በየትኛውም ጉዳይ ላይ በአግባቡ ተፈፃሚ መሆን አልቻለም።

***

በትይዩ «ልበ መንግስት» በኢየሱስ መመስረቱንም በአግባቡ ማጤን ተገቢ ነው፤ እግዚአብሔር ዳዊትን እንዲህ አለው «ዕድሜህን ጨርሰህ ከአባቶችህ ጋር በምታንቀላፋበት ጊዜ በእግርህ እንዲተካ ከአብራክህ የተከፈለ ዘር አስነሳለሁ መንግስቱንም አፀናለሁ» (2ሳሙ 7፡12) በማለት የፀና መንግስት ባለቤት የሚሆን ከእርሱ ዘር እንደሚመጣ አሳወቀ፤ ይህ ደግሞ ሙሉ ተፈፃሚነቱን ያገኘው በኢየሱስ ነው። በእስራኤል ላይ እግዚአብሔር ንጉስ ሆኖ የሚገዛበትን ስርዓት እግዚአብሔር በኢየሱስ ላይ አደረገ፤ ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመጣ የሚያድን መድሀኒትና ንጉስ ሆኖ ነው የመጣው፤ ይህም ሰብዓ ሰገሎች በፊቱ ቀርበው በመስገዳቸው እንዲሁም በብሉይ ኪዳን ከዳዊት ጋር በመያያዝ የተነገሩ የተስፋ ቃሎች መፈፀሚያ እርሱ መሆኑ ተረጋገጠ፤ ከሩቅ ምስራቅ የመጡት ሰብዓሰገሎች ወደ ቤት በገቡ ጊዜ «ህፃኑን ከእናቱ ከማሪያም ጋር አዩት ተንበርክከውም ሰገዱለት» (ማቴ. 2፡11) በተያያዥም «...እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል ጌታ አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል። በያዕቆብ ቤት ላይ ለዘላለም ይነግሳል፤ ለመንግስቱም ፍፃሜ የለውም» (ሉቃ. 1፡32-33 አመት) የሚለውን ቃል ማጤን ተገቢ ነው፤ በሐዋ. 2፡25-36 ባለውም ገለፃ ላይ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ የእግዚአብሔር መንግስት ምንነት በኢየሱስ መገለፁንና ለዳዊት ተገብቶ የነበረው ተስፋ ተፈፃሚነት ማግኘቱን አበሰረ «...ወንድሞች ሆይ ከቀደሙት አባቶች ዳዊት ሞቶ እንደተቀበረ፣ መቃብሩም እስከ ዛሬ ድረስ በመካከላችን እንደሚገኝ በድፍረት መናገር እችላለሁ፣

ነብይ በመሆኑም እግዚአብሔር ከዘሮቹ አንዱን በዙፋኑ ላይ እንደሚያስቀምጥ በመሐላ ቃል የገባለት መሆኑን ዐወቀ ይህንን አስቀድሞ በማየቱ እርሱ በሲኦል እንደማይቀርና ስጋውም እንደማይበሰብስ ስለ ክርስቶስ ትንሳኤ ተናገረ፤ ይህን ኢየሱስ እግዚአብሔር ከሞት አስነሳው እኛም ሁላችን ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ካለ በኋላ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ከአብ ተቀብሎ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው... እግዚአብሔር ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ ይረዳ...» በማለት ለዳዊት የተገባለት ሁሉ በኢየሱስ ፍፃሜ ማግኘቱን አረጋገጠ።

ከዚህም ተነሳ የኢየሱስ መምጣት ከመንግስቱ መምጣት ወይም መቀጠል ጋር ተያያዥነት አለው ኢየሱስም ሆነ መጥምቁ ዮሐንስ (ማቴ 3፡2 እና ማር 1፡15) የእግዚአብሔር መንግስት መምጣቷን ነበር ያሳወቁት፡- ይህ መንግስት እስራኤላውያንን ከሮማውያን ገዥነት ነፃ የሚያወጣ ወይም ፖለቲካው ስልጣንን በመያዝ አይሁዶች እንደሚጠብቁት በተአምራት ታጅቦ አመራሩን ይፋ የሚያደርግ መንግስት አልነበረም፡- ይልቅስ የእግዚአብሔርን ንጉስነት የዳግም ልደት ባለቤት የሆኑት እንዴት የመንግስቱ መገለጫ ሊሆኑ እንዳላቸው የሚገልጠው ነው መንግስቱ።

ሉቃ. 17፡20-21 ሰዎች የእግዚአብሔር መንግስት መቼ እንደምትመጣ ኢየሱስን በጠየቁት ጊዜ «የእግዚአብሔር መንግስት በሚታዩ ምልክቶች አትመጣም ሰዎችም እዚህ ነው! ወይም እዚያ ነው! ማለት አይችሉም፤ እነሆ የእግዚአብሔር መንግስት በመካከላችሁ ናትና...» አላቸው በዮሐ 3፡3ም «እውነት እውነት እልሃለሁ ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም» የሚለው ምላሽ ለኒቆዲሞስ ግር ቢያሰኘውም ልከኛው መገለጫው ግን ኢየሱስ የሚገዛው መንግስት፣ ዳግም በመወለድ በተቀላቀሉት ሁሉ ላይ የሚነግስ መንግስት ነው።

ይህን ኢየሱስ በሰዎች ልብ ላይ የሚያስተዳድርበትን አገዛዝ ባለመረዳት ደቀመዛሙርቱ «ጌታ ሆይ የእስራኤልን መንግስት መልሰህ የምታቋቁምበት ጊዜው አሁን ነውን? (ሐዋ 1፡6 አመት) የሚል አጀንዳ ይዘው ቀርበው እንደነበር አይዘነጋም፤ ለዚህም ጥያቄ ኢየሱስ በዚህ ቀን ብሎ ምንም መልስ አልሰጠም፤ ወደ ህሊናቸውና ወደ ልቦናቸው ተመልሰው ያወጠነጥኑ ዘንድ ተዋቸው። ሐዋሪያው ጳውሎስ የዚህን መንግስት ምንነት ሲያብራራ «የእግዚአብሔር መንግስት በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ፅድቅ፣ ሰላምና ሐሴት ነው እንጂ የመብልና የመጠጥ ጉዳይ አይደለም» (ሮሜ 14፡14 አመት) አለ።

የእግዚአብሔር መንግስት ገና ወደ ፊት ትመጣለች ብሎ የፊት የፊቱን ብቻ ማየት ተገቢ አይደለም፤ ዮሐንስ ክርስቲያኖች እየተሰደዱ ባለበት ዘመን እየኖረ እሱም የዚሁ መከረኝነት





ተሳታፊ ሆኖ ስለመንግስቱ ተካፋይነት በአግባቡ ያስረዳ ነበር፤ ማንም የኢየሱስን ጌታነት፣ ንጉስነትና ገዢነትን በማመን ታዞ የሚኖር ሁሉ የዚህ መንግስት ተካፋይ ነው። ራዕ 1፡9 «እኔ ወንድማችሁ ዮሐንስ ከእናንተ ጋር አብሬ በኢየሱስ መከራ ውስጥ መንግስቱን ትዕግስቱንም ተካፋይ የሆንሁ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክርነት ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ» ይላል፤ በዚህም ገለፃው እሱ ራሱ በዚያው ወቅት የመንግስቱ ተካፋይ ሆኖ ነበር፡፡

እርግጥ ነው መንግስትን ስናስብ ገዢን ወይም ንጉስን ነጥለን ማየት የለብንም እነዚህ ሁለቱ ባሉበት ነው «ንጉስ-መንግስት» ማለት የሚቻለው ኢየሱስ ንጉስ ነው ግን በአካል አሁን በዚህ የለም። እናም መንግስቱ መፃኢ ናት ቢባል ምን ነበር? የዚህ ምላሽ ንጉሱ በመካከላችን በእርሱ መንፈስ አማካኝነት ተገኝቷል። መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ውስጥ አድሯል «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ ከእንግዲህ እኔ አልኖርም ነገር ግን ክርስቶስ በውስጤ ኖራል» (ገላ 2፡20 አመት) «...በውስጥ ሰውነታችሁ እንድትጠነከሩ ከክብሩ ባለጠግነት በመንፈሱ በኩል ኃይል እንዲሰጣችሁ እፀልያለሁ ይኸውም በእምነት ክርስቶስ በልባችሁ እንዲያድር ነው» (ኤፌ 3፡16-17 አመት)

አይሁዶች የኢየሱስን ሚስኪንነት፣ ወደ ሞት መሄድ እና በተዋረደ አሟሟት መሞቱን በመመልከት የሮማውያን ቀንበር አለመሰበሩን በማየት የእግዚአብሔር መንግስት የተላለፈች ያህል ደቀመዛሙርቱ አምነዋል፤ ቆጥረዋል፤ እውነቱ ግን የእግዚአብሔር መንግስት በሰዎች መካከል ነበረች፤ ይህማ ካልሆነ ኢየሱስ ሲወለድ «ሰላም በምድር ለሰዎችም በጎ ፈቃድ» በማለት ከላይ የመጡ መላዕክቱ ባልዘመሩለት ነበር፤ የሰላሙ ንጉስ ሰላሙን በምድር ያሰፍን ዘንድ የዛሬ 2000 ዓመት መጥቷል፤ ይህም በመንግስቱ ውስጥ ቀጣይ በመሆን ዘልቋል።

ማቴ 13 በኢየሱስ ሁነኛ ምሳሌዎች የተሞላ ምዕራፍ ነው፤ ይልቁኑ ከቁጥር 31-35 ያለው ስለ እግዚአብሔር መንግስት ወይም ስለ መንግስተ ሰማይ ባህርይና ምንነት ያብራራል፤ ይህንንም በሰናፍጭ እና በእርሾ መስሎ አቅርቦታል፤ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አብራሪዎች አውዳዊ ፍቺን በቀዳሚነት ከመስጠት በስመ እርሾ በመነሻ ላይ ከተዋወቁት ጋር በማስተያየት ብቻ መጥፎ ጎኑን ያወጣሉ፤ ያላለውን ሊሉለት ይሞክራሉ፤ ይህ ግን መቼም አያዋጣም። ሁሉም መግለጫ በአግባቡ ይፈረጃል፤ ከዚህም የተነሳ ኢየሱስ ክርስቶስ «የሰናፍጭ ዘር ከሌሎች ዘሮች ሁሉ ያነሰች ብትሆንም ስታድግ ግን ከቁጥቋጦዎች ሁሉ በልጣ የሰማይ ወፎች መጥተው በቅርንጫፎቿ ላይ እስኪያርፍ ድረስ ዛፍ ትሆናለች በማለት መስፋፋቷን፤ እርሾንም በማንሳት፡- ዱቄቱን በሙሉ እስኪቦካ ድረስ ያብላላው እርሾ መሆኑን በመግለፅ የእግዚአብሔር መንግስት ከክርስቲያኖች ክርስቲያናዊ አኗኗር የተነሳ በህብረተሰቡ ዘንድ ሁነኛ ለውጥን በማምጣት ትስፋፋለች፤ ይህም የእግዚአብሔር መንግስት በመካከላችን መሆኗን ይገልጡበታል።

ኢየሱስ መንግስቱ በሰፋ ቁጥር አመፅ፣ ጥፋት እርኩሰት ከጊዜ ወደ ጊዜ አቅሙ እየተረታ ሲሄድ ይታያል፤ ለዚህም ነው «እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» የሚለው መርህ እውነት የሆነው። (ማቴ 5:48) «ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ይሁን»ም ምላሹን የሚያገኘው፤ ኢየሱስ በሚገዛው መንግስት ውስጥ ነው። ይህ ደግሞ ልደትን ባገኙት የመንግስቱ አባላት ተፈፃሚ ይሆናል። የዚህን እውነተኝነት How Christianity changed the world የሚለውን የ Alvin H. Sch Midt ን መፅሀፍ ማንበብ በቂ ግንዛቤን ያስገኛል።

***

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን የዘላለሙ መንግስት መንደርደሪያም ከኢየሱስ ዳግም መመለስ ጋር ተያያዥ መሆኑን ደግሞ ልብ ማለት ተገቢ ነው፤ ይህን በቅጡ ለመረዳት እነዚህን ከፍሎች በሰከነ ሁኔታ ማንበብ ይገባል።

ማቴ 13:43 *«...በዚያን ግዜ ፃድቃን በአባታቸው መንግስት እንደፀሐይ ያበራሉ ሰሚ ጆሮ ያለው ይሆን ይስማ!»*

ማቴ 25:34 *በቀኝ በኩል ያሉትን «እናንተ አባቴ የባረካችሁ ኑ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግስት ውረሱ...»*

ማቴ 26:29 *...በአባቴ መንግስት ከእናንተ ጋር በአዲስ መልክ እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከአንግዲህ ከዚህ የወይን ፍሬ አልጠጣም»*

1ቆሮ 15:24 *ከዚያም ግዛትን፣ ስልጣንና ኃይልን ሁሉ ከደመሰሰ በኋላ መንግስትን ለእግዚአብሔ አብ ሲያስረክብ ያን ግዜ ፍፃሜ ይሆናል...*

2ጢሞ 4:1፣ 18 *በእግዚአብሔር ፊት እንዲሁም በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ባለው በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት መገለጡንና መንግስቱን በማሰብ ይህን አደራ እልሃለሁ... ጌታ ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል፤ ወደ ሰማያዊ መንግስቱም በሰላም ያደርሰኛል፤ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን አሜን።*

ከላይ የተነበቡት ክፍሎች ሞትን፣ ዳግም መመለሱን፣ ትንሳኤንና ፍርድን፣ ገነትና ሲኦልን ከግምት በማስገባት እናጤናቸው ዘንድ ግድ ይለናል፤ ሞት «መለየት» የሚለውን ትርጉም ይይዛል፤ ሀጢአት ወደ ሰው ሲገባ በቀዳሚነት የዘላለም ሞት ወይም በመንፈስ ሙት መሆን ሲመጣ እሱን አስከትሎ በአካል መፍረስን እንዲሁም ከዚህ ምድር አጠቃላይ ግንኙነት ጋር አስተሳሳሪ የሆኑት ሁሉ ስራቸውን





በማቆም መለየትን ሞት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል፤ ብሉይ ኪዳን በጠለቀ ሁኔታ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት ምንነት በአግባቡ ያብራራ አይመስልም፤ አዲስ ኪዳን ግን በአግባቡ ሁሉን አደርጅቶ ፅፏልና ሞት ተኮር የሆነውን አስተምሮ ለማጣጣም መጣር ተገቢ ነው።

ዘፍ 2:17 «ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ ምክንያቱም ከእርሱ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞታለህ ያለበትን ቃል አዳምና ሔዋን ተላልፈውታል፤ በዚያን ግዜ ሙሉ ለሙሉ ከእግዚአብሔ ተለይተዋል እንጂ ስጋዊ ሞትን አልሞቱም ነበር። ይህ ግን ቆይቶም ቢሆን በመምጣት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

መዝ 6:5 *በሞት የሚያስታውስ የለምና በሲኦልስ ማን ያመሰግንሀል?*

መዝ 30:9 *በእኔ ወደ ጉድጓድ መውረድ (በመሞቴ) ምን ጥቅም ይገኛል?ዐፈር ያመሰግንሀልን? ታማኝነትህንስ ይናገራል?*

መክ 9:10 *እጅህ የሚያገኘውን ስራ ሁሉ በሙሉ ኃይልህ ስራው ልትሄድ ባለው መቃብር ውስጥ መስራትም ሆነ ማቀድ ዕውቀትም ጥበብም የለም።*

ኢሳ 38:18 *ሲኦል አያመሰግንህም፤ ሞት አያወድስህም፡ ወደ ጉድጓድ የሚወርዱ የአንተን ታማኝነት ተስፋ አያደርጉም።*

እነዚህን የመሰሉ ክፍሎች ከሞት በኋላ ወይም በሞት ውስጥ ምንም አይነት ከንውን እንደሌለ አመላካች ይመስላሉ፤ ከዚህም የተነሳ ሳይሆን አይቀርም ሕዝቅያስ እንደሚሞት ሲነገረው የተጨነቀው።

ሐዋ 2:25 *ጌታን ሁል ጊዜ በፊቴ አየዋለሁ እርሱ በቀኜ ነውና ከቶ አልታወክም።*

ሐዋ 13:13 *ኢየሱስንም ከሙታን በማስነሳቱ ለእርሱ የገባውን ቃል ለእኛ ለልጆቻቸው ፈፅሞአል።*

ማር. 12:24-25 *ኢየሱስም የምትስቱት እኮ ቅዱሳት መጽሐፍትንና የእግዚአብሔርን ሀይል ስለማታውቁት ነው፤ ሙታን በሚነሱበት ጊዜ እንደ ሰማይ መላዕክት ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡም አላቸው፤በዚህም አዲስ ኪዳን ሞትንና በሞት ወቅት ከሞት በኋላም ስላለው ጉዳይ የተሻለ ፍንጭ እንደሰጠን ልብ ማለት እንችላለን።*

ይህን ደግሞ ለማረጋገጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በገለጣቸው ጭብጦች ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ይኑረን።

ጌታችን ኢየሱስ ሞትን ይልቅኑ ሲጋዊ ሞትን በተመለከተ «ይህ ሁሉ ግርግርና ለቅሶ ምንድን ነው? ብላቴናይቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም» አላቸው ማር 5፡39 በዚህም ሞትን ከመኝታ እና ከእንቅልፍ ጋር አስተያየው።

ዮሐ 11፡11 *«ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቶአል እኔም ከእንቅልፍ ላስነሳው እሄዳለሁ» አላቸው፤*

ማር 12፡26-27 *ስለሙታን መነሳት ግን በሙሴ መፅሀፍ ይኸውም ስለቁጥቋጦው በተነገረው ክፍል እግዚአብሔር እኔ የአብርሀም አምላክ የይስሐቅ አምላክ ነኝ ያለውን ላላነበባችሁም? እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም ስለዚህ እጅግ ተሳስታችኋል።»* አለ

ሐዋ 7፡60 *እስጢፋኖስ «ጌታ ሆይ ይህን ሀጢአት አትቁጠርባቸው ብሎ ጮኸ ይህን ካለ በኋላም አንቀላፋ።»*

እነዚህ አዲስ ኪዳናዊ መግለጫዎች ሞትን ከእንቅልፍ እኩል አድርገውታል።

ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህንኑ ሲጋዊ ሞት ሲያብራራ በሮሜ 8፡38-39

*«...ይህን ተረድቼያለሁ ሞትም ይሁን ሕይወት...በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም» አለ ይልቁኑ በፊል. 1፡23 በሞት መለየት ጥቅም እንዳለው አመላከተ «በእነዚህ በሁለቱ እጨነቃለሁ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልሆን እናፍቃለሁ ይህ እጅግ የተሻለ ነውና...»*

*ሀ.* በስነ ፍፃሜ ግንዛቤያችን ላይ ስለሞት ያለን ግንዛቤ በጣም ግልፅ ሊሆን ስለሚገባው ነው ይህን መዘርዘር ያስፈለገው፤ ዝርዝሩን ከሶስት አቅጣጫ እናጢነው፡-

ለ. ኢየሱስ ስለሞት ባስተማረው ትምህርት ላይ፣

ሐ. በኢየሱስ ትንሳኤ ላይ፣

መ. የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በእምነት በሚገኘው ሕይወት ላይ ያለውን ይዞታ እንፈትሽ።

በማር 5፡39-40 ሞት እንቅልፍ ነው «...ተኝታለች እንጂ አልሞተችም አላቸው ሰዎቹ ግን ሳቁበት (የሳቁት በእርግጥ ሞታ ስለነበር ነው)

ዮሐ 11፡26 ኢየሱስም እንዲህ አላት «ትንሳኤና ሕይወት እኔ ነኝ በእኔ የሚያምን ቢሞት





እንኳ በሕይወት ይኖራል»።

1ቆሮ 15፡3 «...ቅዱሳት መጽሐፍት እንደሚሉት ክርስቶስ ስለ ሀጢአታችን ሞተ ተቀበረ» የሞት ምንነትና ፍፃሜውን ያስረዳል።

***

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በስፋት የተስተናገደ ትምህርት አንዱ የክርስቶስ ዳግም መምጣት ነው

ማቴ 16፡27 *የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ስራው ያስረክበዋል።*

ማር 8፡38 *በዚህም በዘማዊና በኃጢአተኛ ትውልድ መካከል በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ የሰው ልጅ ደግሞ በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላዕክት ጋር በመጣ ጊዜ በእርሱ ያፍርበታል*

ሉቃ 21፡27 *በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በኃይልና በብዙ ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል። ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቦአልና አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሱ።*

ዮሐ 21፡22 *ኢየሱስም እስከመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ? አንተ ብቻ ተከተለኝ አለው፡፡*

ሐዋ 1፡16 *ወንድሞች ሆይ ኢየሱስን ለያዙት መሪ ስለ ሆናቸው ስለ ይሁዳ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በዳዊት አፍ የተናገረው የመጽሐፍ ቃል ይፈፀም ዘንድ ይገባ ነበር*

1ቆሮ 15፡23 *ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው፤ በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው።*

1ተሰ. 1፡10 *እነርሱ ራሳቸው ወደ እናንተ መግባታችን እንዴት እንደነበረ ስለ እኛ ይናገራሉና ለህያውና ለእውነተኛ አምላክ ታገለግሉ ዘንድ ከሙታንም ያስነሳውን ልጁን እርሱንም ኢየሱስን ከሚመጣው ቁጣ የሚያድን ከሰማይ ትጠብቁ ዘንድ ከጣኦቶች ወደ እግዚአብሔር እንዴት ዘወር እንዳላችሁ ይናገራሉ።*

2ተሰ. 1፡7 *ጌታ ኢየሱስ ከመላእክት ጋር ከሰማይ በእሳት ነበልባል ሲገለጥ መከራን ለሚያሳዩአችሁመከራን፣ መከራንም ለምትቀበሉ ከእኛ ጋር እረፍትን ብድራት አድርጎ እንዲመልስ በእግዚአብሔር ፊት በእርግጥ ጽድቅ ነውና።*